# የምሑራን አስተያየት

<u>ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት፤</u> « ....... ይህ አምባሳደር ዘውዴ ረታ ያሳተሙት « የኤርትራ ጉዳይ » የተባለው መጽሐፍ፤ በኛ በታሪክ ተማሪዎችና መምህራን በኩል እስካሁን ሙሉ በሙሉ ያላየናቸውንና ያልደረስንባቸውን ቀጥተኛ መረጃዎች ለብዙ ዓመታት በክብር ጠብቀው በማጥናትና በማመሳከር፤ አዲስ የተጣራ ዘገባ ስለአቀረቡልን ደራሲውን በሕዝብ ፊት እናመሰግናለን ....... »

<u>ፕሮፌሰር መርዕድ ወልደአረጋይ</u> « ....... ይህ ዘውዴ ረታ አዘጋጅቶ ያቀረበልን መጽሐፍ አንደኛ/ ለኢትዮጵያውያን የመሥሪያ ቋንቋ በሆነው በአማርኛ በመጻፉ፤ ሁለተኛ/ ኢትዮጵያዊና ሀገራዊ በሆኑ ምንጮች ተመሥርቶ በመጻፉ፤ ለዚህ ውስብስብ መስሎ ለሚታየው የኤርትራ ጉዳይ አስተማማኝ የሆነ ግንዛቤ ይሰጣል ብዬ አገምታለሁ ........ »

<u>ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ</u> « ........ የዛሬ ሠላሳ ዓመት ግድም አምባሳደር ሐዲስ ዓለማየሁ በሎንዶን ቢሮዋቸው የቀመሙትን ፍቅር እስከ መቃብር የተሰኘውን የዘመናችን ምርጥ ልብወለድ ድርሰት ለአንባቢያን አቀረቡ:: ዛሬ ደግሞ አምባሳደር ዘውዴ ረታ ሌላ ፍቅር እስከ መቃብር ይዞልን ብቅ ብሏል:: ........ ደራሲው ለአፄ ኃይለሥላሴ መንግሥት በነበረው ቀረቤታና በተለይም ለኤርትራ ጉዳይ የታሪኩን ሁለት አበይት ተዋንያን፣ ማለትም የአክሊሉ ሀብተወልድን እና የአስፍሐ ወልደሚካኤልን አመኔታ በማግኘቱ፤ አያሌ ብርቅ የሆኑ ሰነዶች ለጥናቱ ድምቀትና ጥልቀት ሊሰጡት ችለዋል:: በዚህም አማካይነት በትውልዶች መካከል ተፈጥሮ የቆየውን የዕውቀትና የልምድ ክፍተት ለመድፈን አንድ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል:: ........ አምባሳደር ዘውዴ ረታ ከፍተኛ የታሪክ ሥልጠና ሳያገኙ የተካነበትን የጋዜጠኝነት ሞያ በመመርኮዝ ታሪካዊ ሁኔታዎችን ተረድቶ በሚጥም ቋንቋ ትልቅ ገፀ-በረከት ስለአቀረበልን፣ እናመሰግነዋለን:: ....... »

<u>አቶ ተካልኝ ገዳሙ</u> « ....... አቶ ዘውዴ ረታ ያለመታከት፣ ሰባት ዓመት ሙሉ ለመጽሐፉ ዝግጅት በየአገሩ እየሄዱ ሰነዶችን በማጥናት፤ ኢትዮጵያም ውስጥ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸውን የቀድሞ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ባለሥልጣኖች በማነጋገር፤ ታሪኩን በስፋትና በጥልቀት ለማቅረብ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል:: ........ አቶ ዘውዴ ረታ በማያስለችና በማይፈታተን አማርኛ፤ ከአድልዎ ነፃ በሆነ መንፈስ ይህንን መጽሐፍ በማቅረባቸው፤ ለኢትዮጵያ ታሪክ፣ ለታሪክ ባለሞያዎችና አፍቃሪዎች ከፍተኛ ውለታ ስለዋሉ፣ ሊመሰገኑ ይገባል:: ....... »

## በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት

# የኤርትራ ጉዳይ

1941 - 1963

(እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር)

ዘውዴ ረታ

# የደራሲው መብት

# በሕግ የተጠበቀ ነው::


## ማሳሰቢያ

የኤርትራ ጉዳይ የተመረመረውና የተጠናው፤ በመጀመሪያ በአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ምክር ቤት፤ ቀጥሎ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ስለሆነ፤ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ታሪኩ መሠረቱን ጠብቆ እንዲሄድ የተጻፈው፤ እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር መሆኑን ደራሲው በቅድሚያ ያመለክታል::

# ማውጫ

## ክፍል አንድ
### መቅድም

ገጽ

1. ከጸሐፊው ........ 9
2. መረብ ምላሽ ወይም ምድሪ - ሀማሴን ........ 12
3. የተፈሪ መኮንን ምኞትና ተስፋ ........ 14

## ክፍል ሁለት
### የኤርትራ ጉዳይ፣
### በአራቱ ኃያላን መንግሥታት ሸንጐ
### (ከመስከረም 1945 - 1948)

ገጽ

1. የፖትስዳም ውሳኔ እና የሎንዶን ጉባኤ፤ ........ 23
2. የፓሪስ ስብሰባ፤ ........ 32
3. የፓሪሱ የሠላም ጉባኤ፤ ........ 44
4. የጣልያን ይቅርታ፤ ........ 58
5. የግብፅ ጥያቄ፤ ........ 68
6. የሠላም ጉባኤው ፍጻሜ፤ ........ 70
7. የአራቱ ኃያላን መርማሪ ኮሚሽን በኤርትራ፤ ........ 74
8. የኤርትራ የፖለቲካ መሪዎች ከመርማሪው ኮሚሽን ጋር፤ ........ 80
9. ሐቁን የሸፈነ የምርመራ ውጤት፤ ........ 91

## ክፍል ሶስት
### የኤርትራ ጉዳይ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት
### በሶስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ
### (ሚያዝያ - ግንቦት 1949)

ገጽ

1. ከኃላፊነት መሸሽ ........ 96

2. ሱማሌ ለጣልያን ትሰጥ፤ ኤርትራ በሁለት ትከፈል፤ (አሜሪካና እንግሊዝ) ....97
3. የመስኮብ ውርጅብኝ ........ 106
4. ስፎርሳ እና አክሊሉ ........ 110
5. የአምሣለ ኀት ጉባኤና ውሳኔ ........ 120
6. በኒውዮርክ ያልተጠበቀ ደስታ ........ 126
7. አቶ አክሊሉ፤ የትኛውን ይከተሉ? ........ 129
8. ኢትዮጵያና ጣልያን ........ 132
9. የላቲን አሜሪካ አገሮች፤ የጣልያን ጠበቆች ........ 138
10. ኢትዮጵያና አራቱ ኃያላኖች ........ 142
11. የቤቨንና ስፎርሳ ስምምነት ........ 150
12. የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት፣ በንዑስ ኮሚቴ "15" ........ 158
13. የዋናው ኮሚሲዮን ውጤት ........ 163
14. ጠቅላላው ጉባኤ፣ ከውሳኔው በፊት ........ 168
15. የማክሰኞ ግንቦት "17" ድራማ ........ 172
16. ዕድሜ ለሀይቲ መልዕክተኛ ........ 174
17. ጥሩው ዕድል አመለጠ ........ 178
18. የጃንሆይ አመለካከት ........ 181
19. የጓደኞች ትችት ........ 188

## ክፍል አራት

## የኤርትራ ጉዳይ በአራተኛው ጠቅላላ ጉባኤ

## (መስከረም- ኅዳር 1949)

ገጽ

1. ለመስከረሙ ቀጠሮ የኢትዮጵያ ዝግጅት ........ 193
2. የጣልያን ሤራ ........ 204
3. የአራቱ ኃያላኖች አቋም ........ 209
4. ጠቅላላው ጉባኤ ሥራውን ሲጀምር ........ 212
5. የኤርትራ ጉዳይ በዋናው ኮሚሲዮን ........ 216
6. ኤርትራ! በኢብራሂም ሡልጣን አስተያየት ........ 227
7. ኢብራሂም ሡልጣን ከኢትዮጵያ መልዕክተኞች ጋር ........ 229

8. ሕዝቡ የጠየቀው ኢትዮጵያዊነትን ነው ........ 241
9. ንዑስ ኮሚቴ "17" ........ 244
10. የዋናው ኮሚሲዮን ችሎት ........ 255
11. የጠቅላላው ጉባኤ ውሳኔ ........ 259
12. የአክሊሉ ምሬት "....... ጻበ ለጠየቀ ድንጋይ ......" ........ 264
13. በአዲስ አበባ እና በሮማ ........ 271

## ክፍል አምስት

## የኤርትራ ጉዳይ በአምስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ

## (የካቲት - ታህሣሥ 1950)

ገጽ

1. መርማሪው ኮሚሽን በኤርትራ ........ 284
2. መርማሪው ቡድን ከኢትዮጵያ ጋር ........ 288
3. የኤርትራ ጉዳይ ይመለከተናል የሚሉ አገሮች ........ 291
4. የአምስቱ ኮሚሽነሮች ዳኝነት ........ 292
5. የፌዴሬሽን መፍትሔ ........ 299
6. የአምስተኛው ጉባኤ ሂደት ........ 306
7. የመጨረሻው ውሳኔ ........ 313
8. ደስታና ቅሬታ ........ 321
9. ለኤርትራ ሕገ መንግሥት ዝግጅት ኮሚሽነር ተመረጠ ........ 329
10. በአሥመራ አዲስ ላይዘን ኦፊሰር ........ 330
11. የማቲየንሶ ሕገ መንግሥት ........ 333

## ክፍል ስድስት

## መንግሥቲ ተድላ-ቆተድላ ባይሩ መንግሥት

## (መስከረም 1952 - ሐምሌ 1955)

ገጽ

1. ተድላ ባይሩ የመጀመሪያው የኤርትራ መሪ ........ 360
2. የበዓሉ አከባበር ........ 366
3. ንጉሠ ነገሥቱ መረብን ከፈቱ ........ 370

4. መንግሥቲ ተድላ ..... 372
5. ተድላና ወልደአብ ሁለት ባለጋራዎች ..... 378
6. ኤርትራ የኢትዮጵያ እይደለችም (ወ.ወ.ማ) ..... 382
7. የተከበሩ ስደተኛ ..... 384
8. ድፎ ዳቦ ..... 391
9. ደጃዝማች ፌዴራሊስት ..... 399
10. ያዝልቅልዎ! ..... 405
11. ጫማ በእግር ልክ ካልሆነ ..... 408
12. ፌዴሬሽኑ በሕይወት አለ ወይ? ..... 413
13. ፌዴሬሽኑ ቢፈርስልኝ? (ተድላ ባይሩ) ..... 417
14. ፌዴሬሽኑ ይቀጥል ..... (የጃንሆይ ውሳኔ) ..... 422
15. ብቸኛው ተድላ ..... 437
16. ተድላ ከወልደጊዮርጊስ በኋላ! ..... 440
17. የመሰናበቻው ዋዜማ ..... 441
18. አልቻልኩም! ያውላችሁ ..... 445
19. ወራሽ ማን ነው? ..... 450
20. ደጀጠኒው ደጃዝማች ..... 453

## ክፍል ሰባት

## የአስፍሐ ወልደሚካኤል መንግሥት

(ነሐሴ 1955 - ኅዳር 1962)

ገጽ

1. አስፍሐ ማን ነው? ..... 461
2. ዳግማይ መራሀ መንግሥቲ ..... 466
3. የመጀመሪያው ዓመት ..... 469
4. ሁለተኛው የአስፍሐ ዘመን ..... 484
5. ባንዲራው የኢትዮጵያ ሆነ ..... 486
6. በኢትዮጵያ ሁለት መንግሥት የለም ..... 488
7. ሶስተኛው ዘመነ አስፍሐ ..... 490

8. የፌዴሬሽኑ መፍረስ አስፈላጊ ነበር ............ 492
9. ባይ ባይ ፌዴሬሽን ............ 502

## ክፍል ስምንት

## ከፌዴሬሽኑ በኋላ

(ጥር - ሰኔ 1963)

ገጽ

1. ፌዴሬሽኑ በፈረሰ ማግሥት ............ 510
2. የተድላ ዕቁቢት ትራጄዲ ............ 517
3. መጨረሻው? ............ 527

## ክፍል አንድ

### መቅድም

ገጽ

4. ከጸሐፊው .................... 9
5. መረብ ምላሽ ወይም ምድረ - ሀማሴን .................... 12
6. የተፈሪ መኩንን ምኞትና ተስፋ .................... 14

# ከጸሐፊው

ስለ ኤርትራ ጉዳይ አዘጋጅቼ የማቀርበው ይህ መጽሐፍ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን የነበረውን ታሪክ የሚገልጽ ስለሆነ፣ ከጥቂት ዓመታት በፊት ከኢትዮጵያ ቤተሰብነት ወደ ጉረቤትነት የተለወጡትን የዛሬዎቹን ኤርትራውያኖችና ዛሬ ያሉበትን ሁኔታ አይመለከትም። ኤርትራውያኖች እናታቸው ከነበረችው ከኢትዮጵያ ለመለየት ስለአደረጉት ረዥም ጉዞና፣ በመጨረሻም ነፃነትን ለመቀዳጀት እንዴት እንደበቁ ታሪካቸውን ጽፈው እስኪያቀርቡልን እንጠብቃለን። ከዚህ በፊት ግን የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች፣ እውነተኛውን ጉዳይ በትክክል ሊያውቁት የሚገባ የሀያ ዓመታት የታሪክ ሂደት አለ። ይኸውም፣

1. በኤርትራ ውስጥ እጅግ አብዛኛው ሕዝብ፣ ከባዕድ አገዛዝ ለመላቀቅና ኢትዮጵያዊነቱን ለማስመለስ፣ <u>«ኢትዮጵያ ወይ ሞት»</u> ብሎ መከራና ፈተና እየተቀበለ ምን ያህል እንደታገለ፣

2. የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ለማዋሀድ፣ በኃያላን መንግሥታቶች ዳኝነት እና በተለይ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለብዙ ዓመታት ያደረገው ፋታ የሌለው ሙግት እስከ ምን ድረስ እንደነበረ፣

3. በዓለም ማህበር ሸንጎ ላይ ኤርትራ በፌዴሬሽን ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል ፍርዱ እንዴት እንደተወሰነና፣ ከዚያም ለአሥር ዓመታት የተካሔደው የፌዴሬሽን አስተዳደር በምን መልክ ይሠራበት እንደነበረ፣ ኋላም በምን አኳኋን እንደፈረሰ፣

እውነተኛውን ታሪክ የኢትዮጵያና የኤርትራ ሕዝቦች አውቀውት የየራሳቸውን አቋም መያዝ ይገባቸዋል ብዬ ስለአመንኩ፣ ባለኝ አቅም ለዚህ ጉዳይ ምርምርና ጥናት ብቻ የሰባት ዓመታት ጥረት አድርጌአለሁ።

የአፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት ካበቃ ከስልሣ ዓመታት በኋላ፣ በኢትዮጵያ እጅ የነበረው የኤርትራ ጉዳይ፣ ትክክለኛውና እውነተኛው ሥዕል፣ ለዛሬውና ለመጭው ትውልድ በሀቅ ካልቀረበ፣ የመገንጠሉና ለነፃነት የተደረገው ውጊያ ብቻውን ብዙ ሺህ ጊዜ ተራብቶ ቢጻፍ፣ ታሪኩን የተሟላ አያደርገውም።

እኛ በኢትዮጵያችን የምናምንና የምንኮራ ሕዝቦች፣ ኤርትራ ነፃ መንግሥት ሆና በመገንጠሏ ምንም ዓይነት ቅሬታ አይሰማንም። ኢትዮጵያዊነት ጉድቶናል፣ ነፃ መሆን ይጠቅመናል ብለው፣ ለብዙ ዓመታት ተዋግተው መለየትን የመረጡት ወንድሞቻችን ኤርትራውያኖች ስለሆኑ፣ በምርጫቸውና በውሳኔያቸው የምናዝንበት ምክንያት የለንም። እንደዚሁም በመካከላችን ያለውን የዘርና የባሕል አንድነት፣ ዛሬ ከቤተሰባችን ወጥተዋል ብለን መሠረታዊ የአንድነት ታሪካችንን እንክድም። በፌዴሬሽን አስተዳደር ሆነ በፍጹም አንድነት ዘመን፣ አብረን በኖርንበት በአርባ ዓመታት ጊዜ ውስጥ፣ እኛ ኢትዮጵያውያን በወንድሞቻችን በኤርትራውያን ላይ ምንም ዓይነት በደል እንዳልፈጸምንባቸው መዘንጋት የለባቸውም። የአንድ ቤተሰብ ምርቶች በሆኑ ሕዝቦች መካከል አለመግባባት ቢፈጠ

ር፣ ወይም በመንግሥት በኩል የአስተዳደርና የፍርድ ጉድለት ቢደርስ፣ ሁሉም በየመልካቸው ለየብቻቸው መታየት ይገባቸዋል እንጂ፣ በአንድ ጐተራ ውስጥ ታምቀው በአንድነት መወገዝ የለባቸውም::

ኤርትራውያን ወንድሞቻችን ለሃምሳ ዓመታት የጣልያን ቅኝ ሆነው ከተስቃዩ በኋላ፣ ለአሥር ዓመታት በእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር በተያዙበት ዘመን ኢትዮጵያዊነታቸውን ለማረጋገጥ <u>«ኢትዮጵያ ወይ ሞት»</u> ብለው ያን ሁሉ መከራና ፈተና ለምን ሲሉ እንደተቋቋሙ፤ በመጨረሻም እናታችን ነሽ ብለው ከኢትዮጵያ ጋር ከተዋሀዱ በኋላ፣ ምን ቢጐድልባቸው መገንጠልን እንደመረጡ፤ ምን ቢበደሉ እናት ኢትዮጵያን እንደጠሉ፤ ታሪክ የሚያቀርብላቸውን ጥያቄ በወጉ መመለስ ያለባቸው እነሱ ናቸው::

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን የነበረውን የኤርትራን ታሪክ እንድጽፍ ያተጉኝ ብዙ ሰዎች ናቸው:: በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ ዝርዝሩን ለማውጣት የማይመች ስለሆነ ብዙዎች ደራሲዎች እንደሚያደርጉት፣ በመጨረሻው ገጽ ላይ አስፈላጊውን አገልጻለሁ:: እኔም የኤርትራን ታሪክ አንድ ቀን መጻፍ አለብኝ የሚል ሀሳብ ያሳደረብኝ በሕይወቴ ዘመን ምን ጊዜም የማልረሳው አንድ ትዝታ አለኝ::

እንደ ኤውሮፓ አቆጣጠር በመስከረም 1953 ዓ.ም በጋዜጣና ማስታወቂያ መሥሪያ ቤት የአዲስ አበባ ራዲዮ ወሬ አንባቢና ሪፖርተር ሆኜ ስቀጠር፤ ዕድሜዬ አሥራ ስምንት ዓመት ነበር:: ስለ ዜናዎች አሰባሰብና አቀራረብ በዚያን ጊዜ ለራዲዮ የአማርኛ ዜና አዘጋጅ ከሆኑት ከአቶ አስፋ ይርጉ ዘንድ በመለማመድ ለስድስት ወራት ከቆየሁ በኋላ፣ በክቡር አቶ መኰንን ሀብተወልድ ትዕዛዝ የቤተመንግሥት ዜና ሪፖርተር እንድሆን ተመደብኩ:: በዚሁ በአዲሱ መደቤ ያጋጠመኝ የመጀመሪያው የሪፖርተርነት ሥራ፣ ንጉሠ ነገሥቱ የኤርትራን ቺፍ ኤግዜኩቲፍ ደጃዝማች ተድላ ባይሩን አስጠርተው ማነጋገራቸውን የሚገልጽ ዜና ማዘጋጀት ነበር:: በተሰጠኝ መምሪያ መሠረት ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት በመገኘት ያየሁትን፤ በሚከተለው አኳኋን ጽፌ አቀረብኩ::

« ...... ከጠዋቱ ልክ ሶስት ሰዓት ከሩብ ሲሆን የኤርትራ ቺፍ ኤግዚኩቲፍ ክቡር ደጃዝማች ተድላ ባይሩ ከግቢ ሚኒስቴር በተላከላቸውታርጋ በሌለው ልዩ አውቶ ሞቢል አምሣለ ገነት ቢሮ አጠገብ ሲደርሱ፤ ሻለቃ አስፋ ደምሴ (ኋላ ሌፍተናንት ጄኔራል) ምክትል የልፍኝ አስከልካይ ተቀበሏቸው:: ከዚያም ከግርማዊነታቸው ቢሮ መግቢያ ዋናው በር ላይ ሲደርሱ፣ በመጀመሪያ ቀኛው የልፍኝ አስከልካይ ኮሎኔል መኰንን ደነቀ፣ (ኋላ ብ.ገኔራል) ቀጥሎም የግርማዊነታቸው ልዩ ጸሐፊ አቶ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድ ( ኋላ ጸሐፊ ትእዛዝ) በሞቀ የእጅ ሰላምታ ተቀበሏቸው:: ወዲያውም ከግርማዊነታቸው ቢሮ ገብተው ለጥ ብለው እጅ ሲነሡ፣ ጃንሆይ <u>ተድላ እንዴት ሰነበትክ</u> ? የሚል ቃል አሰሟቸው:: ከዚያም ወደ ግርማዊነታቸው ቢሮ ጠጋ ብለው፣ ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደ ጊዮርጊስ የጽሕፈትና የፍርድ ሚኒስትር፣ ክቡር አቶ አክሊሉ ሀብትወልድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፤ ክቡር አቶ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድ የግርማዊነታቸው ልዩ ጸሐፊ፣ አቶ ገብረወልድ እንግዳወርቅ የጽሕፈት ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር በተገኙበት፤ የሥራ ፍሬያቸውን ዝርዝር በማቅረብ ለሃምሳ አራት ደቂቃዎች ከተነጋገሩ በኋላ ወደ ማረፊያቸው ወደ ራስ ሆቴል ተመልሰዋል::........»

ይህ ወሬ ከማታው በሁለት ሰዓት በራዲዮ ከመነገሩ በፊት የጋዜጣና የማስታወቂያ ቦርድ መርምሮ መፍቀድ ነበረበት:: ከእኩለ ቀን በኋላ በአሥራ አንድ ሰዓት የጻፍኩትን ይዤ ስባቱን የቦርድ አባሎች ለማስፈቀድ ስቀርብ፣ የመጀመሪያ ፈተናዬ ስለሆነ፣ አልፋለሁ አላልፍም ብዙ ሥጋት ነበረብኝ:: በስብሰባው ከተገኙት የቦርድ አባሎቹ መካከል፣

- አቶ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ (ኋላ ብላታ) የአዲስ ዘመንና የሰንደቅ ዓላማችን ጋዜጦች ዲሬክተር፣
- አቶ መኰንን ወርቃገኘሁ የአዣንስ ዲሬክተር፣
- አቶ ከበደ አስፋው የሂሣብና የራዲዮ ዲሬክተር፣
- አቶ አድማሱ ባድማ የሳንሱር ዲሬክተር፣

የተዘጋጀው ዜና አንዳንድ መጠነኛ መሻሻል ተደርጐለት በራዲዮ እንዲነገር፣ በየጋዜጦቹም እንዲወጣ መስማማታቸውን ገለጡ:: አቶ አሐዱ ሳቡሬ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ ዲሬክተር፣ « ...... ይህ ወጣት ሪፖርተር የሥነ ሥርዓቱን ሥዕል ደህና አድርጐ በዝርዝር በመከታተሉ አደንቃለሁ:: ወደፊትም የተሻለ ሪፖርት እንደሚያደርግ አምናለሁ:: ነገር ግን ወሬው አሁን በተጻፈው መልክ እንዲነገር አልደግፍም:: የወሬው ቁም ነገር፣ ደጃዝማች ተድላ ለሥራ ጉዳይ ተጠርቶ አዲስ አበባ መምጣቱና ጃንሆይ ዘንድ ቀርቦ መነጋገሩ ብቻ ነው:: ይኸ ወሬ ከሁለት ዓረፍተ ነገር መብለጥ የለበትም ...... » አሉ:: አቶ ታደሰ አበበ የመሥሪያ ቤቱ ዋና ጸሐፊ፣ አራቱ የቦርድ አባሎች ዜናው በተዘጋጀው መልክ ተሻሽሎ እንዲነገር የተስማሙትንና፣ አቶ አሀዱ ሳቡሬ ባጭሩ ይጻፍ ያሉትን፣ መሥሪያ ቤቱን በበላይነት የሚመሩት ክቡር አቶ መኰንን ሀብተወልድ እንዲወስኑ ባቀረቡት ሀሳብ መሠረት፣ ጉዳዩ ወደ ገንዘብ ሚኒስትሩ ተላከ:: ከምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል የአቶ መኰንን ውሳኔ ደረሰ::

« ..... ይኸ ልጅ ያየኸውን ሁሉ ጽፈህ አቅርብ ተብሎ የታዘዘውን ማለፊያ ሠርቷል:: ለወደፊቱ የሚማር ስለሆነ ማትጋት ነው:: ለአሁኑ ጉዳይ አቶ ሳቡሬ እንዳለው ባጭሩ ይሁን ...... » ብለው የገንዘብ ሚኒስትሩ በሰጡት ትዕዛዝ መሠረት አስፈላጊው ተፈጸመ::

ይህን ጉዳይ ለምሣሌ ያህል ያነሳሁት በፌዴሬሽኑ ጊዜ የኤርትራ ቺፍ ኤግዜኩቲፍ አዲስ አበባ በመጡ ቁጥር፣ ከአውሮኘላን ጣቢያ ጀምሮ እስከ ቤተ መንግሥቱ፣ የሚደረገው የፕሮቶኮል ጀብ ጀብ በምን ምክንያት እንደሆነ ለማወቅ፣ ከዚያን ዘመን ጀምሮ በአእምሮዬ ላይ ተቀርጾ የቀረውን የመከታተል ፍላጐት ለመግለጽ ነው:: በዚያን ጊዜ ደጃዝማች ተድላን ስመለከታቸው፣ ለንጉሠ ነገሥቱ ልዩ መልዕክት ለማቅረብ የመጣ አንድ የውጭ አገር መንግሥት እንደራሴ አድርጌ እንጂ፣ የአገራችን ጉዳይ ባለሥልጣን መስለው አይታዩኝም ነበር:: ለምሣሌ ቢትወደድ መኰንን እንዳልካቸው ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ራስ አበበ አረጋይ የአገሬ ግዛት ሚኒስትር፣ ወደ አምሣለ ገነት ቢሮ ሲገቡ፣ በእልፍኝ አስከልካዮችም ሆነ በልዩ ጽሕፈት ቤት በኩል፣ ለደጃች ተድላ እንደሚደረገው መንከባከብ አይደረግላቸውም:: ከሁለት ዓመት በኋላ፣ ደጃዝማች ተድላ ተሽረው ፊታውራሪ አስፍሐ ሲተኩ፣ ያ ሁሉ የፕሮቶኮል ጀብ ጀብ በአንድ ጊዜ እንደቀዘቀዘ የማየት ዕድል አጋጥሞኛል::

በፓሪስ የጋዜጠኝነትን ሞያ አጥንቼ ከተመለስኩ በኋላ ለአሥር ዓመታት በማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ ለአምስት አመታት በውጭ ጉዳይ ዲፕሎማሲ ሥራ ባገለገልኩበት ዘመን፣ የኤርትራን ጉዳይ በሰፊው ተከታትያለሁ:: እንደ አውሮፓ ዘመን አቆጣጠር በ1962 ዓ.ም የኤርትራ ፌዴሬሽን ሲፈርስ በጋዜጠኝነት አሥመራ ተልኬ ሁሉንም አይቻለሁ:: ከዚያም በኋላ በኤርትራ ጉዳይ ከፍተኛ ሚና የተጫወቱትን የኢትዮጵያንና የኤርትራን ታላላቅ ሰዎች እያነጋገርኩ የታሪኩን አካሄድ በየመልኩ በዝርዝር ለማጥናት ጥሩ ዕድል አጋጥሞኛል::

1. ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ በዓለም ሸንጐ ላይ ለሰባት ዓመታት ተሟግተው ድሉን ያገኙት ጸሐፊ ትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ፣

2. ኤርትራን ከፌዴሬሽን አስተዳደር ወደ ፍጹም አንድነት ለማዋሀድ ያበቁት፣ ቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል፣

በሰጡኝ ሰነዶች በሰፊው ተጠቅሚያለሁ:: ከነዚህ ሌላ በአዲስ አበባና በሮም፣ በዋሽንግተንና በኒውዮርክ፣ በሎንዶንና በፓሪስ እየተዘዋወርኩ ብዙ ምርምርና ጥናቶች አድርጌአለሁ::

ማንም ሰው እንደሚያውቀው የኤርትራ ጉዳይ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ምንጊዜም የሚኖር ነው:: ሰው ሁሉ የሚያውቀውን ጽፎ ማስታወሻ ቢተው፣ በተለይ አኛን ለሚተካው ትውልድ የጠለቀ ምርምር ለማድረግ እንደሚረዳው አይጠረጠርም:: ይህ እጅግ የተወሳሰበ የታሪክ አካሄድ ያለው ጉዳይ ፣ በጣት በሚቆጠሩ ሰዎች ብዕር ብቻ መቆም የለበትም:: በአለንበት ዓለም ላይ አንድ ትልቅ ታሪክ በአንድ ዘመን ብቻ ተጽፎ አይቆምም:: እንኳንስ በቅርቡ የተፈጸመው ቀርቶ፣ የጥንቱም ቢሆን በየጊዜው በሚደረገው ምርምር፣ አዳዲስ ሰነዶች ስለሚፈልቁ ጽሑፉ እንደቀጠለ ነው:: ለምሣሌ የዛሬ ሁለት መቶ ዓመት የተፈጠረው የፈረንሣዩ የቀዳማዊ ናፖሊዮን ታሪክ እስካሁን ተጽፎ አላለቀም:: በዚህ ዓይነት ሲታይ የኛ የኢትዮጵያኖችን ጉዳይ ገና አልተጀመረም ማለት ይቻላል::

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን የተከናወነውን የኤርትራን ጉዳይ፣ በበኩሌ አሟልቼ ለማቅረብ ብዙ ጥረት ስለአደረኩ፣ አንባቢዎች ጠቃሚ ነገሮች እንደሚያገኙበት ተስፋ አደርጋለሁ::

# መረብ ምላሽ ወይም ምድረ ሀማሴን

ከአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ፣ ኮሎኒያሊስት ጣልያን በመጀመሪያ አሰብን፣ ቀጥሎም ምፅዋን፣ ከዚያም ቀስ በቀስ እየተጓዘ እስከ መረብ ወንዝ ድረስ ያሉትን አውራጃዎች « ኤርትራ » ብሎ በመሰየም ቅኝ ግዛቱ አድርጐ ከማወጁ በፊት፣ ይህ ክፍለ ሀገር « መረብ ምላሽ ወይም ምድረ-ሀማሴን » እየተባለ ይጠራ እንደነበረ ጥንታዊ ታሪኮቹ ያስረዳሉ::

ከክርስቶስ ልደት በፊት በመጀመሪያውና በሁለተኛው ሺህ ዓመታት ዘመን ውስጥ የካምና የሴም ነገዶች በቀይ ባሕር በኩል ተጉዘው ወደ አገራችን ሲመጡ፣ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸው በዚህ ኮሎኒያሊስት ጣልያን « ኤርትራ » ብሎ በሰየመው መሬት ላይ ነው:: ከክርስቶስ ልደት በኋላም እስከ አሥረኛው መቶኛ

ዘመን ድረስ፣ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ « አክሱም » ስለነበረ፣ ነገሥታቶቹ እስከ ቀይ ባሕር ድረስ ያለውን ግዛት አጠቃለው አስተዳድረዋል።

በዚህ የጥንታዊው የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ በሆነው በአክሱምና በአካባቢው የተገኙት የታሪክ ቅርሶችና ሐውልቶች፣ የአገራችንን ጥንታዊ ሥልጣኔ የሚያስረዱ መሆናቸውን የዛሬዎቹም የታሪክ መርማሪዎች ስለአረጋገጡ፤ መረብ ምላሽ ወይም ምድረ ሀማሴን የተባሉት ሕዝቦች ለኢትዮጵያዊነታቸው የተለየ ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልግም።

የኢትዮጵያ ነገሥታቶች መንበር ከአክሱም ወደ ላስታ፣ ከላስታ ወደ ጐንደር፣ ከጐንደር እንደገናም ወደ አክሱም በተዘዋወረበት ዘመን፤ ይህን አገር ኮሎኒያሊስት ጣልያን « ኤርትራ » ብሎ በጦር ኃይል እስኪያዘበት እስከ 1885 ዓ.ም ድረስ፣ « ባሕር ነጋሽ » እየተባሉ በንጉሠ ነገሥት በሚሾሙ ታላላቅ ሰዎች ሲተዳደር የኖረ ነው። እርግጥ፣ የቀይ ባሕር አካባቢና የምፅዋ ወደብ ለሶስት ክፍለ ዘመናት ያህል በቱርኮች ተይዞ እንደነበረ፣ ከእነሱም ቀጥሎ ለጥቂት ዓመታት ግብፆች ይዘው የኛ ነው ለማለት መሞከራቸው አይካድም። ይሁን እንጂ ቱርኮቹም ሆኑ ግብፆች፣ በወደቡ ላይ የኢትዮጵያ ነገሥታቶች ያላቸውን የባሕር በር መጠቀሚያ መብት አናውቅም አላሉም። የወደቡም ሹማምንቶች የቱርኮቹን አስተዳደር መከተል ግዴታ ቢሆንባቸውም፣ ከኢትዮጵያ ነገሥታቶች የሚታዘዙትን ሁሉ አክብረው ከመፈጸም አላቋረጡም።

ከ1885 ዓ.ም በኋላ ኮሎኒያሊስት ጣልያን የመረብ ምላሽ አውራጃዎቹን «ኤርትራ» ብሎ የሰየመው እራሱ የፈጠረው አዲስ ስም ሆኖ አይደለም። «ኤርትራ» በአገሩ ዙሪያ ያለው የባሕሩ መጠሪያ የነበረ ነው። በጣሊያን ቅኝ አስተዳደር አገሩ «ኤርትራ» እየተባለ ለሃምሣ ዓመታት ከኖረ በኋላ፣ በ1941 ዓ.ም ጣልያንን አስለቅቀው እንግሊዞች አስተዳደሩን ሲይዙ፤ « ኤርትራ » የተባለውን ስም ወደ ቀድሞ መጠሪያው አልመለሱትም። የባሕሩ መጠሪያ የነበረው የክፍለ ሀገሩ ስም ሆኖ ለግማሽ ምዕተ ዓመት ስለቆየና ስለተለመደ፤ ወደ ቀድሞ ስሙ ለመመለስ አልተሞከረም። አንዳንድ ኤርትራውያኖች ኮሎኒያሊስት ጣልያን ለአገሩ የሰጠው ስም ጸንቶ የቆየው በአፄ ምኒልክ ቸልታ ነው ይላሉ። በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን የኢየሩሳሌም ሊቀጳጳስ የነበሩት አቡነ ፊልጶስ፣ በ1962 ዓ.ም ፌደሬሽኑ በፈረሰ ጊዜ ደስታቸውን በመግለጥ ለኤርትራ ዋና አስተዳዳሪ ለቢትወደድ አስፍሐ ወልደሚካኤል በጻፉት ደብዳቤ፣ « .... አፄ ምኒልክ ድካምና መከራ እንዳይነካቸው ሲሉ፣ የባሕራችንን ስም ለአገራችን መጠሪያ ለውጠ፣ ጠላታችን ጣልያን ያቀረበላቸውን ውል በመቀበላቸው፤ ይኸው ዛሬ ኤርትራ ተብለን ቀረን ...... » ብለዋል። በአቡነ ፊልጶስ አስተያየት ከአድዋም በፊት ሆነ ከአድዋም በኋላ፣ አፄ ምኒልክ ከጣልያን ጋር ሲዋዋሉ፣የአገሩ መጠሪያ «ኤርትራ » እንዳይባል ማስገደድ ይችሉ ነበር ማለቷ ነው።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ከ1945 ዓ.ም ጀምሮ፣ የዚህን አገር ኢትዮጵያነት፣ ለአራቱ ኃያላን አገሮችና ለዓለም መንግሥታት ማኅበር አመልክቶ ሲሟገት፣ መረብ ምላሽ ወይም ምድረ ሀማሴን ይባል የነበረውን የጥንቱን የአገሩን መጠሪያ አልተጠቀመም። ማመልከቻውን ያቀረበው ኮሎኒያሊስት ጣልያን እንደሰየመው « ኤርትራ » ብሎ ነው። በ1993 ዓ.ም እነዚህ የጥንት የመረብ ምላሽ ወንድሞቻችን ነፃነታቸውን ሲያውጁ፤ በዚሁ ጣልያን በሰየመው « ኤርትራ » በተባለው መጠሪያ ቀጥለዋል።

# የተፈሪ መኰንን ምኞትና ተስፋ

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ከሆኑበት ከ1917 ዓ.ም ጀምሮ የንግሥተ ሳባን አገር ለማስልጠንና ለማሳደግ፣ በዚያው መጠን የራሳቸውንም ታሪክ ካለፉት ነገሥታቶች የበለጠ ዝነኛ ለማድረግ፣ የተፈሪ መኰንን ጥልቅ ምኞትና ተስፋ ነበር::

የመረብ ምላሽ ክፍለ-ሀገር ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ፣ «ኤርትራ» በሚል ስያሜ የጣልያን ቅኝ ግዛት የሆነው፣ በአፄ ዮሐንስ ሞት፤ በአፄ ምኒልክ አቅም ማጣት፥ ከዚህም ጋር በኢትዮጵያ አንድነት መፍረክረክ ምክንያት ስለሆነ፤ ታሪክን መልሶ አቦታው ለመትከል ጊዜ ይወስዳል እንጂ ይፈጸማል እያሉ፤ ራስ ተፈሪ መኰንን ለአንዳንድ ታማኝ አገልጋዮቻቸው ይገልጹ እንደነበረ ይነገራል:: ልዑል ጌታችን፣ ይህን የተቀደሰ ዓላማዎን ከግቡ ለማድረስ የሚያስቡት ምን ጉዳና በመከተል ነው ? ..... ጦር አዘጋጅቶ ጣልያንን በመውጋት ? ወይስ የፈረንሣይንና የእንግሊዝን እርዳታ አግኝቶ ጣልያንን በማስገደድ ? የትኛው ይሆን? እያሉ፣ ታማኞቻቸው ለሚያቀርቡላቸው ጥያቄዎች የአልጋ ወራሹ መልስ የሚከተለው ነበር::

« ...... መጀመሪያ፣ ከአውሮፓ ኃያላን አገሮች አንዱ የሆነውን ጣልያንን ለመውጋት የሚያስችል አቅም እንደሌለን ደህና አድርገን ማወቅ አለብን:: በአሁኑ ሰዓት ጠላታችን ጣልያን የዚህ የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ድል አድራጊዎች ከሆኑት ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ ጋር ወንበር ይዞ ድል በሆኑት በጀርመንና በነምሣ (ኦስትሪያ) አገሮች ላይ ፍርድ ሰጪ ሆኗል:: የዛሬው ጣልያን ከሀያ ዓመት በፊት አፄ ምኒልክን የገጠማቸው ጣልያን አይደለም:: እኛም በዛሬው ሁኔታችን ከዚህ ቀደም በአድዋ ያገኘነውን ድል ዛሬም እንደግመዋለን ማለት ዘበት ነው::

ኢትዮጵያ የረዥም ዘመናት ታሪክና የአስተዳደር ሥርዓት ያላት አገር ስለሆነች፣ አዲሱን የባሕር ማዶ (የአውሮፓ) ሥልጣኔ ለመ ቀበል የተዘጋጀች መሆንዋን በዓለም ታላላቅ መንግሥታቶች ዘንድ ማሳወቅና ማሳመን አለባት:: በመጀመሪያ የምታስቀድመውም፣ በተለይ በአውሮፓ በጣም የተረገመችበትን <u>የባሪያን ነፃነት</u> ማረጋገጥ ነው::

ሁለተኛ፣ ዘመናዊ የሆነውን የአውሮፓን ሥልጣኔ ለመቀበል ዋናው መሠረቱ ትምህርትን ማስፋፋት ስለሆነ፤ በዚህ ረገድ የሚደረገው ብርቱ ጥረት ለኢትዮጵያ ዕድል፥ በር ከፋች ይሆናል::

በነዚህ ሁለት ዋና ዋና ቁም ነገሮች ላይ በብርቱ ሠርቶ ፍሬውን ማሳየት ሲቻል፤ የኢትዮጵያን መንግሥት ጠንካራነትና የሕዝቡን ተከታይነት፣ በዓለም ላይ ለማስመስከርና ለማሳመን የሚያግድ እንቅፋት አይኖርም:: ይህን ደረጃ ይዘን



« ...... ኢትዮጵያ፤ በትምህርትና በአስተዳደር የዘመኑን ሥልጣኔ ለመከተል መዘጋጀቷን ታላላቅ መንግሥታቶች ካመኑበት፤ በጠላት የተወሰዱባት አገሮቿንና የባሕር በሮቿን ለማስመለስ እንደሚረዷት ተስፋ ማድረግ ይቻላል።

(አልጋወራሽ ተፈሪ መኰንን)
1920 ዓ.ም

ከተገኘን፣ ኢትዮጵያ አለአግባብ በቅኝ ገዥዎች ተቆርጠው የተወሰዱባት አገሮቿ እንዲመለሱላት፣ ዘመናዊ ሥልጣኔን እንዳትቀበል የተዘጉባት የባሕር በሮቿ እንዲከፈቱላት፣ የምናቀርበውን የፍርድ ጥያቄ፣ አልሰማም የሚል የዓለም ዳኛ ሊኖር አይችልም:: ጥያቄያችንንም በምናቀርብበት ጊዜ ፈረንሣዮችም ሆኑ እንግሊዞች፣ ከእኛ ጋር ቆመው ጣልያንን ሊሞግቱልን እንደሚችሉ ተስፋ ማድረግ ይቻላል:: ነገር ግን በዚህ በተባለው አኳኋን እየሠራን ካልገፋንበት፣ እንኳንስ የተወሰዱብንን ግዛቶቻችንን ለማስመለስ ቀርቶ፣ አሁን የያዝነውን አገር፣ መቸውንም የማይተኛልን ጣልያን፣ ወይም ሌላ ባላንጣ መጥቶ አለአግባብ ነፃነታችንን ሊቀማን ይችላል:: ከባዕድ አገዛዝና ከመከራ ለመዳን፣ ነፃነታችንን በሠላም ይዞ ለመቆየት ያለን ዕድል፣ ሥልጣኔን ለመቀበልና አገራችንን ዘመናዊ ለማድረግ የምናሳየው ጥረት ብቻ ነው:: ይህንን ለገርማዊት ንግሥት ዘውዲቱ እና ለታላላቆቹ መሣፍንቶች አስረድቶ እንዲቀበሉት ለማድረግ እጅግ ከባድ ነው:: ሆኖም አስቸጋሪ ነው ብለን ደካሞች መሆን የለብንም:: እስከሚቻለን ሳንለለች መጣር አለብን:: ........ »

ይህ አስተያየት በጥልቀት ሲጤን ኢትዮጵያ ዘመኑ ያፈለቀውን ሥልጣኔ ለመቀበል፣ በትምህርትና በአስተዳደር ሥርዓት እርምጃ ካደረገች፣ ለነፃነቷ ዋስትና ለማግኘትና በኮሎኒያሊስት ጣልያን የተወሰደባትንም ግዛት ለማስመለስ ትችላለች፣ ብለው አልጋ ወራሽ ተፈሪ መኰንን ያላቸውን የቅርብና የሩቅ ዕቅድ ያመለክታል::

የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ በሆኑ በሰባት ዓመታት ውስጥ ዘመናዊ ትምህርት ቤት በመክፈታቸው፣ ተማሪዎችንም ለከፍተኛ ትምህርት ወደ አውሮፓ በመላካቸው፣ በአገር ውስጥም የሰው ልጅ ባሪያ እየተባለ የሚፈጸምበት ግፍ እንዲወገድ በማወጃቸው፣ አገራቸው በገኔቭ የዓለም መንግሥታት ማህበር አባል እንድትሆን በማስደረጋቸው፣ ኢትዮጵያ በዓለም ቤተሰብ መካከል ተገቢ ሥፍራ ያላትና የምትከበር አገር ሆና ታየቻቸው::

በ1924 ዓ.ም ባለሙሉ ሥልጣን አልጋወራሽ ተፈሪ መኰንን የአውሮፓን አገሮች ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጐበኙ፣ ለተማሪ ቤት ማስፋፊያና ለሆስፒታል መሥሪያ እርዳታ ከመጠየቃቸው በፊት፣ በመጀመሪያ ቅድሚያ የሰጡት ለኢትዮጵያ ሥልጣኔ ዕድገት እጅግ አስፈላጊ ነው ብለው የሚያምኑበትን የባሕር በር ለማግኘት ነበር:: ይህ ተፈሪ መኰንን የሚጠይቁት የባሕር በር አሰብ፣ ጅቡቲ፣ ወይስ በርበራ ? የትኛው ነው ? ሲባል፣ የአልጋወራሹ ምርጫ አሰብ መሆኑ ተነገረ:: ጣልያን በኤርትራ ላይ የነገሠው መጀመሪያ በአሰብ በኩል እግሩን አስገብቶ ነው:: ኢትዮጵያ የታሪኳን ቅርስና የተቀማችውን ግዛት የምታስመልሰው ቀስ በቀስ ስለሆነ፣ መጀመሪያ የአሰብ በር በእጇዋ ከገባ በኋላ ሌላው ይከተላል ብለው ተፈሪ መኰንን አሰበዋል:: የአልጋወራሹ ጥያቄ አሰብን ስለሆነ፣ ፓሪስ ላይ የተቀበሏቸው የፈረንሣይ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ሬይሞንድ ፖንካሬ (RAYMOND POINCARE) የአሰብ ባለቤት ለሆነው ለጣልያን መንግሥት ጥያቄያቸው መልካም አስተያየት እንዲያገኝ ከማግለድ በስተቀር፣ ሌላ የሚፈጽምላቸው ነገር አልነበረም::

ራስ ተፈሪ፣ ከፈረንሣይ በኋላ ጣልያንን በጐበኙበት ጊዜ፣ ቤኔቶ ሙሶሊኒ (BENETO MUSSOLNNI) በፓላሶ ቬኔሲያ (PALAZZO VENEZIA) ጽሕፈት ቤቱ የተቀበላቸው እጅግ በደመቀ ፕሮቶኮል ነበር:: ሆኖም ኢትዮጵያ የባሕር በር ብታገኝ ለዕድገቷ ምን ያህል እንደሚጠቅማት በመዘርዘር፣ የሲኞር ሙሶሊኒን

እርዳታ ሲጠይቁ፣ ፋሺስቱ መሪ አያፌዘ ወደፊት እናስብበታለን ከማለት በስተቀር የተሻለ መልስ ሊሰጣቸው አልፈለገም::

ከሰባት ዓመታት በፊት ኢትዮጵያን ለማስተዳደር ሙሉ ሥልጣን ሲሰጣቸው፣ በጥቂት ጊዜ ውስጥ አገራቸው በሥልጣኔ ገፍታ በአውሮፓ መንግሥታት ዘንድ የምትደመጥ ትሆናለች ብለው ተፈሪ መኰንን ሙሉ ተስፋ አድርገው እንደነበረ ይታወሳል:: ነገር ግን የአውሮፓን አገሮች በመጐብኘትና ከየመሪዎቹ ጋር በመነጋገር ሁኔታውን ሲመዝኑ፣ ኢትዮጵያ በብዙ ረገድ እጅግ ወደ ኋላ የቀረች መሆንዋንና ለተደማጭነትም ደረጃ እንዳልደረሰች ተገነዘቡ:: ይህንን በቶሎ ከተረዱ በኋላ፣ በጐበኟቸው አገሮች ሁሉ ስለ ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ መመለስ ለመነጋገር ወይም ጉዳዩን ለማንሳት ጨርሶ አልቃጡም:: ለሙከራ ወይም ለፈተና ያህል የባሕር በር መተላለፊያ በአሰብ በኩል እንዲሰጣቸው ላቀረቡት ልመና እንኳን፣ የሚያጠግብ ወይም ተስፋ የሚሰጥ መልስ አላገኙም:: « ...... ወይ ጉድ ? የዚህ ዓለም ሁኔታ የሚያስገርም ነው:: በግፍ ከተወሰደብን ከራሳችን መሬት ተቆርሶ ወደ ባሕር መተላለፊያ በር እንዲሰጠን ስናመለክት፣ መልሱ ወደፊት ይታሰብበታል ሆነ:: በዚህ አኳኋን የተወሰደብን መላው ግዛታችን ይመለስልን ብለን ጠይቀን ቢሆን ምን ልንባል ኖርዋል ? ...... » እያሉ፣ ተፈሪ መኰንን ውስጥ ውስጡን እየነደዱ ባዶ እጃቸውን ወደ አገራቸው ተመለሱ::

ለአሥራ ሶስት ዓመታት ኢትዮጵያን በሙሉ ሥልጣን ካስተዳደሩ በኋላ አልጋወራሽ ተፈሪ « ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገሥት » ተብለው ዘውድ ሲጭኑ፣ በያለበት የተፈጠሩባቸው ውስብስብ ችግሮች ወሰን የሌላቸው ሆኑ::

በአገር ውስጥ የየአውራጃው መሣፍንትና ባላባት ለጥ ስጥ ብለው አልተገዙላቸውም:: በመኳንንቱና በሀይማኖት መሪዎችም ሠፈር ኢትዮጵያን ለማሠልጠን በማለት፣ ከፈረንጆች ጋር የሚያደርጉት መቀራረብና ወዳጅነት አልተወደደላቸውም:: በአስተዳደሩም በኩል በየአውራጃው ያለውን የየመሣፍንቱን ሥልጣን እየገፈፉ አዲስ አበባ ላይ ለማከማቸት አስበዋል እየተባለ፣ በየዕለቱ የሚዶለትባቸውና የሚዘጋጅባቸው ሤራ ሠላም አልሰጣቸውም:: በውጭውም ዓለም በሙሶሊኒ ማሲንቆ የሚዘፈንባቸው ፕሮፓጋንዳ አድማጭ እየሳበ ሄደ:: « ..... የኃይለሥላሴ ኢትዮጵያ አንዲት ቅንጣት የመሻሻል እርምጃ አላደረገችም:: በፊውዳል ሥርዓት በአገሪቷ ላይ የተዘረጋው የመከራ ጥላ መታጠፍ አልጀመረም:: ዛሬም የሰው ልጅ ባርያ እየተባለ፣ እንደ ዕቃ የሚነገድበት አገር መሆኑ አልቀረም:: ይህችን አገር ከጭለማ ወደ ብርሃን የሚያሻግራት ያስፈልጋታል:: ... » እየተባለ፣ በመላ ኤውሮፓ አገሮች የፋሽስት ፕሮፓጋንዳ በሰፊው ተዛመተ:: በዚህ ሁሉ ሁኔታ፣ ንጉሠ ነገሥት ኃይለሥላሴ የኤርትራን ዶሴ ላልተወሰነ ጊዜ ወደ ጐን ትተው፣ መጀመሪያ የኢትዮጵያን ነፃነት ከኮሎኒያሊስት ቀንበር ለማዳን ከመታገል በስተቀር ሌላ ምርጫ አልነበራቸውም:: የኢትዮጵያን ነፃነት ጠብቆ ለማቆየት ያደረጉትም ጥረት፣ ከአምስት ዓመት በላይ ጊዜ ሊሰጣቸው አልቻለም:: « ..... የባሪያን ንግድ በአዋጅ ከልክያለሁ:: ለሥልጣኔ ዕድገት ዘመናዊ ትምህርት ቤቶች ከፍቼ ወጣቶቹን አስተምራለሁ:: በዴሞክራሲም ሥርዓት ስለማምን፣ ሕዝቡ በአስተዳደሩ ጉዳይ ተካፋይ ለመሆን እንዲችል ሕገ መንግሥት አዘጋጅቼ ሰጥቻለሁ:: የሕዝብ ምክር ቤት አቋቁሜ እንዲሠራበት አድርጌአለሁ:: ኢትዮጵያን በሥልጣኔ ለማራመድ የምደክምበትን ሁሉ በወሬ ከምትሰሙት መጥታችሁ እዩልኝ.. » እያሉ፣ የፋሽስትን ፕሮፓጋንዳ ለመከላከል ቢሞክሩም፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሚያዳምጣቸው አላገኙም:: ዘውድ በጫኑ በስድስተኛው ዓመት

ሙሶሊኒ ከኤርትራና ከሱማሌ ጦሩን እየነዳ ሕዝቡን በመርዝ ጋዝ እየጨረሰ፣ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛቴ ብሎ ያዘ። ቀዳማዊ ኃይለሥላሴም ስደተኛ ሆነው እንግሊዝ አገር ገቡ።

በሰኔ 1940 ዓ.ም ሙሶሊኒ ተንቀዥቅዦ በዓለም ጦርነት ውስጥ ከሂትለር ጋር በመሰለፍ እግሊዞችን መውጋት ሲጀምር፤ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት የኢትዮጵያን ነፃነት ለማስመለስና ጣልያንን ቀደም ሲል ከታወቁት ከቅኝ ግዛቶቹ ከኤርትራ፣ ከሱማሌና ከሊቢያ ለማባረር ወሰነ። ስደተኛው ንጉሠ ነገሥትም በየአውራጃው ያሉትን የኢትዮጵያን አርበኞች ለማስተባበርና የነፃነቱን ውጊያ ለማደራጀት ከእንግሊዝ አገር በፍጥነት ተነሥተው ሱዳን ገቡ። የታላቋ ብሪታንያም ባለሥልጣኖች የጦር ዝግጅታቸውን እያጠነከሩ፣ በንጉሠ ነገሥት ኃይለሥላሴ ስም የኢትዮጵያን፣ የኤርትራንና የሱማሌን ሕዝቦች ለውጊያው ለመቀስቀስ አዘጋጅተው በአውሮፕላን የበተኗቸው ልዩ ልዩ ጽሑፎች የሚከተሉት ነበሩ።

1 . ..... የአገሬን፣ እንዲሁም ከእንግዲህ ወዲያ ሕዝቦቻቸው በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሥር የሚኖሩትን የኤርትራንና የቤናዲርን (የጣሊያን ሱማሌ) ነፃነት ለማስመለስ መጥቻለሁ።

2...... ከመረብ ወዲያ ያላችሁ ሕዝቦች ሁሉ ከኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችሁ ጐን በመቆም በትግሉ ተባበሩ። የእናንተ ዕድል ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የተሳሰረ ነው። ..... »

እንግሊዞችም በራሳቸው ስም ለኤርትራ ሕዝብ በበተኑት ጽሑፍ ላይ ያሠፈሩት ቃል፣ « ...... ጣልያንን እየከዳችሁ ከታላቋ ብሪታንያ ጦር ጋር ብትሰለፉ፣ በመጨረሻው በሚገኘው ድል ተገቢ ዋጋችሁን ታገኛላችሁ። ..... <u>የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር አንድ መሆን ቢፈልግ፤ ወይም ራሱን ችሎ መተዳደርን ቢመርጥ፤ ፍላጐቱ እንደሚፈጸምለት እናረጋግጣለን።</u> ... » የሚል ነበር።

የኤርትራ የወደፊት ዕድል የሚወሰነው በሕዝቡ ምርጫ ነው የሚል ሀሳብ እንግሊዞች ቢበትኑም፤ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የመረብ ምላሽ ሕዝብ ኢትዮጵያዊነትን እንደሚመርጥ ስለሚተማመኑ ተስፋቸውን አላቀዘቀዙም። ይልቁንም ንጉሠ ነገሥቱ በድል አድራጊነት አዲስ አበባ በገቡ ማግሥት ከኤርትራ ሕዝብ እጅግ አብዛኛው የተካፈለበት « ኢትዮጵያ ወይም ሞት » የሚለው ያገር ፍቅር አንድነት ማህበር በመቋቋሙ፣ እንግሊዞች ለሚያምኑበት የሕዝብ ምርጫ ከዚህ የበለጠ ማስረጃ የት ይገኛል ? የሚል ተስፋ አድሮባቸው ነበር። ነገር ግን የታላቋ ብሪታንያ ባለሥልጣኖች እንኳንስ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል ለመርዳት ይቅርና፤ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥታቸውን በሙሉ ሥልጣን እንዲመሩ አልፈቀዱላቸውም። የቀረው ቢቀር፣ ንጉሠ ነገሥቱ የእንግሊዝን ባለሥልጣኖች ሳያማክሩና እነሱ ሳይስማሙበት የካቢኔ ሚኒስትሮችንና ዋና ዋና አገረ ገዥዎችን ለመሾም እንኳ አይችሉም ተባሉ። ይህ ሁሉ እንቅፋት ያላሰቡትና ያልጠበቁት ቢሆንባቸውም ተፈሪ መኰንን ተስፋ ቆርጠው መታየት አልፈለጉም። የዓለም ጦርነት ተፈጽሞ እነ ዊኒስተን ቸርችል ፋታ ሲያገኙ፤ የተደነቀሩት ችግሮች ሁሉ ይወገዳሉ ብለው በትዕግሥት ለመጠበቅ ሲያስቡ፣ አሁንም ባላሰቡት መንገድ ስለ ኤርትራ ጉዳይ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች አሥመራ ላይ የሰጡት መግለጫ ንጉሠ ነገሥቱን እጅግ የሚያሳዝን ሆነ።

« ...... ኤርትራን ለማስለቀቅ በተደረገው ውጊያ ሕዝቡ ጣልያንን ከድቶ ከእንግሊዝ ጦር ጋር እንዲሰለፍ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስም የተበተኑት ጽሑፎች፣ የጋራ ጠላትን ለማጥቃት የተወሰዱ እርምጃዎች እንጂ፣ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ኤርትራን ለኢትዮጵያ ለማስረከብ የሰጠው ቃል የለም:: ...... በሕግ ረገድ ዛሬም ቢሆን ኤርትራ የጣልያን ቅኝ ግዛት መሆንዋን የኢትዮጵያ መንግሥት አይስተውም:: ...... በ1896 ዓ.ም በንጉሠ ነገሥት ምኒልክና በጣልያን መንግሥት መካከል በተፈጸመው ውል፤ ኤርትራ የጣልያን ቅኝ ግዛት መሆንዋን ኢትዮጵያ እውቃለች:: ...... ከእንግዲህ ወዲህ የኤርትራም ሆነ የሞቃዲሾ ሱማሌ የወደፊት አስተዳደር ምን እንደሚሆን የሚታወቀው፣ ከዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ የአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች ተነጋግረው በሚሰጡት ውሳኔ ስለሆነ፤ እስከዚያው ድረስ በነዚሁ አገሮች ላይ የተቋቋመው የታላቋ ብሪታንያ ወታደራዊ አስተዳደር ይቀጥላል:: ..... » ሲሉ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች አቋማቸውን ገለጡ::

ይህ የእንግሊዞች መግለጫ የተዘጋጀው፣ በተንኮል ጥበብ የንጉሠ ነገሥቱን ሞራል ለመንካት መሆኑ ባይካድም፤ የተገለጸውን ሀሳብ ለመቃወምም ሆነ ለመጋተር ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት የሚያመች አልሆነም:: በመሠረቱ ዓለም በጦርነት እሳት በሚቃጠልበት ሰዓት ሠላም ሳይሰፍንና መንግሥታቶች ሳይረጋጉ፤ ኢትዮጵያዊት የነበረች ኤርትራ ወደ እናቷ እንድትመለስ ለምሥራቅ አፍሪካ ከተመደቡት የታላቋ ብሪታንያ የጦር ባለሥልጣኖች ጋር መከራከሩ፤ አስፈላጊ እንዳልሆነ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ግልጽ ሆኖ ታያቸው::

የፈረንጆቹ የ1942 ዓ.ም አዲሱ ዓመት ሲጀመር፣ ከኤርትራ ጉዳይ ይልቅ፤ በታላቋ ብሪታንያ እና በንጉሠ ነገሥቱ መካከል በሚደረገው የቃል ኪዳን ውል፣ የኢትዮጵያን ነፃነት ለማረጋገጥ መሟገቱ፣ ቅድሚያ የሚሰጠው ትልቅ ጉዳይ ሆኖ ተገኘ:: እንግሊዞች እንደፈለጋቸው ባዘጋጁት ውል፣ ከ1942 እስከ 1944 ዓ.ም ድረስ ለሁለት ዓመታት፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ካቢኔያቸው በታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ሥልጣን የታሰሩ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሆነ:: ድርጊቱ እጅግ ቢያሳዝናቸውም፤ ከብዙ ክርክርና ድርድር በኋላ፣ በውሉ ውስጥ « <u>ኢትዮጵያ</u> ነፃ መንግሥት » መሆኗን የሚያረጋግጥ አንድ አንቀጽ እንዲገባ በመደረጉ፣ ንጉሠ ነገሥቱ አንድ ዓይነት እርካታ አግኝተውበታል:: ውሉን በፈለገው ዓይነት አዘጋጅቶ በግዴታ ያስፈረማቸው የእንግሊዝ የምሥራቅ አፍሪካ የፖለቲካ ሹም ሰር ፊልፕስ ሚቼልስ (SIR PHILLIPS MITCHELS) ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ እንድትመለስ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ያላቸውን ጥ<u>ያቄ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት በቅን መንፈስ</u> ይመለከተዋል ብሎ፣ በፊርማው ሥነ ሥርዓት ላይ ስለገለጸላቸው፤ በዚህም በኩል መጠነኛ ደስታና እምነት ሳያድርባቸው አልቀረም::

በጠቅላላው፤ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኤርትራን ለማስመለስ የሚደረገው ጥረት ጊዜ እንደሚፈጅ ገና ከመነሻው ያውቃሉ ቢባልም፤ ከጣልያን መባረር በኋላ እንግሊዞች ብዙ ችግር እንደሚፈጥሩባቸው አልገመቱም ነበር:: የዓለም ጦርነት ተፈጽሞ ድል አድራጊዎቹ የአራቱ ኃያላን መሪዎች እስኪሰበሰቡ ድረስ፣ የኤርትራን ጥያቄ ማንሳት የለብዎትም ቢባሉም፤ ከ1942 ዓ.ም ጀምሮ፣ ተፈሪ መኰንን ኤርትራ ለኢትዮጵያ እንድትመለስ ያላቸውን ጽኑ ፍላጎት፤ አጋጣሚ ዕድል ባገኙ ቁጥር ለየመንግሥታቱ እንደራሴዎች ከማሳሰብ አላቋረጡም:: ለምሳሌ ያህል፤

1. በታላቋ ብሪታንያ እና በኢትዮጵያ መካከል የሚደረገውን ሁለተኛውን ስምምነት፣ (1944-1946) ለመፈራረም አዲስ አበባ መጥቶ ከሰነበተው፣ ከቸርችል ልዩ መልዕክተኛ ከሎርድ ደ-ላዋር (LORD DE LA WARR) ጋር ሲነጋገሩ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ከሁሉም ቅድሚያ በመስጠት አጥብቀው የጠየቁት፣ የኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ የእንግሊዝ መንግሥት እንዲደግፋቸው ነበር።

2. በየካቲት 1945 ዓ.ም በሲስ ካናል ላይ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት (F.D ROOSEVELT) ሲቀበላቸው፣ ንጉሠ ነገሥቱ ካመለከቷቸው ጠቅላላ ጉዳዮች መካከል አንዱ፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል፣ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት እንዲረዳቸው ያቀረቡት ጥያቄ ነበር።



*« ...... የሕይወታችንን መቆየት የምንመኘው በቅኝ ገዥዎች የተወሰዱብንን አገሮቻችንን ለማስመለስ ጊዜ እንድናገኝ ነው ...... »*

(ቀ.ኃ.ሥ መስከረም 1945)

# ክፍል ሁለት

## የኤርትራ ጉዳይ፣
## በአራቱ ኃያላን መንግሥታት ሸንጎ
## (ከመስከረም 1945 - 1948)

ገጽ


1. የፖትስዳም ውሳኔ እና የሎንዶን ጉባኤ፤ .......... 23
2. የፓሪስ ስብሰባ፤ .......... 32
3. የፓሪሱ የሠላም ጉባኤ፤ .......... 44
4. የጣልያን ይቅርታ፤ .......... 58
5. የግብፅ ጥያቄ፤ .......... 68
6. የሠላም ጉባኤው ፍጻሜ፤ .......... 70
7. የአራቱ ኃያላን መርማሪ ኮሚሽን በኤርትራ፤ .......... 74
8. የኤርትራ የፖለቲካ መሪዎች ከመርማሪው ኮሚሽን ጋር፤ .......... 80
9. ሐቁን የሸፈነ የምርመራ ውጤት፤ .......... 91

# የፖትስዳም ውሳኔ እና የሎንዶን ጉባኤ

ጀርመን ድል ሆና ከተያዘ በኋላ የአራቱ ኃያላን መንግሥታት መሪዎች፤ ሔንሪ ትሩማን የአሜሪካ ፕሬዚዳንት፣ ዊንስተን ቸርችል የታላቋ ብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ማርሻል ስታሊን የሶቪየት ሕብረት መሪ፣ ፖትስዳም (POTSDAM) በምትባል በጀርመን ግዛት ውስጥ ከበርሊን ደቡብ ምሥራቅ በምትገኝ አንድ ትንሽ ከተማ፣ ተሰብስበው ከወሰኗቸው ታላላቅ ጉዳዮች አንዱ፤ የሂትለር ግብረአበሮች ሆነው ጦርነቱ ውስጥ ከገቡት የፋሽስት አገሮች ጋር ስለሚደረጉት የእርቅ ስምምነቶች ዝግጅት ነበር።

የሂትለር ተከታዮች የሆኑት በመጀመሪያ ጣልያን፣ በሁለተኛ ደረጃ ሩማንያና ቡልጋሪያ፣ ሁንጋሪያንና ፊንላንድ በድምሩ አምስት ሲሆኑ፣ ከነዚህ አገሮች ጋር የሚደረገውን የሰላም ስምምነት ለማዘጋጀት የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲቋቋም፤ በነሐሴ 1945 ዓ.ም በፖትስዳም የተደረገው የመሪዎቹ ስብሰባ ወሰነ።

የፈረንሣይ ሬፑብሊክ ከኃያላኖቹ መንግሥታት ክለብ ውስጥ አራተኛዋ ሆና እንድትመደብ፣ በዊንስተን ቸርችል ከፍተኛ ጥረት በያልታ ኮንፈራንስ ጊዜ ቢፈቀድላትም፤ በአሁኑ በፖትስዳሙ ስብሰባ ላይ እንድትካፈል አልተደረገም። ፈረንሣይ፣ አራተኛዋ ታላቅ መንግሥት ተብላ ለመጀመሪያ ጊዜ ባንዲራዋን አውለብልባ ለመካፈል የበቃችው፤ በሎንዶን በተደረገው ስብሰባ ላይ ነው።

የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች፤ የእንግሊዙ ኧርነስት ቤቨን፣ (EARNEST BEVIN) የመስኮቡ ሞሎቶቭ (MOLTOV) የአሜሪካው ጀምስ በርንስ፣ (JAMES BYRNES) የፈረንሣዩ ዦርዥ ቢዶ፣ (GEORGE BIDAULT) የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ሊቢያ፣ ኤርትራና ሱማሌ የወደፊት ዕድላቸውን ለመወሰን መነጋገር የጀመሩት በመስከረም 1945 ዓ.ም በተደረገው በዚህ በሎንዶኑ ስብሰባ ላይ ነው።

የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ባቀረበው ሀሳብ፤ የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የበላይ ጠባቂነት ለአሥር ዓመታት በሞግዚት እንዲተዳደሩና ከዚያም በኋላ ነፃነታቸውን እንዲቀበሉ ያስፈልጋል አለ። አስተዳደሩ ምን ዓይነት መልክ እንደሚኖረው ሚስተር በርንስ (BYRNES) ሲያስረዳ፤ የአራቱ ኃያላን መንግሥታት ወኪሎች ባሉበት፣ ከሶስቱ ቅኝ አገሮች የሚመረጡ አንዳንድ የሕዝብ እንደራሴዎችና የቀድሞ ገዢያቸው ጣልያንም በአባልነት የሚሰየሙበት የመማክርት ኮሚቴ ተቋቁሞ፣ ለእያንዳንዱ አገር አንዳንድ ሞግዚት ይሾምለታል አለ። ጀምስ በርንስ (JAMES BYRNES) ይህንን ዕቅድ የመረጠበትን ምክንያት ሲገልጥ፣ የጣሊያን መንግሥት ቅኝ ግዛቶቹን እስከዛሬ ያስተዳደራቸው በመጨቆን ስለሆነ ራሳቸውን የማይችሉ ሆነዋል። ስለዚህ ሊቢያና ኤርትራ ለአሥር ዓመታት፣ ሱማሌ ላልተወሰነ ጊዜ፣ በሞግዚት ሥልጣን እየተዳደሩ ለነፃነት መደራጀት ያስፈልጋቸዋል። ከዚህም በቀር የአትላንቲክ ቻርት ፈራሚዎችና በጦርነቱ ጊዜ የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ሞስኮ ላይ ተስማምተው ባደረጉት ውሳኔ መሠረት፣ የጠላት ቅኝ ግዛቶች የነበሩት ሕዝቦች ከእንግዲህ ወዲህ ነፃነታቸውን የሚያገኙበትን መንገድ ማዘጋጀት ነው እንጂ፣ ከኮሎኒያሊስት እጅ ወጥተው ለሌሎች ገዥዎች እንዲዳረጉ አያስፈልግም ሲል የአሜሪካ የዲፕሎማሲ መሪ አስተያየቱን ሰጠ። የሚስተር በርንስ ማስጠንቀቂያ

በቀጥታ የሚመለከተው የታወቁትን ኮሎኒያሊስቶች እንግሊዝንና ፈረንሣይን ሳይሆን፣ ያለጥርጥር ሶቪየት ሕብረት በበኩሉ ከጣልያን ቅኝ ግዛቶች ውስጥ አንዱ ለእኔ በሞግዚትነት ይሰጠኝ ብሎ እንዳያስቸግር የተሰነዘረ ሳይሆን አልቀረም::

የፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዦርዥ ቢዶ (GEORGE BIDAULT) ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች የወደፊት አስተዳደር ከአሜሪካ የቀረበውን ሀሳብ የማይቀበል መሆኑን የዲስኩሩ መክፈቻ አድርጎት ነበር:: በዦርዥ ቢዶ አስተያየት፤ ጣልያን ሶስቱም ቅኝ ግዛቶቿ ሊመለሱላት ይገባል::

እነዚህን በጨለማ ዓለም ውስጥ የነበሩትን አገሮች አቅንቶ ለተሻለ ሕይወት ያበቃቸው ጣልያን ነው:: የጣልያን ሕዝብ በ1943 ዓ.ም የፋሽስትን ሥልጣን አውድሞ ከታላላቅ የቃል ኪዳን አገሮች ጦር ጋር በመሰለፍ፤ የዓለም ጠንቅ የሆኑትን ዲክታተሮች ለማጥፋት ያደረገውን አስተዋፅኦ መዘንጋት አይቻልም:: ስለዚህ፣ አዲሲቷ ሬፑብሊክ ጣልያን በታላቋ ብሪታንያ እጅ የተያዙባት ቅኝ ግዛቶቿ ሊቢያ፣ ኤርትራና ሱማሌ ተመልሰው እንዲሰጧት አጅግ ተገቢ መሆኑን ሙሴ ቢዶ በመንግሥቱና በፈረንሣይ ሕዝብ ስም ሆኖ አጠንክሮ አሳሰበ::

በዚህ ጉዳይ ላይ ከምዕራብውያን ታላላቅ መንግሥታት መካከል አሜሪካና ፈረንሣይ ፀየበኩላቸው የሚያስቡትን ሲናገሩ፤ ታላቋ ብሪታንያ አስተያየቷን ለፉጥና ማቅረብ አልፈለገችም:: የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ኧርነስት ቤቨን የስብሰባው ሊቀመንበር በመሆኑ ሌሎቹን እያናገረ፣ ለነዚህ ቅኝ ግዛቶች የወደፊት አስተዳደር ምን መፍትሔ እንደሚሻል የራሱን ዕቅድ ለጊዜው ሸፍኖ አቆይቶታል:: ይሁን እንጂ የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ተመልሰው ለጣልያን እንዲሰጡ ታላቋ ብሪታንያ እንደማትደግፍ የታወቀ ነበር::

የሶቪየት ሕብረት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሙሴ ሞሎቶቭ (MOLOTOV) ስለ ጣልያን ኮሎኒዎች ጉዳይ አሜሪካዊው ጀምስ በርንስ እንደተናገረው፣ ጣልያኖች በቅኝ ግዛቶቻቸው ላይ የተጠቀሙት ሌላ አገር ለመውጋት የጦር ማስፈሪያና ማሸጋገሪያ በማድረግ ነው እንጂ ለሕዝቡ መሻሻል የሠሩት አንዳች ነገር አለመኖሩን ካስረዳ በኋላ፣ « <u>ጣልያን ከቅኝ ግዛቶቿ በመነቀሏ የሶቪየት ሕብረት ሕዝብ ይደሰታል</u> » አለ:: ለእነዚህ ቅኝ አገሮች የወደፊት መፍትሔ ሲያቀርብ፤ በሊቢያ ውስጥ ለትሪፖሊታንያ እና ለሲረናይከ አውራጃዎች በምስራቅ አፍሪካ ለኤርትራና ለሱማሌ አንዳንድ የሞግዚት አስተዳዳሪ ለተወሰነ ጊዜ እንዲመደብላቸው አስፈላጊነቱን ከገለጸ በኋላ፣ የሶቪየት መንግሥት ከሊቢያ አውራጃዎች ውስጥ ትሪፖሊታንያን በሞግዚትነት እንዲሰጠው ጠየቀ:: የሙሴ ሞሎቶቭ ጥያቄ እንደዚህ በቶሎ ይቀርባል ተብሎ ያልተጠበቀ በመሆኑ፤ ሶስቱ ምዕራብውያኖች (እንግሊዝ፣ አሜሪካ ፈረንሣይ ) መቃወማቸውን ለመግለጽ ጥቂት ማሰብ አስፈልጓቸው ነበር::

ትሪፖሊታንያ፣ ሲረናይከ፣ ፈዛን፣ የተባሉት የሊቢያ ክፍለ ሀገሮች፣ እንግሊዞች በጦርነቱ ብዓት እንደአጠኗቸው፣ በተለይ ሁለቱ አውራጃዎች ሲረናይከና ትሪፖሊታንያ አማካይ የሆኑ የስትራቴጂ ቦታዎች መሆናቸውን ተገንዝበዋል::



ላቶ አክሊሉ ሀብተወልድ

*« ...... ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ለመመለስ ቆርጠን ለምንደክምበት ሥራ፥ ይኸው ዕምነታችንን በአንተ ላይ ጥለን ዋና መላክተኛችን አድርገንሀል ...... »*

ቀ.ኃ.ሥ

ሐምሌ 1946 ዓ.ም
(ፎቶ U.N)

ታላቋ ብሪታንያ እና ዩናይትድ ስቴትስ ዓለምን ለመግዛት የተነሳውን የሂትለርን ጦር የደመሰሱት ከመስኮብ ጋር ቢሆንም፣ በእንግሊዞች የሩቅ ግምት የማርሻል እስታሊን አመራርና የማርክሲዝም ግስጋሴ የሚያሳስብ እንጂ የሚያዝናና ሆኖ አልታያቸውም። በጦር መሣሪያና ድርጅት በየጊዜው እያደገ ከሚጓዘው ከሶቪየት መንግሥት ጋር ምዕራባውያኖች አንድ ቀን ጦርነት ለመግጠም ቢገደዱ ፣ በሊቢያ ካሉት አውራጃዎች ሲረናይክ እና ትራፖሊታንያ፣ ለአየርና ለባሕር የጦር ኃይሎች ማከማቻና ማንቀሳቀሻ ምቹ ሥፍራዎች መሆናቸው ታምኖበታል።

መስኮብ ትሪፖሊታንያን በሞግዚትነት ለማስተዳደር ተሽቀዳድሞ የጠየቀው፣ ምዕራባውያኖች የሚያስቡትን የቅርብና የሩቅ ጥቅም ለማደናቀፍና እኔም አለሁ ብሎ ለመጋተር መሆኑ በግልጽ ታወቀ። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ገና ስብሰባው ሲጀመር የጣልያን ቅኝ ግዛቶች በተባበሩት መንግሥታት የበላይነት፣ በአራቱ ኃያላኖች መማክርት ኮሚቴ ለተወሰነ ጊዜ ቢተዳደሩ ይሻላል ብሎ ያቀረበው ሀሳብ፣ በተለይ የሶቪየት መንግሥት አገሮቹን እየመረጥን እኩል እንከፋፈላቸው የሚል ችግር እንዳይፈጥር አስቀድሞ መንገዱን ለመዝጋት ነበር።

የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የስብሰባው ሊቀመንበር በመሆኑ፣ በሌሎቹ ምዕራባውያን ጓደኞቹ ስም ሆኖ ትራፖሊታንያን በሞግዚትነት ለማስተዳደር፣ ከሶቪየት ሕብረት የቀረበው ጥያቄ የማይቻል መሆኑን ተናገረ። ሚስተር ቤቨን ለሙሴ ሞሎቶቭ ምክንያቱን ሲያስረዳ፣ የፋሽስትን ይዞታ ከአፍሪካ ለመደምሰስ በተደረገው ጦርነት የሶቪየት ሕብረት ተካፋይ ባለመሆኑ ነው ብሏል። የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቀራረቡን ሳያለሰልስ የደረቀ እምቢታ ለመስኮብ የወረወረው፣ ከስምንት ወራቶች በፊት በያልታ ስብሰባ ላይ የተደረገው ስህተት እንዲደገም ስለአልፈለገ ነው። በየካቲት 1945 ዓ.ም በያልታ በተደረገው የሶስቱ ኃያላኖች (አሜሪካ፣ እንግሊዝ መስኮብ) ስብሰባ ላይ፣ ዓለምን ተከፋፍሎ ለመቆጣጠር በተነደፈው ካርታ፣ የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት በደግነት ለስታሊን ያንን ሁሉ ስጦታ ባያሸክመው ኖሮ፣ ዛሬ የሶቪየት መንግሥት ከምዕራባውያኖች ጋር እኩል ተወዳዳሪ ነኝ ብሎ አይጠግብም ነበር። አሁንም ሙሴ ሞሎቶቭ በታውን እየለቀቀ ድንበር እያለፈ ለማስቸገር ሲሞክር በቶሎ ካልታገደ፣ ማስታመሙ ጥቅም የለውም ብሎ የታላቋ ብሪታንያ የሠራተኞች ወገን የፖለቲካ መሪ የሆነው ኧርነስት ቤቨን ያምናል።

## የኢትዮጵያና የጣልያን አቤቱታ

የሎንዶኑ ስብሰባ ከመጀመሩ በፊት የጣልያን መንግሥት የቅኝ ግዛቶቹን ጉዳይ ስብሰባው ላይ ተገኝቼ ለማስረዳት ይፈቀድልኝ ሲል እንደአመለከተው ሁሉ፣ ኢትዮጵያም በበኩልዋ መልዕክተኛዋን ልካ «የጥንት ግዛቶቼ ኤርትራና ሱማሌ እንዲመለሱልኝ» በማለት የምታቀርበውን ጥያቄ ሎንዶን ስብሰባ ላይ ተገኝታ ለማስረዳት እንድትችል በወግ አመልክታ ነበር። ነገር ግን፣ የአራቱ ኃያላኖች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች፣ ከሁለቱ ባለጋራዎች ከሆኑት አገሮች የቀረበላቸውን ጥያቄ ከመረመሩ በኋላ፣ ጣልያን መልዕክተኛዋን ለሎንዶኑ ስብሰባ እንድትልክ ሲፈቅዱ፣ ኢትዮጵያ ሀሳቧን በጽሑፍ ማመልከቻ መግለጽ እንጂ ሎንዶን መገኘት የለባትም ብለው አድሎነቱ ግልጽ የሆነ አሳዛኝ ውሳኔ አደረጉ።

በዚህ ሎንዶን ላይ በሚደረገው የአራቱ ኃያላን መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ፣ የሮማ መንግሥት መልዕክተኛ ልክ ሀሳቡን እንዲገልጽ ሲፈቀድለት፣ ኢትዮጵያ በመከልከሏ፣ በንጉሡ ነገሥቱና በመንግሥታቸው ላይ የደረሰው ብስጭት መጠን አልነበረውም:: በኢትዮጵያ ላይ የተደረገውን አሳዛኝ ውሳኔ ለማስለወጥ ከአዲስ አበባ አንዳንድ እርምጃዎች ተወሰዱ::

1. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለአሜሪካ ፕሬዚዳንት ለሚስተር ትሩማንና ለአዲሱ የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስትር ለሚስተር ክሊመንት አትሊ (CLEMENT ATLEE) ኢትዮጵያ በለንደኑ ስብሰባ ላይ ተገኝታ አስተያየቷን ለመግለጽ እንድትችል አስቸኳይ መልዕክት ላኩ::

2. በአዲስ አበባ ያሉት የውጭ አገር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ኀላፊዎች ልዑል ቤተመንግሥት ተጠርተው፣ የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በወሰዱት እርምጃ ኢትዮጵያ ምን ያህል እንዳዘነች ለየመንግሥታቸው እንዲያስታውቁ ተጠየቁ::

3. በሎንዶን የጃንሆይ ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ብላታ አየለ ገብሬ እና፣ በዋሽንግተን የኢትዮጵያ ጉዳይ ፈጻሚ አቶ ጌታሁን ተሰማ፣ ለየተመደቡበት አገር መንግሥት የኢትዮጵያን ቅሬታ እንዲገልጹ ታዘዙ::

4. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለሮይተር የዓለም ዜና ማሰራጫ ድርጅት ኢንተርቪው በመስጠት፣ የፋሽስት የግፍ ጥቃት በመጀመሪያ የደረሰባት ኢትዮጵያ፣ ከጣልያን ጋር በሚደረገው የዕርቅ ድርድር፣ በተለይ ቅኝ ግዛቶቹን በሚመለከተው ጉዳይ፣ በሎንዶን ስብሰባ ተገኝታ ሀሳቧን ማቅረብ የሚገባት መሆኑን አስረዱ:: ንጉሠ ነገሥቱ አስተያየታቸውን በመቀጠል፣ የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ለዓለም ሠላምና ደህንነት የሚያደርጉት ጥረት ፍሬ ሊሰጥ የሚችለው፣ እድሎ በሌለበትና ሚዛኑ በተጠበቀ ፍርድ ላይ ተመሥርተው ሲሠሩ ብቻ ነው በማለት አስጠነቀቁ::

5. በአዲስ አበባ የሚኖሩት የኤርትራ ተወላጆች ከፍ ያለ ሠላማዊ ሠልፍ በማድረግ፣ ለአራቱ ኃያላን መንግሥታት የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች « ከእናት አገራችን ከኢትዮጵያ ጋር እንድንቀላቀል ፍርድ ይሰጠን » ሲሉ አመለከቱ:: የሠላማዊ ሠልፉን የመሩት በአዲስ አበባ የኤርትራና የኢትዮጵያ አንድነት ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ገብረመስቀል ሀብተማርያም በዚያን ጊዜ የፖስታ ሚኒስቴር ዋና ዲሬክተር ነበሩ:: ለአራቱ ኃያላን መንግሥታት ወኪሎች በሠላማዊ ሰልፈኞቹ ስም አቶ ገብረመስቀል በሰጡት መግለጫ « ...... <u>በኮሎኒያሊስቱ ጣልያን የጦር ኃይል ከአገራችን ተገንጥለን መራራውን የቅኝ አስተዳደር ስንቀበል የኖርን ሕዝቦች ስቃያችን ተወግዶ ከእናት አገራችን ከኢትዮጵያ ጋር ለመዋሀድ እንድንችል ፍርድ</u> እንጠይቃለን ...... » የሚል ነው::

የአራቱ ኃያላን መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ የሚካሔደው በሎንዶን መሆኑ ስለታወቀ፣ ከዚህም በላይ ኤርትራ ከፋሽስት እጅ

ወጥታ የምትተዳደረው በታላቋ ብሪታንያ ወታደራዊ አስተዳደር ስለሆነ፣ ሠላማዊ ሠልፉ የተጀመረው በእንግሊዝ ሌጋሲዮን ነበር። ሠልፈኞቹ ስሜታቸውን አጋግለው እየተርመሰመሱ ወደ ሌጋሲዮኑ ሲገቡ፣ በቀጫጭኖቹ መንገዶች ግራና ቀኝ የበቀሉትን ሳሮች ስለረጋገጧቸው፣ የእንግሊዙ እንደራሴ ሚስተር ሮበርት ሀው (ROBERT HOWE) በጣም ተበሳጭቶ የአፄ ገብረመስቀልን ዲስኩር ለማዳመጥም ሆነ ለመቀበል እምቢ እስከ ማለት ደርሶ ነበር። ነገር ግን ገብረመስቀል ያሳዩት ቆራጥነትና የሕዝቡም የጋለ መንፈስ ቀላል ሆኖ ስለአልተገመተ፣ በመጨረሻው መግባባት ተፈጥሮ የሕዝቡ ማመልከቻ በሠጣ እንዲቀርብና፣ ሠልፈኞቹም በሥርዓት ከሌጋሲዮኑ እንዲወጡ ተደረገ። በሌሎቹ፣ በመስኮብ፣ በፈረንሣይና በአሜሪካ ሌጋሲዮኖች አንዳችም ችግር ሳይፈጠር፣ ሳር ሳይረገጥ አበባም ሳይቀጠፍ፣ የየመንግሥታቱ እንደራሴዎቹም የሕዝቡን ማመልከቻ በሥርዓት ተቀብለው ሠልፈኞቹም በሠላም ተበታትነዋል።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና መንግሥታቸው በዚህ አኳኋን የኢትዮጵያን ስሜት ዓለም እንዲያውቅላቸው በየመልኩ ጥረት ቢያደርጉም፣ የሚሰማቸው አላገኙም። የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ስሞታ ከየአቅጣጫው ቢጎርፍላቸውም፣ ጣልያን መልክተኛዋን ለንደን ልካ እንድታስረዳ፣ ኢትዮጵያ በጽሑፍ ጥያቄዋን እንድታቀርብ ከሰጡት ውሳኔ አንኳኳቅም አሉ። ፍርድ ለሁሉም እኩል መሆን አለበት ብለው የሚቆሙ ቢሆኑ ኖሮ፣ የአጥቂውን ዲስኩር ለማዳመጥ ሲወስኑ፣ የተጠቂውን አቤቱታ በጆሮ መስማት አያስፈልግም አይሉም ነበር። መቼውንም ቢሆን የፖለቲካ ብየኔ በጥቅም ላይ የተመሠረተ ስለሆነ፣ ከትክክለኛ ሚዛንና ከእውነተኛ አቋም እጅግ እንደሚርቅ ለዚህ ዓለም አዲስ ነገር አይደለም።

ለኮሎኒያሊስቱ ጣልያን ከተሰጠው ዕድል ሌላ፣ ኢትዮጵያን እጅግ አድርጉ ያስገረማት፣ የትሪየስቴ (TRIESTE) ግዛት ከጣልያን ተነጥቆ እንዲሰጣት፣ የማርሻል ቲቶ ዩጎዝላቪያ ያላትን ጥያቄ በዚሁ በለንደኑ ስብሰባ ቀርባ እንድትገልጥ ጥሪ የተደረገላት መሆኑ ነው። በአራቱ ኃያላን መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚፈጸመው ሚዛን የሌለው ፍርድ፣ አንድ ቀን የዓለም ታሪክ የሚታዘበው እንደሚሆን ተስፋ በማድረግ፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያ፣ የለንደን ዳኞች የወሰኑትን ተቀብላ በኮሎኒያሊስት ጣልያን የተወሰዱብኝ የኤርትራና የሱማሌ ግዛቶቼ ሊመለሱልኝ ይገባል ስትል ማመልከቻዋን አቀረበች። « ..... ካለፉት ሃምሣ ዓመታት ጀምሮ ጣልያን በጦር ኃይል ከኢትዮጵያ ገንጥሎ የወሰዳቸው የኤርትራና የሱማሌ ሕዝቦች፣ ዝቅተኛ ዘር እየተባሉ ሰብዓዊ ክብራቸውን ገፍፎ በሥቃይ ያስተዳደራቸውና ድህነት ላይ የጣላቸው በመሆናቸው፣ የወደፊት ዕድላቸውን ለማሻሻልና መብታቸውን ለማስከበር ከወንድሞቻቸው ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር ከመዋሀድ በስተቀር ሌላ መፍትሔ አይኖርም ...» ስትል ኢትዮጵያ አስተያየቷን በሰፊው ገለጸች። በተለይ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ከክርስቶስ ልደት ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት ጀምሮ፣ በፍጹም አንድነት የኖሩ፣ አንድ ዓይነት ዘርና አንድ ዓይነት ባሕል ያላቸው በመሆናቸው፣ ሁለቱ ሕዝቦች ተነጣጥለው ሊኖሩ አለመቻላቸውን በኢትዮጵያ ማመልከቻ በሰፊው ተብራርቶ ቀርቧል። እንደተጠበቀው የጣልያን



« ...... አዲሲቷ ጣልያን የቀድሞ ቅኝ ግዛቶቿ ኤርትራ፡ ሊቢያና ሱማሌ እንዲመለሱላት፡ የፈረንሣይ መንግሥት ይጠይቃል ....... »

ዦርዥ ቢዶ የፈረንሣይ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር
መስከረም 1945
(ፎቶ U.N)

መንግሥት መልዕክተኛ በተደረገለት ጥሪ መሠረት በአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ ተገኝቶ፣ በ1885 እና በ1889 ዓ.ም ኤርትራንና ሱማሌን፣ በ1911 ዓ.ም ሊቢያን፣ ከያዘበት ዘመን ጀምሮ እነዚህን ምድረ በዳ እና በረሃማ የነበሩትን አገሮች አቅንቶ፣ የሰው ልጅ ሕይወት መኖሪያ ለማድረግ በጣልያኖች መስዋዕትነት የተገኘውን ውጤት በሰፊው አስረዳ:: ጣልያን እነዚህን ሶስት አገሮች በተለያዩ ጊዜያቶች ቅኝ አገሮቹ አድርጎ የያዛቸው፣ ከማንም መንግሥት ላይ ነጥቆ ወይም ተዋግቶ አለመሆኑን ከተናገረ በኋላ፣ ኤርትራና ሱማሌ ከግዛቶቹ ተገንጥለው የተወሰዱ ናቸው በማለት፣ ኢትዮጵያ የምታቀርበው ጥያቄ መሠረት የሌለው መሆኑን አረጋግጣለሁ አለ:: በሮማ መንግሥት አስተያየት፣ በጣልያን የተፈጠረው የኤርትራ ግዛትና ሕዝቡ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ኖሮት አያውቅም:: የኤርትራ ሕዝብ በታሪኩና በዘሩ፣ በቋንቋውና በባሕሉ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር የሚመሳሰል ወይም የሚቀራረብ መልክ ጨርሶ የለውም:: የሱማሌ ግዛት ደግሞ እንኳንስ የኢትዮጵያ የነበረ ነው ሊባል ይቅርና፣ ይህ በረሃማ አገር በሕንድ ውቅያኖስ አካባቢ መኖሩን እንኳን ኢትዮጵያ የሰማችው፣ ከጣልያን ይዞታ በኋላ ስለሆነ፣ የተለየ ማብራሪያ ማቅረብ አያስፈልግም:: በማለት የጣልያን መልዕክተኛ የተራቀቀና በታሪክ ቅጥፈት የተሞላ ማመልከቻውን አቀረበ::

ከጣልያን ዲስኩር በኋላ፣ ለስብሰባው የቀረበው የኢትዮጵያ ማመልከቻ ነበር:: ኤርትራና ሱማሌ እንዲመለሱላት በሰፊው የገለጸችውን የታሪክ፣ የዘርና የባሕል ግንኙነት ሳያነቡ ወይም ሳይመለከቱ፣ በደፈናው የኢትዮጵያ ጥያቄ አግባብ ስለሌለው ከአጀንዳው መሰረዝ አለበት ሲሉ የፈረንሣይ፣ የመስኮብና የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ውሳኔ አቀረቡ:: ነገር ግን የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የኤርትራ ሕይወት በብዙ ረገድ ከኢትዮጵያ ጋር የተያያዘ ስለሆነ፣ ጉዳዩ በጥንቃቄ ተጠንቶ ተገቢው ውሳኔ የሚሰጠው ነው በማለት ስለተከራከረ፣ የኢትዮጵያ ማመልከቻ አጀንዳው ላይ እንዲቆይ ተደረገ::

ኧርነስት ቤቨን በኤርትራ በኩል ኢትዮጵያን የደገፈ ቢሆንም በሱማሌ ጉዳይ የሚጭረው እሣት ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ትልቅ የራስ ምታት ነበር:: የቤቨን ፕላን፣ ታላቋ ሱማሌን ለመፍጠር፣ በጣልያን በእንግሊዝና በፈረንሣይ ከተያዙት የሱማሌ ግዛቶች ጋር፣ ከኢትዮጵያ ሰፊውን የኦጋዴንን አውራጃ የሚጨምር ነው:: ከኢትዮጵያ ጋር በታሪክ፣ በዘርና በባሕል የሚመሳሰል መልክ ያላት ኤርትራ ነች እንጂ፣ በደቡብ በኩል ያለው የሱማሌ ነገድ አይደለም ብለው፣ እንግሊዞች ያምናሉ:: በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ኤርትራን ካገኘች ለታላቋ ሱማሌ ዕቅድ ኦጋዴንን ለመልቀቅ እንደማታስቸግር የቤቨን ኤክስፐርቶች ሙሉ ተስፋ አድርገዋል:: ሆኖም በዚህ በሎንዶኑ ስብሰባ ላይ ትልቅ ሱማሌ ፈጥሮ በታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ሞግዚትነት እንዲተዳደር ለማድረግ ውስጥ ውስጡን ሲጐነጐን የሰነበተው የቤቨን ፕላን በይፋ አልተገለጠም:: ከአሜሪካ ከፈረንሣይና ከመስኮብ የተሰነዘሩት መፍትሔዎች እጅግ የተለያዩና ሊቀራረቡም ያልቻሉ በመሆናቸው፣ በስምምነት ከአንድ ውሳኔ ላይ መድረስ አልቻሉም:: የሁለተኛው የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ ከሰባት ወራት በኋላ በፓሪስ ስለሚደረግ፣ እስከዚያ ባለው ጊዜ ምክትል ሚኒስትሮቻቸው የእነዚህን ቅኝ ግዛቶች ዶሴ በሰፊው እንዲያጠኑና፣ ለሚቀጥለው ስብሰባ አንድ ዓይነት የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርቡላቸው ተስማምተው የሎንዶኑ ጉባኤ ተፈጸመ::



« ...... የኤርትራ ሕይወት ከኢትዮጵያ ጋር የተያያዘ ስለሆነ፣ ጉዳዩ በጥንቃቄ መጠናት አለበት ...... »

እርነስት ቤቨን   የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር
(ሎንዶን መስከረም 1945)

# የፓሪስ ስብሰባ


(ከሚያዝያ እስከ ሐምሌ 1946 ዓ.ም)

በመስከረም 1945 ዓ.ም የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በሎንዶን ተሰብስበው በጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ሳይስማሙ እንደተለያዩት ሁሉ፣ ምክትሎቻቸውም ለስድስት ወራት መፍትሔ ፍለጋ ሲፋጁ ከርመው፣ ለፓሪሱ ቀጠሮ « አራቱ ታላላቆች » የሚግባቡበትን መንገድ ማስናዳት አልቻሉም።

አራቱ ኃያላኖች ከጣልያን ጋር የሚፈረመውን የዕርቅ ውል አዘጋጅተው በሐምሌ ወር 1946 ዓ.ም በፈረንሣይ ዋና ከተማ ለሚደረገው የሠላም ጉባኤ ማቅረብ ስለአለባቸው፣ የቅኝ ግዛቶቹ ጉዳይ በቅድሚያ ውሳኔ ማግኘት ነበረበት። በሚያዝያ ወር መጨረሻ ላይ መልካምና ውብ በሆነው የፀደይ አየር፣ በፓሪስ ከተማ እየተደሰቱ፣ የአራቱ ታላላቅ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባቸውን ሲጀምሩ፣ ከስምንት ወራት በፊት በመስከረም 1945 ዓ.ም ሎንዶን ላይ ከነበራቸው የተለያየ አቋም ጋር ሲመዘን፣ የተቀራረቡበት መንገድ ሊታይ አልቻለም።

<u>አሜሪካኖች</u> ሶስቱም የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች በጋራ ሞግዚትነት እንዲተዳደሩ ተደርጎ፣ ሊቢያና ኤርትራ ከአሥር ዓመት በኋላ ነፃነታቸውን ሲቀበሉ፣ ሱማሌ ላልተወሰነ ጊዜ ትቆያለች የሚሉትን ሀሣብ አልለቀቁም። <u>ፈረንሣይ፣</u> የጣልያን ኮሎኒዎች በሙሉ ለጣልያን መመለስ አለባቸው የሚለውን ሙግቷን አልተወችም። <u>መሰኮብ</u> ለቅኝ ግዛቶቹ ለተወሰነ ዘመን አንዳንድ የሞግዚት አስተዳደሪ መመደብ አስፈላጊ መሆኑን እየገለጸ፣ ከሊቢያ አውራጃዎች ትሪፖሊታንያ ለሶቪየት ሕብረት በአደራ እንድትሰጥ ያቀረበውን ጥያቄ አልሰረዘም። በዚህ አኳኋን ሁሉም ከየአቋማቸው እልፍ አንልም ብለው የሚጋተሩ ከሆነ መጨረሻው የት ላይ ነው ?

አሜሪካዊው ጀምስ በርንስ እና (JAMES BYRNES) መስኮቡ ሞሎቶቭ (MOLOTOV) ከዚህ ችግር እንደ የመውጫ ዘዴ ለማግኘት እራት እየተገባበዙ በሚወያዩበት ጊዜ፣ በሰሜን ጣልያን የሚገኘው ትሪየስቴ (TRIESTE) የተባለው አውራጃ እንደ ጦር ካሣ ተቆጥሮ ለዩጐዝላቪያ እንዲሰጥ ምዕራባውያኖች ከተስማሙ፣ ትሪፖሊታንያን ካልሰጣችሁን ብለን አናስቸግራችሁም የሚል ሀሳብ ከሶቪየት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቀረበ። ያቺ ትሪየስቴ የምትባል የጣልያን ግዛት ታሪኳ እጅግ የተወሳሰበ ነው። በጥንታዊው ዘመን የሮማውያን ቅኝ እንደነበረች ይነገራል። ከዚያም ወዲህ ከአሥራ አራተኛው እስከ አሥራ ዘጠነኛው መቶኛ ዓመት መጀመሪያ ድረስ የጀርመን የሀብስበርግ ዳይናስቲ (HABSBOURG OF DYNASTY) የባሕር በር ሆና ከኖረች በኋላ፣ ከ1814 እስከ 1918 ዓ.ም ድረስ የአስትሪያ ሀንጋሪያ ኢምፓየር (AUSTRO UNGARIAN EMPIRE) ግዛት ሆነች። የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት ከተፈጸመ በኋላ በ1919 ዓ.ም፣ ጀርመንና አስትሪያን ድል ያደረጉት መንግሥታቶች ( ፈረንሣይ፣ እንግሊዝ አሜሪካ ) የአውሮፓን የግዛት ካርታ ሲያስተካክሉ፣ ጣልያን በጦርነቱ ላደረገችው ተሳትፎ መካሻ እንዲሆን ይቺን የትሪየስቴ አውራጃ ከሰሜን ግዛቷ ጋር አቀላቅለው መረቁላት። በ 1945 ዓ.ም ደግሞ ዩጐዝላቪያ « ትሪየስቴ » የኔ መሆን አለባት



የስታሊን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሚስተር ሞሎቶቭ
(ሙሴ ኒየት - አቶ እንቢ)

1. *« ..... የቀድሞዎቹን የጣልያን ኮሎኒዎች እኛ አራቱ ኃያላኖች ተከፋፍለን እናስተዳድራቸው ...... » ሎንዶን (1945)*

2. *« ..... የቀድሞዎቹ የጣልያን ኮሎኒዎች፣ ለባለቤቱ ለጣልያን መመለስ አለባቸው:: ...... » ፓሪስ (1946)*

3. *« ...... የቀድሞዎቹ የጣልያን ኮሎኒዎች በU.N ሞግዚትነት መስኮብ አባል በሆነበት ኮሚቴ ይተዳደሩ ...... » ኒውዮርክ (1949)*

4. *ለኢትዮጵያ የአሰብን ወደብ ማግኘት ብቻ ይበቃታል ....... » (1950)*

(ፎቶ U.N)

ብላ በጦር ኃይል ለመውሰድ ከመሞከሯም በላይ፣ ከጦርነቱም ፍጻሜ በኋላ በሶቪየት ሕብረት እየተረዳች ይህችን አውራጃ ከግዛቷ ጋር ለማቀላቀል ብዙ ታግላ አልተሳካላትም። አሁን ደግሞ፤ መስኮብ ትሪፖሊታንያን ለማስተዳደር ካልሰጣችሁኝ ብሎ ከደነቀረው ችግር ለመገላገል ብለው፣ ምዕራባውያኖች ትሪየስቴን ለዩጐዝላቪያ ለመስጠት አይፈልጉም።

የመስኮብ ምኞት በየጊዜው እየጨመረና ወሰኑን እየጣሰ በመሄዱ የሚበላጨው፤ የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፤ የሞሎቶቭን ሀሳብ ለማደናቀፍ የሚከተሉትን ሶስት ሀሳቦች ደረደረ።

1. የትሪፖሊታንያ እና የሲረናይከ አውራጃዎች ለየብቻቸው ነፃ መንግሥት ሆነው እንዲቋቋሙ፤

2. በኤርትራ ጉዳይ ኢትዮጵያ ያቀረበችውን የይገባኛል ጥያቄ ልዩ ኮሚቴ ተቋቁሞ እንዲያጠናው፤

3. በያለበት የተበታተኑትን የሱማሌን ሕዝቦች በአንድነት አሰባስቦ ታላቋ ሱማሌን ለመፍጠር የሚያስፈልገው ጥናት እንዲደረግ፤

ሚስተር ቤቨን እነዚህን ሶስት ሀሳቦች ሲተነትን በመስኮብና በፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ላይ የሚታየው ንዴት እጅግ የጋለ ነበር። ሙሴ ሞሎቶቭ ወዲያውኑ ተነሥቶ በሰጠው መልስ « ...... የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ፍላጐት በማንኛውም መልክ የቀድሞዎቹን የጣልያን ቅኝ ግዛቶች አጠቃልሎ በእጁ ለማስገባት ብቻ ሳይሆን፣ በተጨማሪም ከኢትዮጵያ የኦጋዴንን አውራጃ ቆርጦ ለመውሰድ ማቀዱን በግልጽ ያስረዳል ..... » ሲል እያፌዘ ተናገረ። የፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም በበኩሉ ምንም እንኳን እንደ ሙሴ ሞሎቶቭ በእሽሙር መራቀቅ ባይሆንለትም፤ የቤቨን ሀሳብ መዘዙ ብዙ ነው በማለት አጠንክሮ ተቃወመ። ዦርዥ ቢዶ (GEORGE BIDAULT) በሊቢያ ሥፈር ነፃነት የሚባል ፕላን መስማት አይፈልግም። ታላቋ ሱማሌ የሚባለውም ሀሳብ፣ ጂቡቲን የሚጨምር በመሆኑ አይቀበልም። በጠቅላላው፣ የቤቨን ዕቅድ ለታላቋ ብሪታንያ ጥቅም ብቻ ታስቦ የተዘጋጀ ነው በማለት፣ ሁለቱ ኃያላኖች መስኮብና ፈረንሣይ አሻፈረን ስላሉ የቀረበው ሀሳብ ንግግር ሳይደረግበት ቀረ።

## የሞሎቶቭ ኮክቴል (COCKTAIL MOLOTOV)

በጠባዩና በሀሳቡ ጠማማነት እጅግ የታወቀው፣ ቅጽል ስሙ ሙሴ ኒየት (በመስኮብኛ ቋንቋ እቶ እንቢ) የሆነው ቪአቸስላቭ ሚካኤሎቪች ስክሪአቢን ሞሎቶቭ (VIATCHESLAV MIKHAILOVITCH SKRIABINE MOLOTOV) የሶቪየት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ፍቱን መፍትሔ ነው ብሎ፣ አንድ ያልተጠበቀ ልዩ ሀሳብ ይዞ፣ ግንቦት 10 ቀን 1946 ዓ.ም እኩለ ቀን ላይ ቀረበ። « ...... ሶስቱም አገሮች፣ ሊቢያ፣ ኤርትራና ሱማሌ፣ ለአሥር ዓመታት በጣልያን ሞግዚትነት ተዳድረው፤ ከዚያ በኋላ ነፃነታቸውን ሊቀበሉ ይችላሉ ...... » አለ።

ከስምንት ወራት በፊት በሎንዶኑ ስብሰባ ላይ ኮሎኒያኒስት ጣልያን በፈጸመችው በደል ከቅኝ ግዛቶቿ ላይ በፍጹም መነቀል ይገባታል ብሎ የፈረደ

ሰው፡ በድንገት ተገልብጦ የጣልያን ደጋፊ ሆኖ በመቅረቡ እንግሊዞችና አሜሪካኖችን ሲያስገርማቸው፣ ለፈረንሣይ መልዕክተኛ ትልቅ ደስታ ሆነ። በስምንት ወር ዕድሜ ውስጥ የመስኮብ ሀሳብ ከአንድ ጫፍ ወደሌላው ሩቅ ጫፍ የዘለለው ምን ምክንያት ቢያጋጥም ነው ? ተብሎ ሲውጠነጠን፣ በወቅቱ በጣልያን አገር ውስጥ የሚተራመሰው የፖለቲካ ንቅናቄ ለኮሙኒስቶች ወደ ሥልጣን መቅረብ የሚረዳ መስሎ ስለታየ፤ ሶቪየት ሕብረት ቀደም ብሎ ከወደፊት ባለሥልጣኖቹ ጋር የወዳጅነት ሜዳ ለማዘጋጀት ብሎ ነው የሚል ግምት ተሰጠው። በመሠረቱ በዚያን ጊዜ የተፋፋመው የጣልያን የፖለቲካ ሁኔታ ወዴት እንደሚያመራ በትክክል መተንበይ ባይቻልም፤ አዝማሚያው ወደ ግራ ሊያዘነብል እንደሚችል ያመለክት ነበር። ሆኖም የጣልያን ሕዝብ ሀይማኖቱ ስለሚገታው፣ መስኮብ እንደሚመኘው ጭልጥ ብሎ ከኮሙኒስት አዘቅት ውስጥ ይጠልቃል ለማለት ያስቸግር ነበር። በዚያን ሰዓት በጣልያን የፖለቲካ ሕይወት ውስጥ የሚጫወቱት የግራ ክንፎች የተባሉት ሶሲያሊስቶችና ኮሙኒስቶች፣ ስለቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ያላቸው ሀሳብ፣ ከቀኝ ወገን የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር አንድ ዓይነት ነው። ቅኝ ግዛቶቹ በጣልያን የተያዙት ከፋሽስት መፈጠር በፊት ስለሆነ እና፣ ከጣልያንም እጅ የተነጠቁት በፋሽስት የሥልጣን ዘመን ስለሆነ፣ አሁን አዲሲቷ ጣልያን መልሳ ልትረከባቸው ይገባል ብለው ያምናሉ። የሶቪየት መንግሥት ለቅኝ አገር ይዞታ መሯሯጥ የካፒታሊስት አገሮች ሞያ ነው እያለ ሲተች የኖረ ቢሆንም፣ አሁን ከጣልያን የግራ ወገን የፖለቲካ መሪዎች ጋር ለመወዳጀት የካፒታሊስቶችን ሀሳብ መከተል አስፈለገው።

ኮሎኒያሊስት ጣልያንን ለመርዳት በግንቦት 10 ቀን ከሶቪየት መንግሥት የተሰነዘረው አዲሱ ሀሣብ፣ ፈረንሣይ ብቻዋን ከመንጨርጨር ጩኸቷን የሚካፈልላት ትልቅ ጓደኛ ስለአገኘች፤ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዡርዥ ቢዶ በተለይ በእንግሊዝ ላይ ትልቅ ድል ያገኘ አድርጐ ቆጥሮታል። የዲስኩሩም ቃናው ተለውጦ መስኮብ ከእኔ ጋር ከሆነ ማን አለብኝ ? የሚል አቅጣጫ የያዘ መንፈስ ሆኖ ታይቷል። የካቲት 4 ቀን 1945 ዓ.ም በመስኮብ ግዛት ውስጥ በምትገኝ «ያልታ» (YALTA) በተባለች ከተማ፣ የሶስቱ ታላላቅ መንግሥታት መሪዎች (አሜሪካ፣ መስኮብ፣ ታላቋ ብሪታንያ) ስብሰባ ላይ፣ ዊንስተን ቸርችል እና አንቶኒ ኤደን፣ ፈረንሣይ አራተኛዋ ታላቅ መንግሥት ሆና እንድትቆጠርና ለወደፊቱ በኃያላኖቹ ስብሰባ ሁሉ እንድትካፈል ያደረጉት ጥረት ወሰን አልነበረውም። በዚያን ጊዜ ለፈረንሣይ ይህ ክብርና ደረጃ አይገባትም ብለው የተከራከሩትና እጅግ የተቃወሙት ማርሻል ስታሊን እና ሙሴ ሞሎቶቭ እንደነበሩ ታሪኩ ያቀርባቸዋል።

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲፈነዳ፣ አብዛኛዎቹ የፈረንሣይ የፖለቲካና የጦር መሪዎች ለሂትለር በማጐንበስ የፈጸሙት አሳፋሪ ሥራ ከታሪኩ ገጽ ሊጠፋ ባይችልም፡ ፈረንሣይ በደረሰችበት ከፍተኛው የሥልጣኔ ዕድገቷ፣ በትልቁ ታሪኳና በዓለም ላይ በስፈነው ስመጥር ካልቸሯ፣ ከኃያላኖች ገበታ እንድትለይ አያደርጋትም በማለት፣ ቸርችል የወሰደው አቋምና ሩዝቬልትም የሰጠው ድጋፍ፣ ስታሊንን ለማሸነፍና ፈረንሣይን የኃያላኖቹ ክበብ አባል ለማስደረግ አብቅቷል። በያልታ ስብሰባ ላይ የታላቋ ብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር ያን ያህል ባይጥርበት ኖሮ፡ በ 1946 ዓ.ም ዘመን ታሪክ ውስጥ የዓለምን የሠላም ውል ለማደራጀትና የብዙዎችን አገሮች ነፃነትና የወደፊት ዕድል ለመወሰን፣ ፈረንሣይ የኃያላኖች ጉባኤ አባል ለመሆን አትችልም ነበር። የፈረንሣይ ሬፑብሊክ በዚህ ዓይነት ድጋፍና ሁኔታ ከኃያላን መንግሥታቶች አንዱ ለመሆን ዕድሉን ከተቀበለች በኋላ፣

ለመጀመሪያ ጊዜ ተካፋይ ከሆነችበት ከሎንዶኑ ስብሰባ ጀምሮ፣ በዓለም ጉዳይ ላይ አስተያየቷን የምትሰጠው ከእንግሊዝና ከአሜሪካ እጅግ እየራቀች ሆነ።

ኧርነስት ቤቨን አንዳንድ ጊዜ በጦርኘር ቢዶ ሁኔታ ሲበሳጭ፣ ፈረንሣይ ከእኛ ጋር በስብሰባ መካፈል የሚገባት፣ በጦርነቱ ዘመን የጦር ኃይሎቿን ከእኛ ጋር አስተባብራ ተካፋይ በሆነችበት ጉዳይ ላይ ብቻ እንዲወሰን ያስፈልጋል። ከዚህ ውጭ ግን ፈረንሣይ ባልታየችበትና ምንም ዓይነት ተካፍሎ ባላደረገችበት ጉዳይ ውስጥ እየገባች መዘባረቅ የለባትም፤ የሚሎረቂቅ ውሳኔ ለማቅረብ እስከ መቃጣት ይደርስ ነበር። ቤቨን መንፈሉ በዚህ ሁኔታ በሚበሳጭበት ሰዓት የፈረንሣይን ጣጣ ያመጡብን የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ቸርችል እና፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አንቶኒ ኤደን ናቸው በማለት ሳያማርራቸው አልቀረም። ለጣልያን፣ ቅኝ ግዛቶቿ ካልተመለሱላት ብለው ፈረንሣይና መስኮብ የሚያደርጉት ትብብር እየጠነከረ ስለሄደ፣ የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቀደም ሲል ለሊቢያ ጉዳይ ያቀረበውን ሀሳብ አሻሽሎ፣ የሲረናይከ አውራጃ በታላቋ ብሪታንያ አስተዳደር እንዲቆይ ከተስማማችሁ፣ ለወዳጃችሁ ለጣልያን ትሪፖሊታንያን እንድትረከብ እናደርጋለን። ለሌሎቹ ለኤርትራና ለሱማሌ ግን ካለፈው የተለወጠ ሀሳብ የለም አላቸው።

ሙሴ ኒየት (አቶ እምቢ በመስኮብኛ) አሁንም እያፌዘ የተሰበሰብነው ለእነዚህ ላልታደሉ አገሮች የሚገባቸውን መብት እንዲያገኙ መፍትሔ ፍለጋ ነው እንጂ፤ ለታላቋ ብሪታንያ ጥቅም ማዳበሪያውን በያለበት ለመነስነስ አይደለም አለው። ቤቨን በበኩሉ እጸፋውን ለመመለስ ጊዜ አልወሰደም። እነዚህ ቅኝ ግዛቶች ተመልሰው ለጣልያን ከተሰጡ፣ ለዘለዓለሙ ዕድላቸው ይዘጋል ሲል ሞሎቶቭ ከስምንት ወር በፊት የተናገረውን ለውጦ ዛሬ ለጣልያን ካልተመለሱላት በማለት የሚያደርገው ሙግት እሱ እንዳለው፤ ያልታደሉት አገሮች የሚገባቸውን መብት ያገኛሉ ብሎ አይደለም። በጣልያን የፖለቲካ ሕይወት የወደፊት ጥቅም አገኝበታለሁ በሚል ሕልም መሆኑን ለመገንዘብ ማን ያቅተዋል? በማለት ደህና አድርጐ አስታጥቆታል።

በጣልያን አገር በግራ ክንፎችና በቀኝ ወገኖች መካከል በሚተራመሰው የፖለቲካ ጦርነት ውስጥ፣ የማህል አቋም ይዞ የሚንገታገተው የሲኞር አልቺዴ ዴጋስፐሪ የክርስቲያን ዴሞክራት መንግሥት፣ ኮሎኒዎቹ እንዲመለሱለት ከፈረንሣይና ከሶቪየት ሕብረት ያገኘው ድጋፍ ከፍ ያለ ተስፋ ስለሰጠው፣ የአሜሪካንን እርዳታ ለማግኘት የተለየ ጥረት አደረገ። አሜሪካ ተጨምሮ ሶስቱ ኃያላኖች ከወሰኑ፣ የታላቋ ብሪታንያ ተቃውሞ ብቻውን፣ የጣልያንን ዕድል ሊዘጋ አይችልም ብሎ አመነ። ቁጥራቸው እጅግ በርካታ የሆነው የጣልያን ዘር ያላቸው አሜሪካኖች፣ በኮሎኒዎቹ ጉዳይ የትሩማን አድሚኒስትሬሽን ጣልያንን መርዳት አለበት ብለው ተንቀሳቀሱ። በዲኘሎማሲ መስክም የጣልያን ወዳጆች የሆኑት አገሮች ላቲኖቹ፤ የአሜሪካ መንግሥት የፈረንሣይንና የመስኮብን ሀሳብ እንዲደግፍ አማሰዱ።

አሜሪካኖች በሎንዶኑ ሰብሰባ ጊዜ ለሶስቱም ቅኝ ግዛቶች የጋራ ሞግዚት አስተዳደር ቢቋቋም ይሻላል ሲሉ ያቀረቡትን ሀሳብ አሁን በመካሔድ ላይ ባለው የፓሪሱ ስብሰባ ላይ፣ አጠንክረው አላቀረቡትም። በዚህ መሐል ፈረንሣይና መስኮብ ጣልያንን ለመርዳት ያቀረቡትን ሀሳብ አሜሪካ ወደ መሰማማት አዘንብሏል የሚል ወሬ በድንገት ፓሪስ ደረሰ። ይህም ዜና ሊነፍስ የቻለው፣ በዋሽንግቶን የጣልያን አምባሳደር አልቤርቶ ታርኪያኒ (ALBERTO TARCHIANI) በዋይት ሀውስ እና

በስቴት ዲፓርትመንት እየተሯሯጠ የመንግሥቱን አቤቱታ በሚያቀርብበት ጊዜ፣ ተስፋ ያለው መልስ አግኝቻለሁ፡ እያለ የሚልከው የምሥጢር ሪፖርት በማፈትለኩ ነበር። በእውነተኛውም የታርኪያኒ ሪፖርት ያህን ያህል የፈጠራ ወሬ አልነበረም። የጣሊያንን አምባሳደር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር (JAMES BYRNES) ጀምስ በርንስ እና ፕሬዚዳንት ሐሪ ትሩማን (HARRY TRUMAN) ተቀብለው አነጋግረውታል። በዚያን ሰዓት በአሜሪካኖች በኩል ለወደፊቷ ጣልያን የመጨነቅ ዝንባሌ እንደነበረ የሚካድ አይደለም።

አቶ ጌታሁን ተስማ በዋሽንግተን የኢትዮጵያ ሚሲዮን ጉዳይ ፈጻሚ፡ ግንቦት 25 ቀን 1946 ዓ.ም ለውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ለአክሊሉ ሀብተወልድ ባስተላለፉት መልዕክት « ..... በደረሰኝ መምሪያ መሠረት የስቴት ዲፓርትመንት ኃላፊዎችን ሳነጋግር፣ በሁኔታቸው ለጣሊያን የሚያደሉ መስለው ታይተውኛል። ..... ጣልያኖች የአሜሪኖችን ድጋፍ ለማግኘት የሚያደርጉት የፕሮፓጋንዳ ማጧጧፈር ብዙ ስለሆነ፣ ጃንሆይ ለፕሬዚዳንት ትሩማን ልዩ መልዕክት ቢልኩ ይሻላል። .... ሃሳቤ የሚደገፍ ከሆነ የጃንሆይን መልዕክት በኛ ሚሲዮን በኩል ለማቅረብ ጊዜ ስለሚወስድ፣ አዲስ አበባ ባለው በአሜሪካ ሌጋሲዮን በኩል ቢተላለፍ በቶሎ ሊደርስ ይችላል። ..... በዋሽንግቶን ያለው የጣልያን አምባሳደር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩን በስልክ ሳይቀር እንደፈለገው ማነጋገር ሲችል፣ እኔ በስቴት ዲፓርትመንት ውስጥ የሚኒስትሩን ረዳት እንኳን ለማግኘት ባጭር ጊዜ ውስጥ አይፈጸምልኝም ...... » ብለዋል። የአቶ ጌታሁንን ሀሳብ በመደገፍ ጃንሆይ ለፕሬዚዳንት ትሩማን መልዕክት እንዲልኩና፣ በወቅቱ ያለውንም ሁኔታ እንዲረዱት አቶ አክሊሉ ለንጉሠ ነገሥቱ ያቀረቡት ማስታወሻ የሚከተለው ነበር።

« ....... በዋሽንግተን የግርማዊነትዎ ሌጋሲዮን ጉዳይ ፈጻሚ እቶ ጌታሁን ተስማ፣ ጣልያኖች የአሜሪካኖችን እርዳታ ለማግኘት የሚያደርጉት ጥረት የሚያሰጋ ሆኖ ስለታየው፣ ጃንሆይ ለፕሬዚዳንት ትሩማን ልዩ መልዕክት እንዲልኩ ሀሳብ አቅርቧል። ...... ጌታሁን እንዳስተዋለው፣ ጣሊያኖች የአሜሪካንን ድጋፍካገኙ፣ ወደ ቀድሞ ቅኝ ግዛቶቻቸው ወደ ሊቢያ፣ ኤርትራና ሱማሌ የመመለስ ዕድላቸውን ስማንያ በመቶ ሊያረጋግጥላቸው ይችላል። ሀያ በመቶው አጠራጣሪ ይሆናል የምለው በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው። አንደኛው ጃንሆይ እንደሚያውቁት፣ የእንግሊዞች ተንኮል እጅግ የረቀቀ ስለሆነ አሜሪካኖች ከመስኮብና ከፈረንሣይ ጋር እንዳይስለፉ አፍራሽ መንገድ ይኖራቸዋል፡ በማለት ነው። ሁለተኛው ደግሞ የመስኮብ ሀሳብ በየጊዜው የሚዋዥቅና በአንድ መሠረት ላይ ቆሞ የማይቀጥል ስለሆነ፣ ሞሎቶቭ ዛሬ ለጣልያን ደጋፊ ቢሆንም ነገ ተቃዋሚ ሆኖ ለመገኘት ምንም የሚሳነው ነገር ስለሌለ ነው። ..... ሆኖም በእኛ በኩል የተቻለውን ሁሉ ማድረግ ስላለብን፣ ከዚህ ማስታወሻ ጋር የቀረበው የጃንሆይ መልዕክት እንዲፈቀድና በአስቸኳይ ለፕሬዚዳንት ትሩማን በአሜሪካ ሌጋሲዮን በኩል እንዲላክ በታላቅ ትህትና አሳስባለሁ።....... »

## የአሜሪካ ዳኝነት

ኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ሱማሌ ወደ ግዛቷ እንዲቀላቀሉላት፡ ጣሊያን ሶስቱም የቀድሞ ኮሎኒዎቿ እንዲመለሱላት፡ ሁለቱ ባለጋራዎች የሆኑት አገሮች በየበኩላቸው የዩናይትድ ስቴትስ አፍ አሜሪካንን እርዳታ ጠየቁ።

ታላቅና መልካም ወዳጃችን ! በሚል መክፈቻ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ለፕሬዚዳንት ትሩማን በጻፉት ደብዳቤ፣ የአሜሪካኖችን ሰብዓዊ አስተያየትና ትክክለኛ ፍርድ ማግኘት እፈልጋለሁ አሉ::

« ..... ጣልያን የኢትዮጵያ ፍጹም ጠላት መሆኑን ለዓለም ሕዝብ ያስመሰከረው፣ በፋሽስት ዘመን በፈጸመው ግፍ ብቻ አይደለም:: ከ 1885 ዓ.ም እስከ 1935 ዓ.ም ድረስ ባለው በአንድ የትውልድ ዘመን ውስጥ ኢትዮጵያ ሶስት ጊዜ በጣልያን ጦር ተወግታለች::

..... በ 1885 ዓ.ም ኮሎኒያሊስቱ ጣልያን ኢትዮጵያን በሰሜንና በደቡብ ባሉት የባሕር በሮቿ በኩል ጦርነት ከፍቶ ከግዛቶቿ ላይ ኤርትራንና ሱማሌን ነጥቆ ኮሎኒዎቹ አደረጋቸው::

...... በ 1896 ዓ.ም መላ ኢትዮጵያን በቅኝ አስተዳደሩ ለመያዝ እስከ አድዋ ድረስ መጥቶ ባደረገው ጦርነት በመጨረሻው ድል ሆኖ አፍሮ ተመለሰ::

...... በ 1936 ዓ.ም ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛቱ ውስጥ ለማስገባት የፋሽስት ጦር ከፍ ያለ ዝግጅት አድርጐ መጣ:: በጦርነቱ ሰዓት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነፃነቱ የሚያደርገውን መከላከል ፊት ለፊት ገጥሞ ማሸነፍ ሲያቅተው፣ የፋሽስቱ መንግሥት በዓለም ሕግ በተከለከለ፣ በመርዝ እና በጋዝ ሕዝባችንን ጨርሶ አገራችን ገባ:: በየጊዜው ለዓለም ታላላቅ መንግሥታት ደጋግመን እንዳመለከትነው፣ በ 1896 እና በ 1936 ዓ.ም ጣልያን ከፍ ያለ ጦር ይዞ አገራችንን የወጋው፣ ድርጅቱንና መነሻውን ከኢትዮጵያ ላይ ነጥቆ በወሰዳቸው በኤርትራ እና በሱማሌ ግዛቶቻችን ላይ አድርጐ ነው::

...... ክቡርነትዎ እንደሚያውቀው በተለይ በፋሽስት ጦር ከሌሎቹ አገሮች ይልቅ የተጠቃውና ከሰብዓዊ መንፈስ ውጭ የሚያሰቅቅ ስቃይ የተቀበለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው:: ...... ይህ ለነፃነቱና ለመብቱ ከግፈኛ መንግሥት ጋር ሲዋጋና መከራ ሲቀበል የኖረ ሕዝብ፣ ከእንግዲህ ወዲህ ሠላም አግኝቶ ሕይወቱን ለማሻሻል አጥብቆ ስለሚመኝ፣ የዩናይትድ ስቴትስን ትክክለኛ ፍርድና እርዳታ ይጠይቃል:: ...... ኤርትራና ሱማሌ የኢትዮጵያ ግዛቶች ስለሆኑ፣ ለእነዚህ ሕዝቦች ከኮሎኒያሊስት እጅ መውጣትና ነፃነትን ማግኘት ትክክለኛ ትርጉሙ ወደ እናት አገራቸው ወደ ኢትዮጵያ መመለሱ ነው::

...... ኢትዮጵያ ያቀረበችው ጥያቄ በፍርድ መታየቱ ቀርቶ፣ እንደአለፈው ጊዜ የኮሎኒያሊስቱን ጥቅም ለመጠበቅ በማሰብ፣ ጠላታችን ጣልያን ወደ ኤርትራና ሱማሌ እንዲመለስ ቢወሰን፣ በታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ነፃነት ላይ መፍረድ መሆኑን፣ ለክቡርነትዎ የምናሳስበው እጅግ ከፍ ባለ የጠነከረ ስሜት ነው:: ደጋግመን መልካም አስተያየትዎን የምንጠይቀውም፣ ዳግመኛ በኢትዮጵያ ላይ ፍርድ እንዳይጐድል ነው::

...... በዚህ በአለንበት አስቸጋሪ ዘመን፣ የዓለም ሠላምና ፀጥታ መሠረት እንዲጨብጥ፣ ለአገሮች መቀራረብና መግባባት፣ ለሕዝቦች ደህንነትና ብልፅግና እንዲያመርት፣ የዩናይትድ ስቴትስ አፍ አሜሪካ መሪ ምን ያህል ከባድ ኃላፊነት እንዳለበት እናውቃለን:: ...... » ካሉ በኋላ፣ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መልዕክታቸውን የደመደሙት በሚከተሉት ቃላቶች ነበር:: « ..... ድሆች አገሮች በምኞት

በተደላደሉ ግፈኞች እንዳይጠቁ፣ የሕዝቦች ነፃነትና መብት በእኩልነት ተከብሮ እንዲኖር፣ የክቡርነትዎና የመንግሥትዎ መሠረታዊ ዓላማ መሆኑን እንዘነጋም:: በተጨማሪ የእኛን የግል አስተያየት ለማከል የምንፈልገው፣ የተባበረው ታላቁ የአሜሪካ መንግሥት ለዚህ የተወሳሰበ መከራ ለተጫነው የዓለም ሕዝብ፣ አንድ ከፍተኛ ሰብዓዊ ተግባር ሊያደርግ ይችላል ብለን የምናሳድረውን ተስፋ ነው:: ... »

ይህ የመጨረሻው ዓረፍተ ነገር ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከቀረበው ረቂቅ ውስጥ ያልነበረ ሲሆን፤ ጃንሆይ በተለመደ አነጋገራቸው የጨመሩት ቃል መሆኑ ይታወቃል:: ለዚህ የተወሳሰበ መከራ ለተጫነው የዓለም ሕዝብ የተባበረው የአሜሪካ መንግሥት አንድ ሰብዓዊ ተግባር ይሠራል ብለን እምነታችንን እናሳድራለን ያሉት ቃል፣ ከኤርትራ ጉዳይ ጋር ጨርሶ የማይገናኝ ስለሆነ፣ ምን ለማለት እንደፈለጉ ትክክለኛውን ምሥጢር ለማወቅ ምርምር አድርጌ ነበር::

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲፈጸም በአውሮፓ የምግብና የመድሀኒት እጥረት ደርሶ ሕዝቡ ሲቸገር፣ በአሜሪካ ጥጋብ ሆኖ ከመዘፈኑም በላይ፣ የእህሉም ምርት ወሰን አጥቶ እንደ ማገዶ ይጋያል እየተባለ፤ የሚነገረውን ጃንሆይ ይከታተሉ ስለነበረ፣ የአሜሪካ ሕዝብ ቸርነቱን ለሰብዓዊ ተግባር እንዲያውል ማሳሰቢያ መስጠታቸው ነው ሲሉ፣ አንዳንድ የንጉሠ ነገሥቱ ቅርብ የነበሩ ሰዎች ተርጉመውታል:: ይህንን ከተናገሩ ከአንድ ዓመት በኋላ በሰኔ ወር 1947 ዓ.ም የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጄኔራል ዦርዥ ማርሻል (GEORGE MARSHALL) በሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ዲስኩር በማድረግ ባቀረበው ፕላን መሠረት፣ የአሜሪካ መንግሥት ለአውሮፓ አገሮች የከነዳው በብዙ ሚሊያርድ ዶላር የሚቆጠር የኤኮኖሚ እርዳታ እንደ ሰብዓዊ ተግባር ሆኖ ሊቆጠር ይችል ይሆን ?.......

በፓሪሱ ስብሰባ ላይ አሜሪካኖች የሚወስዱት እርምጃ ወሳኝ ነው ተብሎ በጣልያኖች በኩል በጋለ ስሜት ስለሚጠበቅ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አልቺዴ ደጋስፐሪ በበኩሉ፤ ለፕሬዚዳንት ትሩማን ባቀረበው ሰፊ አቤቱታ፣ የገለጻቸው ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ነበሩ::

« ..... ለሀያ ዓመታት የጣልያንን ሕዝብ አፍኖ ሲያሰቃይ የኖረውንና ከዚህም አልፎ ለዓለም ጥፋት ከናዚ ጋር ተባባሪ የሆነውን የፋሽስትን መንግሥት ነቅለን ለአዲሲቷ ጣልያን አዲስ የዴሞክራሲ አስተዳደር መስርተንላታል::

..... ጣልያን በጂኦግራፊ አቀማመጧ፣ በሕዝቦቿ ብዛትና በሥልጣኔ ዕድገቷ፤ ለምዕራብ ነፃነትና ዴሞክራሲ፣ ያለባትን የኃላፊነት ድርሻ ለመፈጸም ከዩናይትድ ስቴትስ እና ከሌሎቹም ሊበራል ከሆኑት አውሮፓውያኖች ጋር ተሰልፋለች::

... ያለንበት ዓለም በኮሙኒዝምና በሊበራሊዝም ተከፋፍሎ የአይዲዎሎጂና የሥልጣን ውጊያ የሚካሄድበት ዘመን ስለሆነ፤ የጣልያንን ነፃነትና ክብር የሚያዳክም፣ የጣልያንን መብትና ጥቅም የሚፃረር እርምጃ መውሰድ፤ ጉዳቱ ለጣልያኖች ብቻ ሳይሆን ይልቁንም ለምዕራባውያኖች ጭምር መሆኑ እንዲታወቅልን ደጋግመን አስረድተናል::

... አሁን በፓሪስ በሚካሄደው የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባላይ፣ ጣልያን የቀድሞ ቅኝ ግዛቶቿን ለመረከብ ችግር ያጋጠማት በታላቋ ብሪታንያ ተቃዋሚነት ብቻ ስለሆነ የአሜሪካንን እርዳታ መጠየቅ ግዴታ

ሆኖብናል:: እንደ እውነቱ ከሆነ የእነዚህ ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ፣ ከወደቀው የፋሽስት መንግሥት ወንጀል ጋር ተጣምሮ መታየትና መመዘን የለበትም::

...... እነዚህ ቅኝ ግዛቶቻችን ሊቢያ፣ ኤርትራና ሱማሌ የተመሠረቱት፣ አገሮቹ ከምድረ በዳነት ወደ ለምነት የተለወጡት፣ ለሕዝቡ ሕይወትና እድገት አስፈላጊውን እንዲያመርቱ የተደረጉት፣ ብዙ ዘመናት በፈጀ በጣልያኖች ጥረትና መስዋዕትነት እንጂ የዛሬ ሀያ አምስት ዓመታት በተፈጠረው የፋሽስት ሥልጣን አይደለም::

... አዲሲቷ ጣልያን ለአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች ባቀረበችው ጥያቄ፣ ቅኝ ግዛቶቿን በቀድሞው ዘመን በነበረው መልክ ለመያዝ ሳይሆን፣ በተባበሩት መንግሥታት ቻርት እና በአትላንቲክ መግለጫ መሠረት በሞግዚትነት ለማስተዳደርና ለነፃነት ብቁ ለማድረግ መሆኑን ዋስትና ያለው ቃሏን ስጥታለች::

...... እንግዲህ የአሜሪካ መንግሥት እንዲረዳልን የምናመለክተው፣ የአዲሲቷ ጣልያን ጥያቄ ትክክለኛ የመብት ጉዳይ መሆኑን ነው::

...... አዲሲቷ ጣልያን ከምዕራባውያን ጋር ተሰልፋ ለዴሞክራሲና ለሕዝቦች ነፃነት መታገል የምትችለው፣ የሚጠበቅባትንም የኃላፊነት ድርሻ ከግቡ ለማድረስ የምትበቃው፣ መብቷ ሲከበርላትና አስፈላጊው ድጋፍ ሲሰጣት ስለሆነ፣ በዩናይትድ እስቴትስ ኦፍ አሜሪካ መንግሥት ላይ ሙሉ እምነት ታሳድራለች:: ...... »

ከዚህ በላይ እንደታየው፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና የጣልያን መሪ ለአሜሪካ ፕሬዚዳንት በላኳቸው መልዕክቶች፣ የየራሳቸውን አቋም ግልጽ በሆነ መንገድ በማስረዳት፣ ለየራሳቸው የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ
ጠይቀዋል::

« ..... ኤርትራና ሱማሌ ተመልሰው ለጠላታችን ከተሰጡ፣ አራቱ ኃያላን መንግሥታቶች በኢትዮጵያ ነፃነት ላይ እንደፈረዱ የሚቆጠር ነው ..... » ሲሉ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አስጠንቅቀዋል:: ጠቅላይ ሚኒስትር ደጋስፐሪ ደግሞ በበኩሉ፣ ጣልያን ቅኝ ግዛቶቿ ካልተመለሱላት ለምዕራብ ዴሞክራሲና ነፃነት የኃላፊነት ድርሻዋን መፈጸም አትችልም ብሏል:: እንግዲህ የዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ መሪ የትኛው አገር ትክክለኛ አቋም ያለው ይመስለዋል ? .... ወይም ደግሞ ለየትኛው ወገን መፍረድ የበለጠ ጥቅም ይስጠዋል ? .... የዋይት ሀውስና የስቴት ዲፓርትመንት የፖለቲካና የዲፕሎማሲ ባለሞያዎች፣ ኢትዮጵያና ጣልያን በየበኩላቸው ለጻፉት ደብዳቤ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የሚሰጠውን መልስ ለማዘጋጀት ብዙ ምርምር ማድረግ አስፈልጓቸው ነበር::

ፍርድ ተጓድሎባት የፋሽስትን መከራ እና ፈተና ስትቀበል ለኖረችው ኢትዮጵያ እንዲታዘንላት፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ አገላለጽ እጅግ የሚማርክ ሆኖ አግኝተውታል:: እንዲሁም የኮሙኒዝምን ጃንጥላ ከምዕራብ ዓለም ለመከላከል የጣልያን መዳከም ምን ያህል ጉዳት መሆኑ እንዲታወቅ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ደጋስፓሪ የሰጠው ማስጠንቀቂያ አሳሳቢ ሆኖ ታይቷቸዋል:: ስለዚህ ፕሬዚዳንት ትሩማን ለኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥትና ለጣልያን መንግሥት መሪ በሚሰጠው መልስ፣ የተላኩለት ደብዳቤዎች መድረሳቸውንና አስፈላጊውም ጥናት በመደረግ

ላይ መሆኑን ከመግለጽ በስተቀር፣ በቅኝ ግዛቶቹ ጉዳይ የአሜሪካንን የመጨረሻ ውሳኔ እንዲያውቁት ለማድረግ ጊዜው ገና ነው ተብሎ ተወሰነ።

የስቴት ዲፓርትመንት ኤክስፐርቶች፣ ወደፊት መደረግ ስለአለበት የፖሊሲ ውሳኔ ሲያጠኑ፤ የእነዚህ የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ የአራቱን ኃያላን መንግሥታት የከፋፈለ ስለሆነ፤ አሜሪካኖች ከእንግሊዞች ተለይተው ብቻቸውን መፍትሔ ለማግኘት ቢሞክሩ፣ ውጤቱ ፍሬ እንደማይሰጥ ግልጽ ሆኖ ታያቸው። እንዲሁም ግንቦት 10 ቀን 1946 ዓ.ም በፓሪሱ ስብሰባ ላይ፣ መስኮብ ከፈረንሣይ ጋር ገጥሞ ለጣልያን ሶስቱም ቅኝ ግዛቶቿ እንዲመለሱላት ያቀረበውን ሀሳብ እንግሊዞች ፀቀጥታ መቃወማቸው ትክክል መሆኑን አመኑበት። ይህ ሁሉ ሁኔታ በሰፊው ከተጠና በኋላ ዋሽንግተን የመጨረሻውን ፖሊሲ በይፋ ከማውጣቱ በፊት፣ ዩናይትድ ስቴትስ እና ታላቋ ብሪታንያ ተመሳሳይ አቋም እንዲኖራቸው፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮቹ ጀምስ በርንስ እና ኧርነስት ቤቭን ሊወያዩበት ይገባል ተብሎ ተወሰነ።

የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ገና ከመጀመሪያው በመስከረም 1945 ዓ.ም ጣልያን ወደ ቀድሞ ቅኝ ግዛቶቿ እንድትመለስ ቢደረግ፣ በተለይ የሊቢያና የኤርትራ ሕዝቦች ተቃዋሚነት ብዙ ጠንቅ እንደሚያስከትል ለዩናይትድ ስቴትስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደህና አድርጎ አስረድቶ ነበር። ምናልባትም ከዚሁ የተነሣ ይሆናል ጀምስ በርንስ በሎንዶኑ ስብሰባ ላይ በሰጠው መግለጫ፤ ጣልያን ቅኝ ግዛቶቿን ራሳቸውን እንዳይችሉ በጭቆና አስተዳድራለች በማለት ነቀፌታ ያቀረበው። እንዲሁም አሁን በግንቦት ወር የጣልያን ደጋፊ ሆኖ የሚያራብደው የሶቪየት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ በመስከረሙ የሎንዶኑ ስብሰባ ላይ፤ በአስተዳደሯ ግፈኛ ጨቋኝ የሆነችው ጣልያን ከቅኝ ግዛቶቿ መነቀል ይገባታል ብሎ መናገሩ ይታወሳል። ይህ ሁሉ የሚያሳየው የመጀመሪያው ሰሞን (በ1945 ዓ.ም) የአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች ከፈረንሣይ በስተቀር፣ ሌሎቹ ጣልያን ወደ ቅኝ ግዛቶቿ እንድትመለስ አለመፈለጋቸውን ነው። ጊዜው እየጨመረ ሲሔድ፣ ሁሉም ለየራሱ ጥቅም ፈላጊ በመሆኑ፣ የመስኮብ መንሸራተትና ከፈረንሣይ ጋር ገጥሞ ለጣልያን ማጨብጨብ፣ ለጉዳዩ አንድ ዓይነት ውሳኔ ለመስጠት አላስቻለም። በመሠረቱ በአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ምክር ቤት የሚደረገው ጥናት እንደሚያመለክተው፤ የቅኝ ግዛቶቹን ጉዳይ ለመወሰን ከፖለቲካ ጥቅም ጋር የተያያዘ መፍትሔ ለመፈለግ ነው እንጂ፣ ዳኝነትን ተመርኩዞ ፍርድ ለመስጠት አለመሆኑ እየተረጋገጠ መጣ። በፖለቲካ ጥበብ፣ መቆላለፉንና ማፍታታቱን የተካኑት እንግሊዞች ስለሆኑ፣ አሜሪካኖች የታላቋ ብሪታንያን ዘዴ ከመከተል በስተቀር ሌላ ምርጫ የላቸውም ቢባል አያስደንቅም።

ታላቋ ብሪታንያ ከብዙ ዘመናት ጀምሮ በኮሎኒዎች ጉዳይ ያላት ኤክስፔሪያንስ እጅግ የደረጀ ከመሆኑም በላይ፣ ከ1941 ዓ.ም ወዲህ እነዚህን የጣልያን ቅኝ አገሮች በቀጥታ በማስተዳደር፣ የሕዝቡን ስሜትና የአካባቢውን የፖለቲካ ሁኔታ ደህና አድርጋ ታውቃለች።ስለዚህ ለዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት የሚያዋጣው የእንግሎ አሜሪካንን ሕብረት ማጠንከርና በተመሳሳይ አቋም የሞሎቶቭን ክትቴል ለማክሸፍ ከመጣር በስተቀር፣ ሌላ ምርጫ አይኖርም የተባለው ሀሳብ ትክክልነቱ የማያጠራጥር ሆነ።

## የስብሰባው ውሳኔ

ግንቦት 10 ቀን 1946 ዓ.ም ፈረንሣይና መስኮብ በመተባበር፣ ለአዲሲቷ ጣልያን ቅኝ ግዛቶቿ ካልተመለሱላት ብለው እንደጮሁት ሁሉ፣ ከአንድ ወር በኋላ እንግሊዝና አሜሪካ በአንድነት ሆነው፣ ጣልያን ወደ ቅኝ ግዛቶቿ መመለስ አትችልም አሉ:: ይህ የእንግሎ አሜሪካኖች አቋም በጠለቀ ጥናት ላይ የተመሠረተ መሆኑን ሶቪየት ሕብረትና ፈረንሣይ እንዲያምኑበት፣ የደረደሯቸው ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ነበሩ::

« ...... የሊቢያ፣ የኤርትራና የሱማሌ ሕዝቦች የቀድሞውን የጣልያን አስተዳደር የማይቀበሉ መሆናቸውን ለታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ደጋግመው አመልክተዋል:: የሕዝቡን ጥያቄ ችላ ብለን፣ ሕዝቡ የማይፈልገውን በግዱ ታ ተቀበል ብለን ብንወስን፣ በየአገሩ ብጥብጥና እልቂት እንዲፈጠር በር መክፈት መሆኑ መታወቅ አለበት:: ....... የዓረብ አገሮች ጣልያን ወደ ሊቢያ ይመለሳል የሚል ዜና ሰምተው፣ ከፍ ያለ ተቃውሞ ለመግለጽ ትብብራቸውን በማዘጋጀት ላይ መሆናቸውን ሰምተናል:: እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ከሶስት ዓመት በፊት ሊቢያን ከጣልያን እጅ ለማስለቀቅ በተደረገው ውጊያ ዓረቦቹ ከታላቋ ብሪታንያ ጦር ጋር ተሰልፈው የተዋጉ ስለሆኑ፣ ዛሬ እነሱን የሚያሳዝን እርምጃ መውሰድ የለብንም:: ....... በጠቅላላው ጣልያን ወደ ቅኝ ግዛቶቿ እንድትመለስ ብናደርግ፣ በየአገሩ ከሚፈጠረው ከፍተኛ አደጋ ሌላ፣ ለየአገሩ ሕዝብ ደህንነትና ለራሷ ለጣልያንም ሠላም የማይሰጥ ቋሚ ችግር ስለሚሆን፣ ከዚህ ቀጥሎ በሚቀርበው ረቂቅ መፍትሔ ላይ ተነጋግረን ሁላችንም ብንስማማ በዓለም ሕዝብ ዘንድ የጨዋ ውሳኔ ሆኖ ይቆጠርልናል:: ......

1ኛ. ከጣልያን ጋር በሚደረገው የዕርቅ ውል ላይ፣ የአዲሲቷ ሬፑብሊክ መንግሥት የቀድሞዎቹን ቅኝ ግዛቶቹን፣ ሊቢያን፣ ኤርትራንና ሱማሌን በገዛ ፈቃዱ መልቀቁን እንዲያረጋግጥ፣

2ኛ. ውሉ ተፈርሞ በሥራ ላይ ከሚውልበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አራቱ ኃያላኖች በእያንዳንዱ ቅኝ አገር መርማሪ ኮሚሽን ልከው የሕዝቡን ፍላጐት ከተረዱ በኋላ፣ የአብዛኛውን ሕዝብ ጥያቄ በማክበር ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጡ፣

3ኛ. በዚህ በተወሰነው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ አራቱ ኃያላኖች ተስማምተው አንድ ውሳኔ መስጠት ካቃታቸው፣ ጉዳዩን ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አቅርበው እንዲያስወስኑ፣ ....የሚጠይቅ ነበር::

ይህ መሠረተ ሀሳቡ ከአሜሪካ መንጭቶ በታላቋ ብሪታንያ ኤክስፐርቶች የተቀነባበረው ውሳኔ ፣ የፈረንሣይንና የመስኮብን ዕቅድ የሚያፈርስ፣ ጣልያንን ከፍ ያለ የሞራል ውድቀት ላይ የሚጥል፣ ለኢትዮጵያ ኤርትራን ለማግኘት ተስፋ የሚሰጥ፣ የዓረብ አገሮችን በሊቢያ ምክንያት የሚያስደስት፣ ሆኖ ተገመተ::

የፈረንሣይ መልዕክተኞች መሪ ገርኸ ቢዶ እነዚህ በጣልያን ቅኝ አስተዳደር የኖሩ ሕዝቦች፣ ለወደፊት ዕድላቸው ፍላጐታቸው ምን እንደሆነ ሊጠየቁ ይገባል የተባለው ሀሳብ በተግባር ላይ ሊገለጽ የማይችል አጉል ቴዎሪ ነው በማለት አራከሰ:: የሶቪየት መልዕክተኛ ግን የየእንዳንዱ ቅኝ አገር ሕዝብ አስተያየቱ መታወቅ አለበት ተብሎ ከካፒታሊስቶች የቀረበውን ሀሳብ፣ እፍ

አውጥቶ ለመቃወም አልተመቸውም:: አሠሪዎች ሳይሠሩ በድሎት እየተቀማጠሉ፡ ሠራተኞች እየለፉ በድህነት እየተቆራመዱ የሚኖርበትን ዓለም ለመለወጥ፣ የሬቮሉሽን ጦር ታጥቂያለሁ ብሎ የሚፎክር መንግሥት፣ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን መብት አይገባውም ለማለት አይደፍርም:: ሙሴ ኒየት (አቶ እምቢ) እንደ ልማዱ በእነ ቤቨን የሚዘጋጅ ጥንስስ ለደህው ሕዝብ መርዝ ነው እያለ በመሳደብ፣ የቀረበውን መፍትሔ እቃወማለሁ ለማለት ከማይችልበት ሁኔታ ላይ ወደቀ:: ሆኖም መስኮብና ፈረንሣይ እየተቀባበሉ፣ በተዘጋጀው ረቂቅ መፍትሔ ላይ አንዳንድ ወልጋዳ ምክንያቶችን በመደንቀር፣ እንግሉ ሳክሶኖችን ለማበሳጨትና ውሳኔውንም ለማዘግየት ብዙ ጥረት አደረጉ::

እንግሊዙ ቤቨንና አሜሪካዊው በርንስ ኀላናቸው እንዲጸድቅላቸው፣ የቅኝ ግዛቶቹ ጉዳይ ውሳኔው ለአንድ ዓመት እንዲቆይ በመደረጉ የሚሰጠው ጥቅም፣ አራቱ ኃያላኖች የየአገሩን ሕዝብ አስተያየት መርምረው ለማወቅ የሚያስችላቸው ከመሆኑም በላይ፡ ጉዳዩን በእርጋታ ለማጥናትና ለዘለቄታው የሚስማማ መፍትሔ ለመስጠት ይረዳቸዋል እያሉ፣ የማግባቢያ ዲስኩራቸውን ቀጠሉ::

## የሙሴ ኒየት ቀኝ ኋላ ዙር

የ 1946 ዓ.ም የሰኔ ወር በጣልያን አገር፣ በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ሕዝቡ በቀጥታ የሚካፈልበት ትልቅ የፖለቲካ ምርጫ የሚደረግበት ሰሞን ነበር::መላው የጣልያን ሕዝብ (የጾታ ልዩነት ሳይኖር) ከንጉሣዊ ዘውድ እና ከሬፑብሊክ አስተዳደር የትኛውን እንደሚፈልግ፣ ከዚህም ጋር አያይዞ የፓርላማው አባል የሚሆኑትን የሕዝብ እንደራሴዎች፣ ከልዩ ልዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል እንዲመርጥ ተጠየቀ::

ለሀያ ዓመታት በፋሺዝም ጨቋኝ አስተዳደር ታስሮ የኖረ ሕዝብ፣ በአንድ ጊዜ ሙሉ ነፃነቱን አግኝቶ ሰፊ በሆነ የዴሞክራሲ ሜዳ ላይ ሲለቀቅ፣ የሚጓዝበትን መንገድ ለመምረጥ ያልለመደው ነገር በመሆኑ፡ ከፍ ያለ መደናበርና መደናቆር ደረሰበት:: ምርጫው በሚካሄድበት ሰሞን፡ ከሕዝቡ መቅበጥበጥና ችኩልነት የተነሣ፡ በየከተማውና በየአደባባዩ ብዙ ትርምስ ስለተፈጠረ፣ በሰው ሕይወት ላይ ብዙ አደጋ ሊደርስ ይችላል ተብሎ እጅግ ተፈርቶ ነበር:: ለሕዝቡ ከቀረቡት ሁለት ጥያቄዎች ውስጥ የመጀመሪያው፡ በዘውድና በሬፑብሊክ ሥርዓት መካከል የትኛው እንደሚሻል መምረጥ ሲሆን፡ የጣልያን ንጉሣዊ ቤተሰብ ከሙሶሊኒ ጋር ለሀያ ዓመታት ፋሽስት ሆኖ በመተባበሩ ምክንያት፡ የሬፑብሊክ ወገኖች ቢያሸንፉ የሚያስደንቅ ሆኖ አልተጠበቀም:: ነገር ግን የጣልያንን ያስተዳደር መልክ የሚወስነው ትልቁ ጉዳይ የፓርላማ አባሎች ምርጫ ስለሆነ፣ አሜሪካና ታላቋ ብሪታንያ ኮሙኒስቶች ለሥልጣን የሚያበቃ ኃይል አያገኙም ሲሉ፣ መስኮቦች ደግሞ የቀኙ ክፍል ተጠርጐ ጣልያን በቀይ ባንዲራ ስታሸበርቅ ለማየት ብዙ ተስፋ አደረጉ:: ምንም እንኳን የእንግሊዝና የአሜሪካ የፖለቲካ ምርጫ ኤክስፐርቶች፡ የጣልያንን ወደ ግራ መሄድ ባያምኑበትም፡ አብዛኞዎቹ የምዕራብ ጋዜጦች የኮሙኒዝም ችቦ ሮም ላይ ለመቀጣጠል እሳቱ ተዳፍኖ ይጠብቃል እያሉ ያናፍሱ ነበር:: የዓለምን ጉዳይ በማበጠር የታወቁትም ደራሲዎች፡ በዚያን ሰዓት ከምዕራብ አገሮች መካከል፣ ኮሙኒዝምን ለመቀበል የተዘጋጀች ጣልያን ብቻ ነች እያሉ ፅሰፈው ተችተዋል::

በተዓምር ይሁን በአጋጣሚ፣ የማርሻል ስታሊን መንግሥት የተመኘውና ያደረገው ትንቢት ሳይደርስለት ቀረ። በትልቁ የፓርላማ ምርጫ ከአምስት መቶ ሀምሣ ስድስት (556) መቀመጫዎች ውስጥ፤ ከሙኒስቶቹ ያገኙት አንድ መቶ አራት (104) ወንበሮች ብቻ በመሆናቸው፣ ከጠቅላላው ቁጥር ጋር ሲመዘን ሀያ ነጥብ በመቶ (20%) እንኳን ሳይሞሉ ቀሩ። ከጥቂት ወራቶች በፊት በፈረንሣይ አገር የተደረገው ተመሣሣይ የፓርላማ ምርጫ ውጤት፤ ከጣልያን ጋር ሲመዘን የተሻለ ሆኖ ተገኘ። አምስት መቶ ሰባ (570) ከሚሆኑት የፓርላማ አባሎች ውስጥ፣ የፈረንሣይ ከሙኒስቶች መቶ ስልሣ ወንበሮች በማግኘታቸው ከጠቅላላው ቁጥር ሀያ ዘጠኝ ነጥብ በመቶ (29%) ደርሰው ነበር።

በዚህ አኳኋን ብዙ ተስፋ የተደረገበት የጣልያን ምርጫ ውጤት፣ ከተጠበቀው በጣም ወርዶ መገኘቱ ስለ አበሳጫቸው፤ እነ ሙሴ ኒየት ከፍ ያለ እርዳታ ጭነው ወደ ሮማ የጀመሩትን ጉዞ በድንገት አቋርጠው « ቀኝ ኋላ ዙር » ማለት ግዴታ ሆነባቸው።

ስለ ጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ እንግሊዙ አሜሪካኖች ባቀረቡት መፍትሔ የሕዝብ መብት ተቆርቋሪ መስለው መታየታቸው፤ የረቀቀ ተንኮል ነው ብሎ ቢያምንም፣ የሶቪየት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በጣልያን የምርጫ ውጤት ምክንያት ሀሳቡን ገልብጦ፣ ከነ ቤቨን ጋር ከመስማማት በስተቀር ሌላ መንገድ ሳይኖረው ቀረ። ፈረንሣይም ጓደኛዋ ሲከዳት፣ ብቻዋን መቅረቷ ምንም ጥቅም እንደሌለው ስለተገነዘበች፣ እየቀፈፋት በእንግሊዙ አሜሪካ ሀሳብ ለመስማማት ተገደደች።

ጣልያን የቀድሞ ቅኝ ግዛቶቿን ሊቢያን፣ ኤርትራንና ሱማሌን በገዛ ፈቃዷ መልቀቋን በሚስናዳላት የዕርቅ ውል ላይ እንድትፈርም፤ የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች፤ ቤቨን፣ በርንስ፣ ሞሎቶቭ፣ ቢዶ BEVIN, BYRNES, MOLOTOV, BIDAULT) ሐምሌ 12 ቀን 1946 ዓ.ም በአንድ ቃል ተስማምተው፣ በዚሁ ወር መጨረሻ ላይ በፓሪስ የሚደረገው የሀያ አንድ አገሮች የሠላም ጉባኤ እንዲያጸድቀው አስተላለፉ።

## የፓሪስ የሠላም ጉባኤ

የሂትለር ግብረአበሮች በመሆን ከጀርመን ጦር ጋር ተሰልፈው በዓለም ላይ ጥፋት ካደረሱት ከአምስቱ አገሮች (ጣልያን፣ ሩማንያ፣ ሁንጋሪያ፣ ቡልጋሪያ፣ ፊንላድ) ጋር የሚደረጉትን የዕርቅ ስምምነቶች ለማጽደቅ ሀያ አንድ (21) አገሮች የተካፈሉበት የሠላም ጉባኤ ሐምሌ 29 ቀን 1946 ዓ.ም በፓሪስ ከተማ ተከፈተ።

አራቱ ኃያላኖች (አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሣይ፣ መስኮብ) ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባሎች መካከል፣ አሥራ ሰባት አገሮችን መርጠው በሠላሙ ጉባኤ ላይ እንዲካፈሉ ጥሪ ያደረጉላቸው፤ ከ1940 ዓ.ም ጀምሮ በሙሶሊኒ ላይ ጦር አውጀው የተዋጉ ናቸው በማለት ነው። የእነዚሀ የአሥራ ሰባት አገሮች (17) ተካፋይነት ከመጀመሪያው ሲታሰብ፣ ከአምስቱ የቀድሞ የፋሽስት አገሮች ጋር ለመፈራረም የተዘጋጀውን የዕርቅ ስምምነት ተመልክተው አጸደቁ እንዲባሉ ነው እንጂ፤ በአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች የተረቀቁትን ውሎች፣

የአንቀጹ እየገቡ ይኸ ይለወጥ፣ ይኸ ይሻሻል እያሉ ያስቸግራሉ ተብሎ አልተጠበቀም። ነገር ግን እንደ ካናዳ፣ አውስትራሊያና ኖርዌይ የመሳሰሉት አገሮች፣ « <u>እኛም በሙሉ የማቀርበው ሀሳብ መደመጥ አለበት</u> » የሚል የጠነከረ አቋም ያላቸው መሆኑ ሲታወቅ፣ አሜሪካ፣ እንግሊዝና ፈረንሣይ መስኮብን ችላ ብለው፣ የእያንዳንዱ አገር መልዕክተኛ አስተያየቱን ለጉባኤው ለመግለጽ እና እንዲጸድቅ የሚቀርበውም ውሳኔ ላይ ለመደገፍም ሆነ ለመቃወም ድምፅ መስጠት ይችላል ብለው ተስማሙ።

ለጉባኤው ሥራ አመራር የተዘጋጀውን የውስጥ ደንብ የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ተሰብስበው በሚመረምሩበት ጊዜ፣ በየዐረፍተ ነገሩ « አልስማማም » እያለ ችግር ሲፈጥር የሰነበተው የመስኮብ የዲፕሎማሲ መሪ በመጨረሻ ባቀረበው ሀሳብ፣ «ማናቸውም ውሳኔ የሚጸድቀው ያለ አንዳች ተቃውሞ በአንድ ድምፅ ስንቀበለው ብቻ ነው » ብሎ ጠመመ። ይህንን የደረቀ አስቸጋሪ ሀሳብ ምዕራባውያኖች አንቀበልም ስላሉ፣ ክርክሩ እየጋለ ብዙ ጊዜ ፈጀ። በመጨረሻው የሙሴ ሞሎቶቭ ጊዜያዊ ወዳጅ የሆነው ፈረንሣዩ ገርጎር ቢዶ ይህንን በመሰለ ትልቅ ጉባኤ ላይ፣ የሀያ አንድ አገሮችን አስተያየት በአንድ ድምፅ ለማስተባበር ጨርሶ የማይሞከር መሆኑን ሲያስረዳው፣ የመስኮብ የዲፕሎማሲ መሪ ብድንገት ከፍተኛ መገረም አሳየ። ለካስ ያ ሁሉ ክርክር ሲደረግ የቆየው በተርጓሚዎች ስህተት ኖሯል። ሙሴ ሞሎቶቭ «ማናቸውም ጉዳይ ያለአንዳች ተቃውሞ በአንድ ድምፅ መጽደቅ አለበት» ብሎ ያቀረበው ሀሳብ፣ አራቱ ኃያላኖች የሚያደርጉት ውሳኔ ማለቱ ነው እንጂ፣ ለሠላሙ ጉባኤ አድማቂ እንዲሆኑ የተጠሩትን አሥራ ሰባት አገሮች የሚጨምር አልነበረም። በሙሴ ሞሎቶቭ አስተያየት አሥራ ሰባቱ አገሮች የጉባኤው ተካፋይ እንዲሆኑ የተጠሩት፣ በታላላቆቹ አራቱ የዓለም ጌቶች ተወስኖ የሚቀርብላቸውን አሜን ብለው ከመቀበል በስተቀር፣ ይኸ ካልተጨመረ፣ ይኸ ካልተቀነሰ እያሉ፣ በድምፅ አሰጣጥ የፈለጋቸውን እንዲዘበርቁ አይደለም። ለአገሮች ነፃነትና ለሕዝቦች መብት ታጋይ ነኝ የሚለው የሶቪየት ሕብረት መንግሥት፣ ይህን የመሰለውን ሊበራል ዴሞክራሲ አይቀበልም። ለምሣሌ ከነዚህ ከአሥራ ሰባት (17) አገሮች መካከል የመስኮብ ተከታዮች የሆኑት ፖላንድ፣ ቼኮዝሎቫኪያ፣ ዩክሬንና ቤሎሩሲያ ግዳጃቸው የሙሴ ሞሎቶቭን መምሪያ ተከትለው ድምፅ መስጠት እንጂ፣ እኛም ሀሣብ አለን ለማለት አይፈቀድላቸውም። እንደዚሁም ምዕራባውያኖች፣ እንደ ካናዳ እና አውስትራሊያ የመሳሰሉት የካፒታሊስት ወገኖቻቸው፣ የየራሳቸውን ሀሳብ ሊያቀርቡ ይችላሉ የተባለውን ሙሴ ሞሎቶቭ አይዋጥለትም። ይህንን የኮንፈረንሱን የውስጥ ደንብ ለማዘጋጀት ከመስኮብ በተፈጠረው ውዝግብ ምክንያት፣ የሶስት ሳምንት ጊዜ በከንቱ ከተቃጠለ በኋላ፣ ምዕራባውያኖች እንደሚፈልጉት ማናቸውም ጉዳይ በጉባኤው ተካፋዮች የድምፅ ብልጫ ሊወሰን ይችላል ተብሎ ስምምነት ተደረገ።

## የኢትዮጵያ ተካፋይነት

በፓሪሱ የሠላም ጉባኤ ላይ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያ፣ መካፈል አትችልም ተብሎ እንቅፋት ተደቅኖባት ነበር።

ጣልያን በዓለም ጦርነት ውስጥ ከጀርመን ጐን ሆኖ የገባው በሰኔ 1940 ዓ.ም ስለሆነ፣ በዚያን ጊዜ በሙሶሊኒ ላይ ጦር አውጀዋል ከተባሉት አገሮች መካከል፣ ኢትዮጵያ የለችበትም። ከፋሽስት ጋር የገጠመችው ጦርነት የተፈጸመው በ1936 ዓ.ም ስለሆነ፣ ከአራት ዓመት በኋላ በ1940 ዓ.ም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ

ኢትዮጵያ፣ በብዙዎች አገሮች በተለይም በእንግሊዝና በፈረንሣይ መንግሥታት የታወቀችው፣ የጣልያን ኮሎኒ ሆና ነው:: ስለዚህ ሙሶሊኒ ከሂትለር ጋር ሲሠለፍ ያወጀችው ጦርነት ስለሌለ፣ ለሠላሙ ጉባኤ ልትጠራ አትችልም የሚል ሀሳብ ተፈጠረ::

አክሊሉ ሀብተወልድ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የዲፕሎማሲ መሪ፣ በአራቱ ኃያላን አገሮች እየተዘዋወሩ ከየውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮቹ፣ ከአሜሪካዊው ከጀምስ በርንስ፣ ከእንግሊዙ ኧርነስት ቤቨን፣ ከፈረንሣዩ ዦርዥ ቢዶ፣ ከመስኮቡ ሞሎቶቭ ጋር በመነጋገር፣ በኢትዮጵያ ላይ የታቀደው እርምጃ ምን ያህል አሳዛኝ እና ፍርድ የጐደለው መሆኑን በሰፊው አስረዱ::

« ...... የሙሶሊኒ ጣልያን ኢትዮጵያን የወረረው በጦርነት ነው:: የሂትለር ጀርመን ፈረንሣይን ወግቶ ከያዘው ሁኔታ የተለየ አይደለም:: የፈረንሣይ ያገር ፍቅር ተቆርቋሪዎች የጀርመንን ይዞታ አንቀበልም ብለው እንደዘመቱት ሁሉ፣ የኢትዮጵያም አርበኞች ለአምስት ዓመታት ሳያቋርጡ ከፋሽስት ጠላት ጋር በመዋጋት ቆይተዋል:: የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በስደት ወደ ሎንዶን ቢሄዱም፣ መንግሥታቸው ድል ሆኛለሁ ብሎ ከጣልያን ጋር ስምምነት አልተፈራረመም::

..... በ1941 ዓ.ም የታላቋ ብሪታንያ ጦር ፋሽስትን ከአገራችን ለማባረር ባደረገልን እርዳታ በጥቂት ወራቶች ውስጥ ድል ሊገኝ የቻለው፣ በመላ ኢትዮጵያ ግዛት ያለው የአርበኞቻችን ጦር ተባብሮ በመሰለፉ ነው:: ..... ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ፣ ከጣልያን ጋር የዕርቅ ስምምነት ለማድረግ በተዘጋጀው የሠላም ጉባኤ፣ ኢትዮጵያን ትቶ እንደ ቼኮዝሎቫኪያና እንደ ፖላንድ የመሳሰሉትን አገሮች ተካፋይ ማድረግ ትክክለኛ ፍርድ አይደለም::

..... ቼኮዝሎቫኪያ፣ ከመስከረም 1938 ዓ.ም ጀምሮ በእንግሊዝና በፈረንሣይ መልካም ፈቃድ ነፃነቷ ተገፍፎ በሂትለር እንድትዋጥ፣ በሙኒክ ኮንፌራንስ ከተፈረደባት በኋላ፣ የት ሆና ነው? በ1940 ዓ.ም በሙሶሊኒ ላይ ጦር አውጃ የተዋጋችው ?

..... ፖላንድ፣ ከመስከረም 1939 ዓ.ም ጀምሮ በሂትለር ጦር ተወርራ መንግሥቷ ከፈረሰ በኋላ፣ ከየት ተነስታ ነው ? በ1940 ዓ.ም ከፋሽስት ጋር ጦር የገጠመችው ?

..... ኢትዮጵያ ግን በ1936 ዓ.ም ከፋሽስት ጦር ጋር የተዋጋችና ከፍተኛው ጥቃት የደረሰባት የመጀመሪያዋ አገር ስትሆን፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የጦርነት ማቆሚያ ስምምነት ያላደረገችና አሁንም ከጣልያን ጋር በጦርነት ውስጥ እንዳለች የምትቆጠር ነች:: ..... እንግዲህ ከሙሶሊኒ ጦር ጋር በቀጥታ ያልተዋጉ፣ ምንም ዓይነት ቀጥታ የሆነ አደጋ ያልደረሰባቸው አገሮች እየተመረጡ ሲጠሩ፣ ያንን ሁሉ የፋሽስት ግፍና መከራ የተቀበለች፣ እስከ መጨረሻው ያለማቋረጥ የተዋጋች ኢትዮጵያ፣ ከጣልያን ጋር በሚደረገው የሰላም ውል እንዴት መካፈል አትችልም?.... »

አክሊሉ ሀብተወልድ ከዚህ በላይ በተገለጸው ሀሳብ መሠረት የኢትዮጵያን ቅሬታ ያስረዱት፣ በመጀመሪያ ለአሜሪካ፣ ቀጥሎ ለታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ነበር:: ጀምስ በርንስ እና (JAMES BYRNES) ኧርነስት ቤቨን (ERNEST BEVIN) የኢትዮጵያ ጥያቄ ተገቢ ሆኖ ስለአገኙት ወዲያውኑ



# ሞሎቶቭ እና አክሊሉ

« ...... እኛ ኢትዮጵያውያኖች የፋሽስት መከራ በወደቀብን ጊዜ የሶቪየት መንግሥት እንደሰጠን ድጋፍ፡ ዛሬም በጣልያን መንግሥት ጠላትነት የተደቀነብንን እንቅፋት ለማስወገድ እንደሚረዳን አንጠራጠርም ....... »

(አክሊሉ ሀብተወልድ)
ሰኔ 1946 ዓ.ም

ድጋፋቸውን ሰጡ:: ኢትዮጵያ ለሠላሙ ጉባኤ ተካፋይ መሆን አይገባትም ብለው የተከራከሩት መስኮብና ፈረንሣይ ናቸው:: በተለይ በጠንከረ ሁኔታ የተቃወመው የሶቪየት ሕብረት ስለሆነ፣ በአሰቸኳይ ሞሎቶቭን አነጋግሮ እሺ ማሰኘት በጣም ጠቃሚ መሆኑን የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ አክሊሉን መከራቸው:: የመስኮብ ድጋፍ ከተገኘ የፈረንሣይ መጣመም ሊጐዳ እንደማይችል ስለአመኑበት፣ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዕድላቸውን ለመሞከር ከፓሪስ በፊት ወደ ሞስኮ አመሩ::

አቶ አክሊሉ ከሞሎቶቭ ጋር ሲነጋገሩ፣ የሙሴ ኒየትን ስሜት በሚማርኩ ቃላቶች ቀስቅሶ፣ በቶሎ ድገፉን ለማግኘት፣ አቀራረባቸው የተለየ መልክ ይታይበት ነበር::

ንግግራቸውን ሲጀምሩ፣ « ...... በ1935 ዓ.ም የፋሽስት ጦር ኢትዮጵያን ባጠቃ ጊዜ፣ አሜሪካኖች ጉዳዩ አይመለከተንም ብለው በራቸውን ሲዘጉብን፣ እንግሊዞች መድፈር አቅቷቸው ሲያመነቱ፣ ፈረንሣዮች በእኛ ጀርባ ሙሶሊኒን ሲረዱ፣ ታላቁ የሶቪየት ሕብረት መንግሥት ፋሽስትን በግልጽ አውግዞ፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሰጠውን ከፍተኛ የሞራል ድጋፍ ታሪክ ምንጊዜም አይረሣውም ....... » አሉ:: ቀጥሎም ከጣልያን ጋር በሚደረገው ስምምነት ኢትዮጵያ ተካፋይ መሆን እንደሚገባት በሰፊው ካስረዱ በኋላ፣ የጣልያን መንግሥት ለኢትዮጵያ ጥሪ መተላለፍ የለበትም እያለ የሚነዛውን የፕሮፓጋንዳ ተንኮል አወገዙ:: « .... ጣልያን ድል የሆነ መንግሥት ነው:: በታሪክ እንደሚታወቀው፣ ድል የሆነ ወንጀለኛ መንግሥት የድል አድራጊዎቹን ፍርድ አሜን ብሎ መቀበል አለበት እንጂ፣ በዕርቁ ስምምነት ላይ ተካፋይ መሆን የሚገባቸውንና የማይገባቸውን አገሮች ለመምረጥ አይፈቀድለትም:: ... » ካሉ በኋላ ንግግራቸውን ሲፈጽሙ «.... ለእኛ ለታናናሽ አገሮች፣ ለነፃነታችንና ለመብታችን በቀጥታ የሚታገልልን የሶቪየት ሕብረት መንግሥት መሆኑ የታወቀ ነው:: እኛም ኢትዮጵያውያኖች የፋሽስት መከራ በወደቀብን ጊዜ የሶቪየት መንግሥት እንደሰጠን እርዳታ፣ ዛሬም በጣልያን መንግሥት ጠላትነት የተደቀነብንን እንቅፋት እንደሚያስወግድልን እንጠራጠርም ...... » በማለት የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ያለውን ጽኑ ተስፋ ለሙሴ ሞሎቶቭ አረጋገጡ::

ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት፣ ለሶቪየት ሕብረት ይህን የመሰለ የሞቀ ምሥጋና የቀረበለትና ዝናውም የተደነቀለት ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሆነ፣ የማርሻል ስታሊን የዲፕሎማሲ መሪ በደስታ ተውጦ፣ ፓሪስ በሚደረገው የሠላም ጉባኤ ኢትዮጵያ እንድትካፈል ድጋፉን ለመስጠት ጊዜ አልፈጀም::

አክሊሉ ሀብተወልድ ከአሜሪካ ከእንግሊዝና ከመስኮብ የተሰጣቸው ቃል ኢትዮጵያ ጥሪ እንደሚደርሳት ስለአረጋገጠላቸው፣ በፓሪስ ከፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር ለሚያደርጉት ንግግር ይህን ያህል አልተጨነቁበትም:: ዦርዥ ቢዶ ሲቀበላቸው፣ ኢትዮጵያ የፈረንሣይን እርዳታ እንድታገኝ ትሁት ልመና ለማቅረብ አልፈለጉም:: በአቶ አክሊሉ አስተያየት የፈረንሣይ መንግሥት ለኢትዮጵያ የማይተኛ ጠላት መሆኑን እየደጋገመ አሳይቷል:: በፋሽስት ዘመን የሙሶሊኒ ወዳጅ ሆኖ ያደረሰብን ጉዳት ባጭሩ ተወስቶ የሚቆም አይደለም:: ዛሬም በኤርትራ ጉዳይ ጣልያንን እያገዘ ማጥቃቱን ቀጥሏል:: ባለፈው መስከረም ወር 1945 ሎንዶን ላይ በተደረገው የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያ፣ ኤርትራና ሱማሌ እንዲመለሱላት ያቀረበችው ማመልከቻ፣

ከአጀንዳው ውስጥ መሠረዝ አለበት ብሎ ቀንደኛ ሆኖ የተቃወመን ዡርዥ ቢዶ ነው። አሁንም ለጣልያን በማገዝ ኢትዮጵያ ለሠላም ጉባኤ መጠራት የለባትም ብሎ የጠመመው እሱ ነው። ስለዚህ፤ ኢትዮጵያ እስከመቼ ድረስ የፈረንሣይን የተንኮል ጠባይ ስታስታምም ትኖራለች ? የተፈጸመብን በደል ሁሉ አንድ ጊዜ ቢፈነዳ እና ቢለይልን ይሻለናል የሚል አስተያየት በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ላይ አድሮ ነበር።

ከፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር ለመነጋገር ቀጠሮው ሲደረግ፤ አቶ አክሊሉ አስተያየታቸውን እንዲያለሰልሱ በፓሪስ የኢትዮጵያ ልዩ መልዕክተኛና ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ ተገኝ አጥብቀው መከሯቸው። « ...... እንዳልከው ትዕግሥት ሲበዛ መምረሩ አይቀርም። አሁን ያለኸው እጫፉ ላይ ነው። ፀብዙ ጥረት የሰስቱን ኃያላን መንግሥታት እርዳታ አግኝተሃል። የፈረንሣይን ካሰጨመርክበት፣ ኢትዮጵያ የጠላቷን ድል መሆን የሚያረጋግጠውን ውል ፈራሚ ትሆናለች። እስካሁን የሚደረገውም ድካም ለአገራችን ይህንን ክብርና ደስታ ለማስገኘት ነው። ይህ ከተፈጸመ በኋላ የሚሆነውን ወደፊት ትወስናለህ ...... » አቶ አክሊሉ ይህን ካቶ ተስፋዬ ተገኝ የተሰጣቸውን ምክር ብዙ ጊዜ ሲያስታውሱት ነበር። በቀጠሮው ቀን ዡርዥ ቢዶ የኢትዮጵያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሲቀበል ያሳየው መንፈስ እጅግ የቀዘቀዘ ሆኖ አገኙት። ስለዚሁ ቀን አቶ አክሊሉ ሲያስታውሱ፤ ስውየው የፋሽስት ገጽታ ያለው ጥጋበኛ ከመሆኑም በላይ፤ ፈረንሣዮች የሚሠሩብን ተንኮል እፊቴ ላይ እየተደቀነ በእኔም በኩል ትህትና ለማሳየት ስሜቴ አልረዳኝም ብለዋል። እቢሮው ገብተው ወንበር እንደያዙ ምን ላደርግልህ እችላለሁ ? (qu'est ce que je peux faire pour vous?) የሚል ደረቅ ጥያቄ ሲያቀርብላቸው፣ የገለጹት ሀሳብ የሚከተለው ነበር።

« ...... በአሁኑ ሰዓት በአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ኢትዮጵያን የሚያሳዝን ነገር እየተፈጸመ ነው። በፈረንሣይ ዋና ከተማ በእርስዎ ሊቀመንበርነት ከጣልያን ጋር ዕርቅ ለማድረግ በሚዘጋጀው የሠላም ጉባኤ፣ ኢትዮጵያ እንድትካፈል ጥሪው እስካሁን አልደረሳትም። ጥሪው የዘገየበት ምክንያት፣ ጠላታችን የጣልያን መንግሥት ኢትዮጵያ ተካፋይ መሆን የለባትም ብሎ ያቀረበውን ሀሳብ ከኃያላን መንግሥታቶች ውስጥ አንዳንዶቹ በመደገፋቸው ነው እየተባለ ይነገራል። በእኛ በኩል አንደዚህ እየተባለ የሚነፍሰውን ወሬ አልተቀበልነውም። በፋሽስት ዘመን የተፈጸመብን ግፍ አንሰ አሁን ሠላም በሚመሠረትበት ጊዜ ደግሞ፣ ይህን የመሰለ በደል እንደማይሰነዘርብን በአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች ላይ ተስፋ እናደርጋለን።..... የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በፈረንሣይና በኢትዮጵያ መካከል ከጥንት የተጀመረው የወዳጅነት ግንኙነት ሳይደፈርስ፣ ዛሬም ነገም ወደፊትም በይበልጥ እንዲስፋፋ አጥብቀው ይፈልጋሉ። ዛሬ እኔም እዚህ የምገኘው ይህንን ፍላጐታችንን የበለጠ ለማረጋገጥና፣ እንዲሁም በሠላሙ ጉባኤ ላይ ስለ ኢትዮጵያ ተካፋይነት የወዳጃችንን የፈረንሣይ አስተያየት ለማዳመጥ ነው። ...... »

ከዚህ በላይ የተነገረውን የኢትዮጵያን ሚኒስትር አስተያየት፣ የፈረንሣይ የዲፕሎማሲ መሪ ያዳመጠው በመገረም መንፈስ ነው። ኢትዮጵያ በሠላሙ ጉባኤ ለመካፈል የፈረንሣይን እርዳታ ትለምናለች ሳይሆን፣ አስተያየቷን ለማዳመጥ ትፈልጋለች የሚለውን ቃል የዕብሪት አነጋገር አድርጐ ገምቶታል። በመሠረቱ በዋሽንግተን፣ በሎንዶንና በሞስኮ ካሉት የፈረንሣይ የዲኘሎማቲክ ሚሲዮኖች

በደረሰው መረጃ፣ ጀምስ በርንስ፣ ቤቪንና ሞሎቶቭ ኢትዮጵያ ተካፋይ እንድትሆን ቃል መስጠታቸውን ጆርጅ ቢዶ ሰምቷል። በዚህ አኳኋን የፈረንሣይ ብቻዋን መጣጣም ውጤት እንደማይሰጥ ሙሴ ቢዶ ቢገነዘብም፣ አንዳንድ የማስናከያ ዘዴ በመፈለግ፦ « ኢትዮጵያ በሠላሙ ጉባኤ ላይ ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ኮሎኒዎች የምታቀርበው ሀሳብ ምንድን ነው ? » ብሎ ጠየቀ። ጥያቄው ተንኮል ያዘለ መሆኑን ስለተረዱ፤ የኢትዮጵያ ሚኒስትር በሰጡት መልስ፦ « .... አራቱ ኃያላኖች የቀድሞዎቹን የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ በሚገባ አጥንቶ ለመወሰን፣ የአንድ ዓመት ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው ለጉባኤው የሚያቀርቡትን ሀሳብ በሙሉ ከመደገፍ በስተቀር ሌላ የምንጨምረው የለም። እንደዚሁም ከጣልያን ጋር ለሚደረገው ስምምነት፣ አራቱ ኃያላኖች ካረቀቁት የዕርቅ ውል የተለየ ሀሳብ አይኖረንም .... » አሉት። የፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ያልጠበቀው መልስ ብድንገት ዝቅ ሲልለት በጣም ተደሰተ። ኢትዮጵያ ተካፋይ ብትሆን በተለይ በኮሎኒዎቹ ጉዳይ ኤርትራና ሱማሌ ካልተሰጡኝ የሚለውን የሎንዶኑን እሰልፍ መዘግየትለቻዋን በድጋሚ አታቀርብም። በሌላውም ጉዳይ በተለይ ከጣልያን ጋር የሚደረገው ስምምነት፣ ከአራቱ ኃያላኖች ሀሳብ አታፈነግጥም። ኢትዮጵያ የምትፈልገው በሠላሙ ድርድር ነበርኩ ለማለት ስለሆነ ጥሪው እንዲደርሳት እኛም እንደግፋለን ብሎ ወሰነ።

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በቀጠሮአቸው ሰዓት በኬ. ዶርሰይ ( quai D"orsay ) ከጆርጅ ቢዶ ጽሕፈት ቤት ሲደርሱ ከቢሮው ሳይንቃነቅ እመስጥ ሆኖ በቀዘቀዘ መልክ የተቀበላቸው የፈረንሣይ ዲፕሎማሲ መሪ፣ ንግግራቸውን ፈጽመው ሲወጡ ደስ ብሎት፣ ከቢሮው ወጥቶ አውቶሞቢላቸው እስከቆመበት ድረስ በሞቀ መንፈስ ሸኛቸው።

**ኢትዮጵያ፣** በ1936 ዓ.ም በፋሽስት ጦር የተወጋችና ብዙ ፈተናዎችን በቆራጥነት የመከተች የመጀመሪያዋ አገር ነች።

**ኢትዮጵያ፣** በ1941 ዓ.ም በአርበኞቿ ጀግንነትና በወዳጅ መንግሥት እርዳታ ፋሽስትን ድል አድርጋ ነፃነቷን የመለሰች የመጀመሪያዋ አገር ነች።

**ኢትዮጵያ፣** ከ1936 ዓ.ም ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ ከጣልያን ጋር ዕርቅ ያላደረገች፤ እና የጦርነት ማቆሚያ ስምምነት ያልፈረመች አገር ነች።

**ኢትዮጵያ፣** ዛሬ ከጣልያን ጋር በሚደረገው የሠላም ድርድር፣ ከፋሽስት ጋር ከተዋጉት አገሮች መካከል ሆና የዕርቅ ስምምነቱን መፈረም ጥያቄ የማይቀርብበት ትክክለኛ መብቷ ነው።

በነዚህ መሠረታዊ በሆኑ አቋሞች ላይ ተመርኩዞው በመከራከር፤ አክሊሉ ሀብተወልድ ያደረጉት ጥረት፣ በኃያላን መንግሥታቶች ዘንድ ሰሚ አግኝቶ፤ ኢትዮጵያ በፓሪሱ የሠላም ጉባኤ ላይ ተካፋይ እንድትሆን ሐምሌ 20 ቀን 1946 ዓም ጥሪው ደረሳት። ይህ ጥሩ ዜና አዲስ አበባ ገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ሲደርስ፤ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ለቅርብ ረዳቶቻቸው፣ በጠቅላላውም ለአካባቢያቸው ዘንድ ከፍ ያለ ደስታ ሆነ። ከጃንሆይና ከጸሐፊ ትዕዛዝ

ወልደጊዮርጊስ በፓሪስ ሌጋሲዮን በኩል ለአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የደረሱት ቴሌግራሞች በአዲስ አበባ የተፈጠረውን መልካም ስሜት ያበስራሉ።

**ከግርማዊ ጃንሆይ**
*ይድረስ ካቶ አክሊሉ ሀብተወልድ*

*« .... የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ የደከምክበት ጉዳይ ፍሬ በመስጠቱ ደስ ብሎናል። የአገራችንን በዓለም ሠላም ድርድር ላይ ተካፋይ መሆን በጣም አስፈላጊነቱን ስናስብበት እንደቆየን ታስታውሳለህ። የሚደረገው የሠላም ስምምነት የዓለም መሪዎች በሚሰበሰቡበት ቢሆን ኖሮ፡ እኛም እራሳችን ፓሪስ ለመገኘት ወደ ኋላ አንልም ነበር። በሚኒስትሮች ደረጃ እንዲፈጸም መደረጉም ማለፊያ ነው። ከእያንዳንዱ የትላልቅ መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጋር ስለአደረግከው ንግግር እና እነሱም ስለሰጡህ ምላሽ በዝርዝር የላክልን ቴሌግራም ደርሶን ተመልክተነዋል። ለመስኮቡ ለሞሎቶቭ አስማምረህ የነገርከው፣ ተንኮሉን አቁሞ ወዳጅ ሆኖ እንዲረዳን አስበህ ይሆናል ብለን ስለገመትን፣ ጥሩ አድርገሃል። የፈረንሣዩን ሚኒስትር ያነጋገርክበት ሁኔታ ከሌሎቹ የተለየ ሆኖ አግኝተነዋል። ምናልባት ፈረንሣዮች በዛሬው የኤርትራ ዋና ጉዳዮችን ደጋፊዮችን ባለመሆናቸውና፣ ባለፈውም ዘመን ጠላታችንን ባለየንን የረዱ በመሆናቸው፣ የእኛን ቅሬታ ለማስማት አስበህ ይሆን ? ...... እነሱ ይግፉን እንጂ እኛ ወዳጅነታችንን እየገለጥን መቆየት የኋላ ኋላ ስለሚጠቅመን፣ ለወደፊቱ ስታገኛቸው በፍቅር አነጋግራቸው። በጠቅላላው እስከአሁን በሠራኸው ሁሉ ደስ ተሰኝተናል። በጉባኤው ጊዜ ካንተ ጋራ ስለሚሠሩት መልዕክተኞች የንተ ሀሣብ በቶሎ እንደደረሰን መርጠን እንልካቸዋለን ........ »*

**ከጸሐፊ ትዕዛዝ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ**
**የጽሕፈትና ያገር ግዛት ሚኒስትር**

*የተወደድህ አቶ አክሊሉ፣*

*« ..... አገራችን በዓለም ሠላም ስብሰባ ላይ ተካፋይ እንድትሆን በርትተህ ባገኘኸው ውጤት እዚህ የፈጠረው ደስታ ትልቅ ነው። የኔንማ ሳገኝህ ነው የምገልጽልህ። አቶ መኰንን አንድ ሁለት ቃል ጻፍለት ብለው፣ ሥራውን ገና መጀመሩ ስለሆነ፡ ሲጨርስ* FELICITATION *እለዋለሁ ይላል። የእሱን ነገር መቸም ታውቀዋለህ። ምንም ደስ ቢለው ገልጦ አያሳይም። እንደ አንተ ያለ ጥሩ ጠበቃ፣ ተሟጋች ሲረታ እፎይ ማለት ይገባው ነበር። ያንተ ሥራ ግን የተገኘውን ፍርድ ወዲያው ለማስፈጸም መታገልን ስለሚጠይቅ ሊያሳርፍህ አይችልም። ሆኖም ጉባኤው ከመጀመሩ በፊት ባሉት በነዚህ ጥቂት ቀናቶች ውስጥ ለማረፍና ሐኪምም ለማየት ያስችልህ ይሆናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በስብሰባው ላይ ያለብህ ችግር ብዙ መሆኑን አውቃለሁ። አንተን የሚረዱህን መልዕክተኞችና ቁጥራቸውን መወሰን ያንተ አስተያየት ይጠበቃልና ቶሎ ላክልን። ...... »*

ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴና ከጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ለአቶ አክሊሉ የተላከው መልዕክት እንደሚያሳየው ሞራልን ከፍ የሚያደርግና የሚያበረታታ ነው። ለጉባኤው ስለሚመደቡት መልዕክተኞች ሀሳብ እንዲሰጡ በተጠየቁት መሠረት፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ሆነው ክቡር ራስ አበበ አረጋይ የጦር



ብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ታዕዛዝ በሞስኮ የግርማዊነታቸው ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር፣ ለሠላሙ ጉባኤ ተካፋይ ለመሆን ፓሪስ በደረሱ ጊዜ፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ሲቀበሏቸው።

(ሐምሌ 1946 ዓ.ም)
(Photo AAU)

ሚኒስትር ፓሪስ እንዲመጡ፣ አክሊሉ ሀብተወልድ በፉ ካለ አስተያየት ጋር በቴሌግራም ለንጉሠ ነገሥቱ አመለከቱ።

« ..... በአምስቱ ዓመታት የጠላት ዘመን፤ ራስ አበበ አረጋይ ለአገራችን ነፃነት ያለማቋረጥ ከፋሽስት ጋር ያደረጉት ውጊያና የፈጸሙት ከፍተኛ የአርበኝነት ሞያ፣ በብዙዎች የዓለም ጋዜጦች የተጻፈላቸው በመሆኑ፣ ከጣልያን ጋር ለሚደረገው ዕርቅ የመልዕክተኞች መሪ ሆነው ፓሪስ በሚመጡ ጊዜ፣ ኢትዮጵያ እጅግ የጐላ ዝና (ፑብሊሲቴ) ታገኝበታለች። ከዚህም በላይ አገራችን በፋሽስት ጣልያን ብትያዝም አርበኞቿ ጦርነቱን ሳያቆሙ እስከ መጨረሻው መዋጋታቸውን ዓለም እንዲያውቅልን ያደረግነው ጥረት፣ ለፕሮፓጋንዳ አለመሆኑን የራስ አበበ ፓሪስ መገኘት ደህና ማስረጃ ይሆንልናል። ከራስ አበበ ጋር አንድ ሁለት ስመጥር አርበኞች ቢመጡ በጣም ጥሩ ይመስለኛል ...... » በማለት አቶ አክሊሉ የገለጹት አስተያየት ንጉሠ ነገሥቱ በቀላሉ የሚቀበሉት አልነበረም። በተለይም ራስ አበበ ኢትዮጵያን በመወከል ከፍተኛ ዝና ያስገኙልናል የሚለው ቃል፤ በልማዱ ከሚገለጸው አስተያየት የተለየ በመሆኑ፣ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት ተቀባይነትን ሊያገኝ አልቻለም። በስደተኞችና በአርበኞች መካከል ያለውን የውስጥ መቃቃር አቶ አክሊሉ በጥልቀት አያውቁትም። ያቀረቡትም ሀሳብ ከየዋህነት የመነጨ ነው በማለት ንጉሠ ነገሥቱ ቅሬታ አሳሳደሩባቸውም። ከጸሐፊ ትዕዛዛቸው ከወልደጊዮርጊስ ጋር ብቻ በመነጋገር ለፓሪሱ ስብሰባ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሰዎች እንዲሆኑ ጃንሆይ አዘዙ።

| | |
|---|---|
| 1፡ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ<br>የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር | የመልዕክተኞች<br>መሪ |
| 2. ብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ታዕዛዝ<br>በመስኮብ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር | መልዕክተኛ |
| 3. ብላታ ኤፍሬም ተወልደመድህን<br>በሎንዶን ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር | መልዕክትኛ |
| 4. አቶ ተሰፋዬ ተገኝ<br>በፓሪስ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር | መልዕክተኛ |
| 5. አቶ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድ<br>የግርማዊነታቸው ልዩ ጸሐፊ | መልዕክተኛ |
| 6. ሼክ ዑመር አሊ አዝሃሪ | መልዕክተኛ |
| 7. ሃጂ ፋራህ | መልዕክተኛ |
| 8. አቶ መንበረ ያየህይራድ | መልዕክተኛ |
| 9. ልጅ እምሩ ዘለቀ | መልዕክተኛ |
| 10. ልጅ ፋሲል ሽፈራው | መልዕክተኛ |

## በአማካሪነት የተመደቡ

- ጆን ስፔንሰር ( JOHN SPENCER)
- ጆርጅ ብላወርስ (GEORGE BLOWERS)
- ፕሮፌሰር ቤንዊች (PROF. BENTWICH)

በጠቅላላው አሥር ኢትዮጵያውያኖችና ሶስት የውጭ አገር ዜጎች ነበሩ።

ከዚህ ከኢትዮጵያ መልዕክተኞች ዝርዝር ጋር ፓሪስ በሚገኘው የኢትዮጵያ ሌጋሲዮን በኩል የተላከው ጃንሆይ በብዕራቸው የፈረሙበት ደብዳቤ እንዲህ የሚል ቃል ይገኝበታል።

*ይድረስ ካቶ አክሊሉ ሀብተወልድ እንደምን ሰንብተሃል። እኛ በሥላሴዎች ቸርነት ደህና ነን። ይኸው የጠቅላላውን ሥራ ዕምነት በአንተ ላይ ጥለን ለሠላሙ ጉባኤ የመረጥናቸው መልዕክተኞች ወደ እዚያው መጥተዋል።*

*እግዚአብሔር በሥራው ይርዳህ።*

በዚህ ደብዳቤ አቶ አክሊሉ ቀደም ሲል ያቀረቡት ሀሣብ እንኳንስ ሊፈቀድ ቀርቶ መድረስ አለመድረሱም አልተጠቀሰም። ምናልባት ቴሌግራሙ ባይደርስ ወይም የኮድ መፍታት ችግር አጋጥሞ ይሆን ወይ ? ብለው አቶ ተስፋዬን ቢጠይቋቸው፤ « .... የተላከው በትክክል ለመድረሱ እርግጠኛ ነኝ። ነገር ግን በዝምታ የታለፈው መልስ ሳያስፈልገው ቀርቶ ይሆናል ..... » አሏቸው።
አቶ አክሊሉ የአቶ ተስፋዬ ተገኝ አባባል ስላልገባቸው፣ « ..... ለጃንሆይ ቴሌግራም ልኬ መልስ ሳይሰጡኝ የቀረበት ጊዜ የለም ...... » አሉ። የአቶ ተስፋዬ መልስ በሌላ አነጋገር ያቀረብከው ሀሳብ ስላልተወደደ መልሱን መጠበቅ የለብህም፤ ማለታቸው ነበር።

አክሊሉ ሀብተወልድ በራስ አበበ ጉዳይ መልስ ባለማግኘታቸው ቅር ሲሰኙ፤ የብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ታዕዛዝ መልዕክተኛ ሆኖ በሊስቱ ውስጥ መመደብ፣ ተጨማሪ ሀሣብ ሆነባቸው። ይኸውም በስደቱ ዘመን የጃንሆይ የዲፕሎማሲ ዋና አማካሪ ሆነው ብዙ ከፍተኛ አገልግሎት የሰጡ፣ ከጦርነቱም በኋላ የመጀመሪያው የጃንሆይ ካቢኔ ሲቋቋም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩ ሰው፣ ዛሬ በመልዕክተኞች ሊስት ውስጥ ሲመድቧቸው፣ ሊያዝኑም ሊበሳጩም ይችሉ ይሆናል በማለት ነበር። በሠለጠነው ዓለም ትናንት በጠቅላይ ሚኒስትርነት ያገሩን መንግሥት ሲመራ የነበረ ሰው፣ ዛሬ ደግሞ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ ሊመደብ ይችላል። እንደዚሁም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረ፤ ኋላ አምባሳደር ቢሆን አያስገርምም። በኢትዮጵያ ግን ይህ ዓይነቱ አሠራር ሲፈጸም፣ ተመልካቹ እንደ ሽረት፣ ሰውየው ደግሞ እንደ ቅጣት ሊቆጥሩት ይችላሉ። በዚህ መንፈስ ጉዳዩን በማሰላሰል አቶ አክሊሉ የሰጉበት ጉዳይ፣ በመጨረሻው ምንም ዓይነት ችግር አልፈጠረም። ብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ፓሪስ ሲደርሱ ያሳዩት መንፈስ፤ ለሥራውም ያላቸው መልካም ሀሳብና ትጋት በጣም የሚያስደስት ስለሆነ፣ የሁለቱ ሰዎች ትብብር የጠነከረ ሆነ። አቶ አክሊሉ የሎሬንሶን የረዥም ጊዜ አገልግሎትና የሥራ ልምድ ከፍተኛ ግምት ሲሰጡት፣ ብላታ ሎሬንሶ ደግሞ በበኩላቸው የአቶ አክሊሉን ችሎታና በሥልጣንም የበላይነታቸውን ያለአንዳች ቅሬታ መቀበላቸውን አሳዩ። በመሠረቱ ምንም እንኳን በሁለቱ ሰዎች መካከል የአሥራ ሁለት ዓመት የዕድሜ ልዩነት ቢኖር፣ (ሎሬንሶ ታላቅ) ሁለቱም በአንድ ዓይነት የፈረንሣይ ካልቸር የታነጹ በመሆናቸው፣ የፖለቲካ ጠብ ከሌለ፣ በአስተሳሰብም ሆነ በሠለጠነ ቋንቋ መግባባታቸው አያጠራጥርም። ሎሬንሶ ከሞንትፐሊየ (MONTPELLIER) አክሊሉ ከሶርቦን (SORBONNE) ዩኒቨርሲቲዎች የሕግ ምሩቆች ናቸው።

የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ፓሪስ ሲደርሱ፣ በአቶ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድ በኩል ከጸሐፌ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ለአቶ አክሊሉ የተላከ አንድ«ብርቱ ምስጢር» የሚል የግል ማስታወሻ ደረሰ:: ጉዳዩ ስለ ራስ አበበ ሲሆን ቁም ነገሩ የሚከተለው ነበር::

« .... የመልዕክተኞች መሪ ሆነው የጦር ሚኒስትሩ ፓሪስ እንዲመጡ የላከው ማስታወሻ ደርሶ እንዲፈጸም ታስቦበት ነበር:: ራስ አበበ፣ በማላውቀው አገርና በማልሰማው ቋንቋ ለመሥራት ስለማልችል ይቅርብኝ አሉ:: ቀጥሎም ቢትወደድ መኰንን በሳንፍራንሲስኮው ጉባኤ ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትርነት ደረጃቸው ሳይሆን እንደ አንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ተቆጥረው የደረሰባቸውን በደል ስለሚያስታውሱ፣ ይኸው እንደገና ፓሪስ እንዲደገም አልፈልግም አሉ:: በዚህ ሁሉ ምክንያት ሀሳብህን መፈጸም ስላልተቻለ፣ በተለይ ለኤርትራ ጉዳይ የሚያስፈልጉህን ሰዎች ጨማምረን ልከናል ..... »

ጸሐፌ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ በዚያን ጊዜ ለአቶ አክሊሉ ብዙ የሚሳሱና የሚጨነቁ በመሆናቸው፣ የወጣቱ ሚኒስትር ሞራል እንዳይነካ አስማምረው የቀባቧት እንጂ፣ ጉዳዩ ያልተፈጸመበት ትክክለኛው ምክንያት ይህ አልነበረም:: እርግጥ ቢትወደድ መኰንን በውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ ላይ፣ በጠቅላይ ሚኒስትርነቴ ምን አደርጋለሁ ? ቢሉ ትክክል ነው:: እንደዚህ ማለታቸውም አያጠራጥርም:: የጦር ሚኒስትሩ ራስ አበበ ግን ፓሪስ ቢመጡ፣ በጉባኤው ላይ የሚደረገውን ሁሉ አቶ አክሊሉና ረዳቶቻቸው ስለሚሠሩ፣ ለእሳቸውም የተለየ አስተርጓሚና ረዳት ተመድቦላቸው፣ ዝነኛው የአርበኝነት ሞያቸውን በግርማ ሞገሳቸው እንዲያንፀባርቁ የታሰበ መሆኑ በትክክል ቢነገራቸው፣ እምቢ ማለታቸው ያጠራጥራል:: እውነተኛው ምሥጢር ጃንሆይ ራስ አበበ የመልዕክተኞች መሪ ሆነው እንዲሄዱ አለመፈለጋቸው ነው:: አቶ አክሊሉ ግን እዚህ ሁሉ ትርጉም ውስጥ ሳይገቡ፣ ጸሐፌ ትእዛዝ የነገሯቸውን ተቀብለው ሥራቸውን ቀጥለዋል::

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ኢትዮጵያ፤ ለዚህ ለሠላም ጉባኤ ድምጿን ማስማት የምትፈልገው፣ በመጀመሪያ ኤርትራና ሱማሌ ወደ ግዛቷ እንዲቀላቀሉላት፣ ቀጥሎም የፋሽስት ጦር በአገሪቱ ሕዝብ ላይ ላደረሰው ከፍተኛ ጉዳት የሚከፈላት የጦር ካሣ በሚገባ እንዲተመንላት ነበር:: በእነዚህ በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያላትን አቋም ለጉባኤው ከማስረዳቷ በፊት፣ የጠላቷ የጣልያን መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር የሚሰጠውን መግለጫ አዳምጦ፣ የኢትዮጵያን ሀሳብ ማቀነባበር የሚሻል መሆኑን አክሊሉና ሎሬንስ ተስማምተው ስትራቴጂ አዘጋጁ::

የትናንትናዋ ፋሽስት፤ የዛሬይቱ ሬፑብሊክ የተባለችው ጣልያን፤ ያስፈውን ድርጊቶቿን እንደምታወግዝና ፀፀቷን እንደምትገልጽ፣ የዓለም ጠንቅ በመሆን የፈጸመችውን ጠላትነቷን በወዳጅነት ለመለወጥ ምን ማድረግ እንዳሰበች፣ ከአዲሶቹ መሪዎቿ ለመስማት፣ በጉጉት የሚጠብቁት የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ብቻ ሳይሆኑ ብዙዎቹ የጉባኤው ተካፋዮች ጭምር ናቸው:: ቅዳሜ ነሐሴ 10 ቀን 1946 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በኋላ በአሥር ሰዓት የጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር ሲኞር አልቼዴ ደጋስፐሪ እንዲናገር ስለተወሰነ፤ የሀያ አንዱ አገሮች መልዕክተኞችና በብዙ መቶ የሚቆጠሩ እንግዶች፤ የስብሰባውን አዳራሽ ሞልተውት በዚያ የነሐሴ ከፍተኛ ወበቅ መተናፈሻ ጠፍቶ ነበር::



« ...... የጣልያን ኮሎኒዎች ኤርትሯ ሊቢያና ሱማሌ፤ ከፋሽስት ጥፋት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ስለሌላቸው፣ በቀጥታ ለጣልያን መመለስ ይገባቸዋል ...... »

አልቺዴ ደጋስፐሪ የጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር
(ሐምሌ 1946 ፓሪስ)

ጠቅላይ ሚኒስትር ደጋስፐሪና አራቱ ተከታዮቹ በፕሮቶኮል አስተናባሪዎች አማካይነት ከመሰብሰቢያው አዳራሽ ገብተው፣ መሐል መሐሉን እየተራመዱ፣ ከመጨረሻው ጥግ ወደተያዘላቸው ሥፍራ ሲያመሩ በግራና በቀኝ ለሚገኙት መልዕክተኞች የፈገግታ ሰላምታ ለመስጠት መሞከራቸው አልቀረም:: ነገር ግን ከአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች እንዲሁም ከሆላንድና ከብራዚል መልዕክተኞች በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ የተመለከቷቸው በተከሳተረ ገጽታና በቁጣ በደፈረሰ ዓይን ነበር:: የሲኞር ደጋስፐሪን ፀረ ፋሽስትነት የሚያደንቀው የሆላንዱ መልዕክተኛ መጀመሪያ በጭብጨባ ለመቀበል፣ ቀጥሎ በትህትና ሰላምታ ለመስጠት ሲዳዳው አይተው፣ ብዙዎቹ መልዕክተኞች በዓይኖቻቸው ሲገላምጡት፣ ሎሬንሶ ታዕዛዝ እጅግ ተበሳጩ:: ወዲያው ከሆላንዱ አጠገብ በመሄድ ወዳጅ የሚያነጋግሩ መስለው፣ « ..... ድል የሆነ ጠላት ቅጣቱን ፈጽሞ ምሕረት እስከሚቀበል፣ ሰላምታና ክብር አይገባውም:: ስለዚህ እርፈህ ተቀመጥ ..... » የሚል ቃል አሰሙት:: የሆላንዱም መልዕክተኛ ይህ ቃል የተሰጠው ለዛቻ ይሁን ለምክር፣ ነገሩ በትክክል ሳይገባው ደንግጦ፣ በደፈናው «እሺ አመሰግናለሁ» አላቸው:: ይህንን ትርኢት አይቶ እጅግ የተገረመው ከደጋስፐሪ ተከታዮች አንዱ የነበረው፣ በዚያን ዘመን የጣልያን የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር ጁሴፔ ብሩዛስካ ነው:: (GIUSSEPE BRUSASCA)

# የጣልያን ይቅርታ

« ..... የጣልያን ሕዝብ « የቀድሞ ጠላት » ሊባል የማይገባውና እውነትም የቀድሞ ጠላት ያልነበረ ነው:: ..... »

አልቺዴ ደጋስፐሪ

ቅዳሜ ነሐሴ 10 ቀን 1946 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በኋላ በአሥር ሰዓት፣ የሠላም ጉባኤው ሊቀመንበር ፈረንሣዩ ዡርዥ ቢዶ « ..... አሁን የአዲሲቷ ጣልያን መንግሥት መሪ የሚያደርገውን ንግግር እናዳምጣለን ... » ብሎ የሊቀመንበሩን ደወል ባሰማ ጊዜ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲኞር አልቺዴ ደጋስፐሪ ከአዳራሹ በስተጫፍ ከተሰጠው ወንበር ተነስቶ በአንድ የፕሮቶኮል ረዳት እየተመራ መሐል መሀሉን እየተራመደ ወደ መናገሪያው ስኀት ሲያመራ፣ እጅግ የተከዘ መንፈስ ይታይበት ነበር:: ነገር ግን ዲስኩሩን ሲጀምር፣ ገና ከመጀመሪያው የሚያሳየው፣ ጣልያን የዓለም ሠላም ጠላት ተብሎ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛነቱን አምኖ ምሕረት ለመጠየቅ ወይም ለመለማመጥ አለመዘጋጀቱን ነበር::

ቀጥሎም የሂትለር ግብረአበር የሆነውን የሙሶሊኒን መንግሥት የጣልያን ሕዝብ መደምሰሱን እና ከተባበሩት የቃል ኪዳን የጦር ኃይሎች ጋር ተሠልፎ ናዚስቶችን በመውጋት ያደረገው መስዋዕትነት እንዲታወቅለት፣ የጠቅላይ ሚኒስትር ደጋስፐሪ ትልቅ ጥረት ሆነ:: አስተያየቱን ከዚሁ ጋር በማያያዝ፣ ..... ከአገሩ ውስጥ ፋሽስቶችን ከውጭ ናዚስቶችን በመውጋት ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረገው የጣልያን ሕዝብ፣ ዛሬ ሠላም ሲመሠረት እንደ ቀድሞ ጠላት ተቆጥሮ የጠነከረ የቅጣት ውል እንዲፈርም መገደዱ ትክክለኛ ፍርድ ይሆን ?..... » በሚል ጥያቄ ከጉባኤው አስተዛዛኝ አስተያየት ለማግኘት ከሞከረ በኋላ ፣ ወደ ቅኝ ግዛቶቹ ጉዳይ ተሻገረ::